**be wed** ተጋባ
They were wed in our church. በቤተ ፡ ክርስቲያ ናችን ፡ ተጋቡ

**be wedded** ተዋሐደ
Science and art are wedded in this project. ሳይንስና ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ በዚህ ፡ እቅድ ፡ ውስጥ ፡ ተዋሕደዋል

**wedding**
1. ሰርግ. Two hundred people were invited to the wedding. ለሰርጉ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ ተጠራ
2. የሰርግ ፡ (የጋብቻ) ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት. At the end of the wedding, the priest gave his benediction. በሰርጉ ፡ (በጋብቻው) ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ ቄሱ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጠ

**wedding banquet** ሰርግ
One and all came to the wedding banquet. ማንም ፡ ሳይቀር ፡ በሰርግ ፡ ላይ ፡ ተገኘ

**wedding feast** ሰርግ
A minstrel will play songs at our wedding feast. ሰርጋችን ፡ ላይ ፡ አዝማሪ ፡ ይዘፍንልናል

**wedding guest** ለሰርግ ፡ የተጋበዘ ፡ ሰው
The wedding guests came in large numbers. ለሰርጉ ፡ የተጋበዙት ፡ ሰዎች ፡ በብዛት ፡ መጡ

**wedge** (v.), ~ **oneself** በጭንቅ ፡ ሾለከ
He wedged himself through the narrow window. በጠባቡ ፡ መስኮት ፡ ውስጥ ፡ በጭንቅ ፡ ሾለከ

**be wedged**
1. ተቀረቀረ. His foot was wedged between two rocks. እግሩ ፡ በሁለት ፡ ድንጋይ ፡ መካከል ፡ ተቀረቀረ
2. ታጨቀ. Ten people were wedged into the car. ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ መኪናው ፡ ውስጥ ፡ ታጭቀው ፡ ነበር

**wedge** (n.) ሽብልቅ
The rock was split by using wedges. ድንጋዩ ፡ በሽብልቅ ፡ ተፈለጠ

**wedlock**
*The child was born in wedlock. ልጁ ፡ የተወለደው ፡ በሕግ ፡ ከተጋቡ ፡ ወላጆች ፡ ነው
*The child was born out of wedlock. ሕፃኑ ፡ ከሕግ ፡ ጋብቻ ፡ የተወለደ ፡ አይደለም

**Wednesday** ረብ ፤ ረቡዕ

**weed** (v.) አረመ ፤ አረም ፡ ነቀለ
I have to weed the garden. አትክልቱን ፡ ማረም ፡ (አረም ፡ መንቀል) ፡ አለብኝ

**weed out** መርጦ ፡ አስወጣ
The teacher weeded out the students of bad character. መምህሩ ፡ ጠባየ ፡ መጥፎ ፡ የሆኑትን ፡ ተማሪዎች ፡ መርጦ ፡ አስወጣቸው

**weed** (n.) አረም
The whole garden is full of weeds. አትክልቱን ፡ አረም ፡ ውጦታል

**kill the weeds** አረም ፡ አረመ
Every year we kill the weeds that overgrow the path. የእግር ፡ መንገዱን ፡ የሚሸፍነውን ፡ አረም ፡ በያመቱ ፡ እናርማለን

**week** ሳምንት
I will be back in three weeks. በሦስት ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ እመለሳለሁ

**week after week** በየሳምንቱ
I find myself doing the same thing week after week. በየሳምንቱ ፡ ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ እሠራለሁ

**a week ago** ከሳምንት ፡ በፊት
He came a week ago. የመጣው ፡ ከሳምንት ፡ በፊት ፡ ነበር

**a week from now** ከሳምንት ፡ በኋላ
A week from now we'll have an exam. ከሳምንት ፡ በኋላ ፡ ፈተና ፡ ይኖረናል

**by the week** በየሳምንቱ
They pay their employees by the week. ለሠራተኞቻቸው ፡ በየሳምንቱ ፡ ይከፍሏቸዋል
[See also 'today']

**weekday** የሥራ ፡ ቀን
You may visit me any weekday. በማንኛውም ፡ የሥራ ፡ ቀን ፡ ልትጠይቀኝ ፡ ትችላለህ

**weekdays** ከሰኞ ፡ እስከ ፡ ዓርብ
The store is open weekdays. ሱቁ ፡ ከሰኞ ፡ እስከ ፡ ዓርብ ፡ ክፍት ፡ ነው

**weekend**
1. የሳምንት ፡ መጨረሻ. This weekend we start our vacation. በዚህ ፡ ሳምንት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያችንን ፡ እንጀምራለን
2. እሑድና ፡ ቅዳሜ. Try to catch up in your work by working weekends! እሑድና ፡ ቅዳሜ ፡ በመሥራት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረህበትን ፡ ለማሟላት ፡ ሞክር

**weekly** (weeklies), n. ሳምንታዊ ፡ መጽሔት
He publishes a weekly. ሳምንታዊ ፡ መጽሔት ፡ ያሳትማል

**weekly** (adj.)
1. ሳምንታዊ. Is your weekly report ready? ሳምንታዊ ፡ ሪፖርትህን ፡ አዘጋጅተሃል ?

2. (= adv.) በሳምንት. His weekly wage is $80. በሳምንት ፡ የሚያገኘው ፡ ሰማንያ ፡ ብር ፡ ነው
3. (= adv.) በየሳምንቱ. She writes a weekly letter to her parents. ለወላጆቿ ፡ በየሳምንቱ ፡ ደብዳቤ ፡ ትጽፋለች

**weep** (wept) አለቀሰ
Don't weep! I'll get you another doll. አታልቅሺ ፤ ሌላ ፡ አሻንጉሊት ፡ አመጣልሻለሁ

**weft** ማግ
The weft broke and the weaver had to begin anew. ማጉ ፡ ስለተበጠሰ ፡ ሸማኔው ፡ እንደገና ፡ መጀመር ፡ ነበረበት

**weigh** (vt.)
1. መዘነ. Please weigh this package for me! እስቲ ፡ ይህንን ፡ ጥቅል ፡ መዝንልኝ
2. አመዛዘነ. He weighs his words before speaking. ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ የሚናገረውን ፡ ያመዛዝናል
3. መረጠ. It was an important message, and he was weighing his words. በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ መልእክት ፡ ስለነበረ ፡ ቃላቱን ፡ ይመርጥ ፡ ነበር

**weigh** (vi.) መዘነ
This piece of meat weighs four pounds. ይህ ፡ ሥጋ ፡ አራት ፡ ኪሎ ፡ ይመዝናል
He weighs a lot. ብዙ ፡ ይመዝናል

**weigh against each other** አነጻጸረ
We must weigh these plans against each other. እነዚህን ፡ እቅዶች ፡ ማነጻጸር ፡ አለብን

**weigh down** ወደታች ፡ አጐበጠ
The fruit weighed the branches down. የፍሬዎቹ ፡ ክብደት ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ ወደታች ፡ አጐብጧቸዋል

**(be) weighed down**
*He is weighed down with worry. ሐሳብ ፡ ተጭኖታል

**weigh in one's favor** አስመሰገነ
His good behavior weighs in his favor. መልካም ፡ ጠባዩ ፡ ያስመሰግነዋል

**weigh on one** ከበደው
The responsibility weighs heavily on me. ኀላፊነቱ ፡ በጣም ፡ ከብዶኛል

**weigh on one's mind** ሐሳብ ፡ አሳደረበት
The theft weighs on his mind. ስርቆቱ ፡ ሐሳብ ፡ አሳድሮበታል

**weigh oneself** ተመዘነ
I weighed myself once a week. በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተመዘንኩ

**weigh out** መዘነ
The grocer weighed out the flour and butter for us. የምግብ ፡ ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ ፡ ሻጩ ፡ ዱቄትና ፡ ቅቤ ፡ መዘነልን

**weigh with one** ዋጋ ፡ አልሰጠውም
+His opinion doesn't weigh with me at all. ለሱ ፡ አስተያየት ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አልሰጠውም
[See also 'heavily']

**weight** (v.), **be weighted down with** ብዙ ፡ ተሸከመ
He was weighted down with packages. ብዙ ፡ ጥቅሎች ፡ ተሸክሞ ፡ ነበር

**weight** (n.)
1. ክብደት. My weight is 160 lbs. ክብደቱ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ነጥር ፡ ነው
Did you put down the weight of the package? የጥቅሉን ፡ ክብደት ፡ መዘገብከው ?
2. የሚዛን ፡ ድንጋይ ፤ መመዘኛ. The weights are under the scale. የሚዛኑ ፡ ድንጋዮች ፡ እሚዛኑ ፡ ሥር ፡ ናቸው
We need standard weights and measures. የተወሰነ ፡ መመዘኛና ፡ መለኪያ ፡ ያስፈልገናል
3. ሚዛን. Can you guess my weight? ሚዛኔን ፡ ልትገምት ፡ ትችላለህ ?
4. ዋጋ. Don't attach too much weight to what he says! ለሚናገረው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዋጋ ፡ አትስጠው
5. ሐሳብ. That's a great weight off my mind. ትልቅ ፡ ሐሳብ ፡ ወረደልኝ
*The weight of the responsibility bears heavily on me. ኀላፊነቱ ፡ በጣም ፡ ከብዶኛል

**lose weight** ክብደት ፡ ቀነሰ
When I was sick I lost a lot of weight. ታምሜ ፡ ሳለሁ ፡ ብዙ ፡ ክብደት ፡ ቀነስኩ

**put on weight**
He is putting on weight. ክብደቱ ፡ እየጨመረ ፡ ነው

**receive the weight of** ተሸከመ
These pillars receive the full weight of the roof. እነዚህ ፡ ምሰሶዎች ፡ ጣሪያውን ፡ በሙሉ ፡ ይሸከማሉ

**support the weight of** ተሸከመ
The pillars support the weight of the roof. ምሰሶ ፡ ጣሪያ ፡ ይሸከማል
[See also 'carry']

**weighty**
1. አሳሳቢ. The problem was too weighty for discussion to be put off. ችግሩ ፡ አሳሳቢ ፡ ስለነበረ ፡ ውይይቱን ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ ለማስተላለፍ ፡ አልተቻለም

2. አጥጋቢ. The speaker presented weighty arguments in favor of accepting the plan. ተናጋሪው ፡ እቅዱ ፡ ተቀባይነት ፡ እንዲያገኝ ፡ አጥጋቢ ፡ ማስረጃ ፡ አቀረበ
3. ከባድ. The old President could no longer deal with the weighty cares of state. ሽማግሌው ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከባድ ፡ የሆኑትን ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ሊያከናውን ፡ አልቻለም
A weighty object broke the board it rested on. ከባዱ ፡ ነገር ፡ ያረፈበትን ፡ ሳንቃ ፡ ሰበረው

**weird** እንግዳ
Something made a weird noise. አንድ ፡ ነገር ፡ እንግዳ ፡ ድምፅ ፡ አሰማ
**weird looking** ልዩ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ያለው
I saw a weird looking person in the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አየሁ

**welcome** (v.) ተቀበለ ፤ በደስታ ፡ ተቀበለ
He welcomed her with open arms. በደስታ ፡ ተቀበላት
He would welcome the opportunity to go abroad. ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለመሄድ ፡ የተሰጠውን ፡ ዕድል ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል
**welcome home** በደስታ ፡ ተቀበለው
They welcomed their son home when he returned from America. ልጃቸው ፡ ከአሜሪካ ፡ ሲመለስ ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት
**be welcomed** ተቀበሉት
+We were welcomed with open arms. እጃቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ተቀበሉን

**welcome** (n.) አቀባበል
They gave us a warm welcome. የጋለ ፡ አቀባበል ፡ አደረጉልን
*You will always have a welcome here. ምንጊዜም ፡ ብትመጣ ፡ በደስታ ፡ እንቀበልሃለን
*The chairman preceded his statement with a welcome to the audience. ሊቀ ፡ መንበሩ ፡ ከንግግሩ ፡ አስቀድሞ ፡ አዳማጮቹን ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣችሁ ፡ አለ
**welcome** (adj.)
1. በደስታ ፡ የሚቀበሉት. A welcome guest is one who brings happiness with him. በደስታ ፡ የሚቀበሉት ፡ እንግዳ ፡ ደስታን ፡ ይዞ ፡ የሚመጣ ፡ ነው
2. የሚያስደስት. That's the most welcome news I have heard in months. በስንት ፡ ወሬ ፡ የሰማሁት ፡ የሚያስደስት ፡ ወሬ ፡ ነው
**welcome home!** እንኳን ፡ ደኅና ፡ ገባህ!
**be welcome** በደስታ ፡ ተቀበለው
+You're always welcome here. እዚህ ፡ ምንጊዜም ፡ በደስታ ፡ እንቀበልሃለን
**be welcome to** ቻለ
You are welcome to use our library. በመጻሕፍት ፡ ቤታችን ፡ ልትጠቀም ፡ ትችላለህ
You are welcome to borrow my bicycle. ከፈለግህ ፡ ብስክሌቴን ፡ ልትዋስ ፡ ትችላለህ
**you are welcome!** አብሮ ፡ ይስጠን
When the beggar said "Thank you", the man replied saying "You are welcome!" ለማኙ ፡ « እግዜር ፡ ይስጥልኝ » ፡ ቢል ፡ ሰውዬው ፡ « አብሮ ፡ ይስጠን » ፡ አለ

**weld** በየደ
The plumber welded the broken pipe. ቧምቧ ፡ ሠራተኛው ፡ የተሰበረውን ፡ ቧምቧ ፡ በየደ
**weld into a (strong) team** አስተሳሰረ
Working together for a month welded them into a strong team. ላንድ ፡ ወር ፡ አብረው ፡ መሥራታቸው ፡ አስተሳሰራቸው

**welder** በያጅ
The welder left a crooked seam when he welded these plates together. በያጁ ፡ እነዚህን ፡ የብረት ፡ ሳሕኖች ፡ ሲበይድ ፡ መጋጠሚያውን ፡ አዛንፎታል

**welfare**
1. ደኅንነት. The welfare of the nation is the President's chief concern. የሀገሪቱ ፡ ደኅንነት ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስብበት ፡ ጉዳይ ፡ ነው
2. በጎ ፡ አድራጎት. The family has been living on welfare since last year. ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ከዓምና ፡ ጀምሮ ፡ በበጎ ፡ አድራጎት ፡ ይኖራል

**well** (v.) መነጨ
Water welled from the ground. ውኃ ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ መነጨ
**well up**
*Tears welled up in her eyes. ዓይኖቿ ፡ እንባ ፡ አቀረሩ

**well** (n.)
1. የውኃ ፡ ጉድጓድ. The villagers dug a well. መንደርተኞቹ ፡ የውኃ ፡ ጉድጓድ ፡ ቈፈሩ
2. ጉድጓድ. Are there oil wells in Ethiopia? ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የዘይት ፡ ጉድጓዶች ፡ አሉ ?
3. ምንጭ. The encyclopedia is a well of information. ዓውደ ፡ ጥበብ ፡ የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ ነው

**well** (adv., adj.)

1. ደኅና. He did well to leave the house before it rained. ከመዝነቡ ፡ በፊት ፡ ከቤት ፡ መውጣቱ ፡ ደኅና ፡ አድርጓል
He lives well on a rather small salary. ደሞዙ ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆንም ፡ ደኅና ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል
Well, just as you say. ደኅና ። እንዳልክ ፡ ይሁን
2. ጥሩ ፡ ነገር. He spoke well of me to the director. ለዲሬክተሩ ፡ ስለኔ ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ተናገረ
3. ጥሩ. It was well for you that no one saw you. ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያይህ ፡ መቅረቱ ፡ ላንተ ፡ ጥሩ ፡ ነው
Well spoken! I couldn't have said it better myself. ጥሩ ፡ ተናግረሃል! እኔም ፡ ራሴ ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ለመናገር ፡ አልችልም ፡ ነበር
4. ብዙ. He is well advanced in his studies. በትምህርቱ ፡ ብዙ ፡ ተራምዷል
5. ታዲያ. You don't drink coffee. Well, what would you like? ቡና ፡ አትጠጣም ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ?
6. እፎይ. Well, here we are at last! እፎይ ። ይኸው ፡ በመጨረሻ ፡ ደረስን
7. መቼም. Well, there is nothing we can do about it. መቼም ፡ ስለሱ ፡ ምንም ፡ ልናደርገው ፡ የምንችለው ፡ ነገር ፡ የለም
8. እና. Well, as I was saying, he comes from an old family. እና ፡ እንዳልኩት ፡ ከትልቅ ፡ ቤተሰብ ፡ ይወለዳል

**well done!** ጐሽ
Well done! You're a good boy. ጐሽ ። ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ነህ

**well over**
1. ከ --- የበለጠ. The exhibition brought in well over a thousand dollars. ኤግዚቢሽኑ ፡ ካንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ አስገኘ
2. ከ -- በላይ. There were well over a thousand people there. ካንድ ፡ ሺ ፡ በላይ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ተገኝቶ ፡ ነበር

**as well as**
1. -ም ፡ --- ም. He gave me money as well as advice. ገንዘብም ፡ ምክርም ፡ ሰጠኝ
2. -- ና ፡ እንዲሁም. He knows German as well as several other languages. ጀርመንኛና ፡ እንዲሁም ፡ አያሌ ፡ ቋንቋዎች ፡ ያውቃል
3. እንዲሁም. Britain as well as France gave aid to certain African countries. እንግሊዝ ፡ እንዲሁም ፡ ፈረንሳይ ፡ ላንዳንድ ፡ የአፍሪካ ፡ አገሮች ፡ እርዳታ ፡ ሰጡ

**as well as I** የኔን ፡ ያህል
He speaks German as well as I do. ጀርመንኛ ፡ የኔን ፡ ያህል ፡ ይናገራል

**be very well** ተስማማ(ው)
We are very well where we are. ያለንበት ፡ ተስማምቶናል

**be well** ተሻለ(ው) ። ዳነ
He is now well and fit for work. አሁን ፡ ተሽሎታል ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል
The child is gaining and will soon be well. የታመመው ፡ ልጅ ፡ እየተሻለው ፡ ስለሄደ ፡ በቅርቡ ፡ ይድናል

**be well again** ዳነ
You will soon be well again and be able to go to work. ቶሎ ፡ ድነህ ፡ ሥራ ፡ ለመግባት ፡ ትችላለህ

**be well off** ሀብታም ፡ ሆነ
He is well off and can afford to buy whatever he wants. ሀብታም ፡ ስለሆነ ፡ የፈለገውን ፡ ለመግዛት ፡ ይችላል

**be well on in years**
He is well on in years. በዕድሜው ፡ ገፋ ፡ ያለ ፡ ነው

**be well past**
He is well past forty. ዕድሜው ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በለጥ ፡ ይላል

**be well situated** ደኅና ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው
The house is well situated — far enough from the road so it isn't too noisy. ቤቱ ፡ ደኅና ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነው ። ከመንገዱ ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ጫጫታ ፡ የለበትም

**be well up**
*His name is well up in the list. ስሙ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያው ፡ ገደማ ፡ ነው

**do very well** ጥሩ ፡ ተካሄደ
The new business is doing very well. አዲሱ ፡ ንግድ ፡ ጥሩ ፡ ይካሄዳል

**do well**
1. ተሻለ(ው). The patient is doing very well after the operation. ከቀዶ ፡ ጥገናው ፡ በኋላ ፡ በሽተኛው ፡ በጣም ፡ ተሻለው
2. ደኅና ፡ ነው. Mother and child are doing well. እናቲቱና ፡ ሕፃኑ ፡ ደኅና ፡ ናቸው

**do well by** በሚገባ ፡ ያዘው
He has done well by his children. ልጆቹን ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ይዟቸዋል

**fairly well** ደኅና ፡ አድርጎ
He treated his son fairly well. ልጁን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያዘው

**get on well** ተስማማ
The three of us get on very well. ሦስታችን ፡ በጣም ፡ እንስማማለን

**get well (again)** ተሻለ(ው) ፤ ዳነ

Will he get well soon? በቅርቡ ፡ ይሻለው ፡ ይሆን ?

I'll do the job for you, but first I must get well again. ሥራውን ፡ እሠራልሃለሁ ፤ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ልዳን

**go well together** ተስማሙ

Do these colors go well together? እነዚህ ፡ ቀለሞች ፡ ይስማማሉ ?

**go well with** ሠመረ

All has gone well with our plans. ላቀዳችን ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ሠምሯል

**how well?** እንዴት

How well is he doing in school? በትምህርቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

How well do you know him? ዕውቂያችሁ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**it's just as well**

*It's just as well I didn't lend him the money. ለሱ ፡ ገንዘብ ፡ አለማበደሬ ፡ ደግ ፡ አድርጌያለሁ

**look well** አማረ(በት)

You look well. Were you on vacation? አምሮብሃል ፤ ዕረፍት ፡ ላይ ፡ ነበርክ ?

Doesn't this hat look well on me? ይህ ፡ ባርኔጣ ፡ አያምርብኝም ?

**(he) may as well**

We may as well begin at once. ቶሎ ፡ ብንጀምርም ፡ ያው ፡ ነው

**(he) might as well** ብ + imperfect + ይሻለዋል

You might as well stop working; it won't get you anywhere. ሥራውን ፡ ብታቆም ፡ ይሻልሃል ፤ ምንም ፡ አይጠቅምህ

**think well of**

He thinks well of me. ስለኔ ፡ ጥሩ ፡ አስተያየት ፡ አለው

**very well**

1. ደኅና ፡ አድርጎ. He did it very well. ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ሠራው

2. እሺ. Very well doctor, I will give up smoking. እሺ ፡ ዶክተር ፤ ሲጋራ ፡ ማጨስ ፡ አቆማለሁ

3. መቼም. I can't very well refuse to help him. መቼም ፡ አልረዳህም ፡ ልለው ፡ አልችልም

*He couldn't very well refuse to come. አልመጣም ፡ ሊል ፡ አይችልም ፡ ነበር

**very well then** እንግዲያውስ ፡ ደኅና ፡ ነው

Very well then, we'll talk it over tomorrow. እንግዲያውስ ፡ ደኅና ፡ ነው ፤ ነገ ፡ እንነጋገርበታለን

**(he) would do well** ብ + imperfect + ይሻለዋል

You would do well to say nothing about what happened. የተደረገውን ፡ ነገር ፡ ባታነሣ ፡ ይሻልሃል

[See also 'enough, fare, full, get along, mean, mix, perfectly, stand, turn out']

### (be) well-advised

*She would be well-advised to follow the instructions. መምሪያዎቹን ፡ ብትከተል ፡ ይሻላታል

### well-balanced

1. የተመዛዘነ. He has a well-balanced outlook on life. ስለ ፡ ሕይወት ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ የተመዛዘነ ፡ ነው

2. ረጋ ፡ ያለ. He is a well-balanced person, and nothing upsets him. ረጋ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አያበሳጨውም

3. በደንብ ፡ የተመጣጠነ. Eat a well-balanced meal! በደንብ ፡ የተመጣጠነ ፡ ምግብ ፡ ብላ

### well-behaved ጨዋ

She is a well-behaved child. ጨዋ ፡ ልጅ ፡ ናት

### well-being ደኅንነት

He worked for the well-being of the nation. ለሀገሪቱ ፡ ደኅንነት ፡ ሠራ

He felt a sense of well-being. የደኅንነት ፡ ስሜት ፡ ተሰማው

### wellborn

1. ጨዋ. A lowly person may often be more polite than a wellborn person. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሰው ፡ ከጨዋ ፡ ልጅ ፡ ይልቅ ፡ ትሑት ፡ ይሆን ፡ ይሆናል

2. የሀብታም ፡ ልጅ. Since school is very expensive, only the wellborn can attend it. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ ስለሆነ ፡ ከሀብታም ፡ ልጆች ፡ በስተቀር ፡ የሚገባበት ፡ የለም

### well-bred ጨዋ

Our host was a well-bred gentleman. አስተናጋጃችን ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነበር

### well-disposed

He is well-disposed toward me. በጥሩ ፡ ዓይን ፡ ይመለከተኛል

### well-done

1. በደንብ ፡ የበሰለ. I like well-done meat. በደንብ ፡ የበሰለ ፡ ሥጋ ፡ እወዳለሁ

2. መልካም. One feels happy after a well-done job. ከመልካም ፡ ሥራ ፡ በኋላ ፡ ደስ ፡ ይለዋል

### well-founded መሠረት ፡ ያለው

His suspicion was well-founded. ጥርጣሬው ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ነበር

**(be) well-grounded** ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ አለው
He is well-grounded in the sciences. በሳይንስ ፡ ትምህርት ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ አለው

**well-informed**
*He's unusually well informed for one so young. በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ አለው

**well-intentioned** ቅን
He is well-intentioned, but clumsy. ቅን ፡ ነው ፡ ግን ፡ ቅልጥፍና ፡ ይጐድለዋል

**well-known** የታወቀ ፤ በጣም ፡ የታወቀ
"Look before you leap" is a well-known precept. ከመዝለልህ ፡ በፊት ፡ ተመልከት ፡ የሚለው ፡ የታወቀ ፡ መመሪያ ፡ ነው
He is well-known as a famous architect. በሕንጻ ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው

**well-mannered** ጨዋ
The well-mannered boy always remembers to say "thank you" when something is done for him. ጨዋ ፡ የሆነ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲያደርጉለት ፡ « አመሰግናለሁ » ፡ ማለትን ፡ አይረሳም

**well-meaning** ልበ ፡ ቅን
She is well-meaning, but she does a lot of harm. ልበ ፡ ቅን ፡ ብትሆንም ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ታደርሳለች

**(be) well-meant** በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ ነው
His remark was well-meant, but insulting all the same. አስተያየት ፡ የሰጠው ፡ በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ ቢሆንም ፡ ስድብ ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም

**well-nigh** በጣም
It's well-nigh impossible to get him to come on time. በጊዜ ፡ እንዲመጣ ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**well-off** ሀብታም
He is well-off and can afford to buy whatever he wants. ሀብታም ፡ ስለሆነ ፡ የፈለገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመግዛት ፡ ይችላል

**(be) well-read** በሰፊው ፡ አንበበ
He is well-read in Ethiopian history. ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ አንብቧል

**well-thought out** በደንብ ፡ የታሰበበት
It seems to be a well-thought out plan. በደንብ ፡ የታሰበበት ፡ እቅድ ፡ ይመስላል

**(be) well-timed** በጥሩ ፡ ጊዜ ፡ ተደረገ ፤ በተገቢ ፡ ጊዜ ፡ ነበር
The conference was well-timed. ጉባኤው ፡ በጥሩ ፡ ጊዜ ፡ ተደረገ
Your remark was well-timed. አስተያየት ፡ የሰጠኸው ፡ በተገቢው ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**well-to-do** ባለጸጋ ፤ ሀብታም
His parents are well-to-do. ወላጆቹ ፡ ባለጸጎች ፡ (ሀብታሞች) ፡ ናቸው

**well-versed** የተራቀቀ
He is well-versed in Amharic literature. ባማርኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ የተራቀቀ ፡ ነው

**welter** (v.) ተንደባለለ
The pigs weltered in the mud. አሳሞቹ ፡ ጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ይንደባለሉ ፡ ነበር

**welter** (n.)
*All we saw was a welter of bodies. ያየነው ፡ የሚፍጨረጨር ፡ ሰውነት ፡ ብቻ ፡ ነበር

**went,** see **go**

**wept,** see **weep**

**west** (n.) ምዕራብ
The wind comes from the west. ነፋሱ ፡ ከምዕራብ ፡ በኩል ፡ ይነፍሳል

**west of** ከ --- በስተምዕራብ
Our house is west of the railroad tracks. ቤታችን ፡ ከባቡሩ ፡ ሐዲድ ፡ በስተምዕራብ ፡ ነው

**west** (adj.) የምዕራብ
The west wind blows only at certain times of the year. የምዕራብ ፡ ነፋስ ፡ የሚነፍሰው ፡ ከመት ፡ ውስጥ ፡ በተወሰነ ፡ ወቅት ፡ ብቻ ፡ ነው

**west-bound** ወደ ፡ ምዕራብ ፡ የሚጓዝ
He left on the west-bound train. ወደ ፡ ምዕራብ ፡ በሚጓዘው ፡ ባቡር ፡ ሄደ

**westerly**
1. ከምዕራብ ፡ የሚነፍስ. A westerly breeze carried the boat out on the Red Sea. ከምዕራብ ፡ የሚነፍሰው ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ ነፋስ ፡ ጀልባዋን ፡ ወደ ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ገፍቶ ፡ ወሰዳት
2. የምዕራብ. The river runs in a westerly direction. ወንዙ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ አቅጣጫ ፡ ይፈሳል

**western** ከምዕራብ ፡ የሚነፍስ
The western wind is strong today. ከምዕራብ ፡ የሚነፍሰው ፡ ነፋስ ፡ ዛሬ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው

**Western world** የምዕራብ ፡ አገሮች
The Western world was unaffected by the change. በለውጡ ፡ የምዕራብ ፡ አገሮች ፡ አልተነኩም

**westerner** ፈረንጅ
There are many westerners in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ፈረንጆች ፡ አሉ

**westernization** የምዕራባውያን ፡ መንፈስ
Westernization has affected many countries in Africa. ብዙዎቹ ፡ የአፍሪካ ፡ ሀገሮች ፡ የምዕ ራባውያን ፡ መንፈስ ፡ ገብቶባቸዋል

**westernize** የምዕራባውያንን ፡ መንገድ ፡ ተከተለ
The Arabs are trying hard to westernize. ዐረቦች ፡ የምዕራባውያንን ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ በጣም ፡ ይጥራሉ

**westward** ወደ ፡ ምዕራብ
He walked westward. ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሄደ

'**wet** (wetted, or wet), v.
1. ውኃ ፡ ነከረ. Wet the cloth before you wipe off the window! መስኮቱን ፡ ከመወልወልህ ፡ በ ፊት ፡ ጨርቁን ፡ ውኃ ፡ ንከረው
2. አረጠበ. He wet his hands, but did not wash them. እጁን ፡ አረጠበ ፡ እንጂ ፡ አልታጠበም
3. ሸና. The baby wet its bed again. ሕፃኑ ፡ እን ደገና ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ሸና

**wet** (adj.)
1. እርጥብ. Don't touch wet paint! እርጥብ ፡ ቀ ለም ፡ አትንካ
2. ዝናብ ፡ የመታው. Wet dogs have an objectionable smell. ዝናብ ፡ የመታቸው ፡ ውሾች ፡ ይ ከረፋሉ
3. (= noun) የዝናም ፡ ጊዜ. We had a wet January. ያለፈው ፡ ጥር ፡ የዝናም ፡ ጊዜ ፡ ነበር
4. የቦካ. The wheelbarrow was full of wet cement. ኩርኩሩ ፡ በቦካ ፡ ሲሚንቶ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**be wet** ራሰ ፤ በሰበሰ
His shirt was wet with perspiration. ሸሚዙ ፡ በላብ ፡ በሰብሶ ፡ (ርሶ) ፡ ነበር

**be wet with tears**
1. በእንባ ፡ ራሰ. Her cheeks were wet with tears. ጉንጮቿ ፡ በእንባ ፡ ርሰው ፡ ነበር
2. እንባ ፡ አዘለ. His eyes were wet with tears. ዓይኖቹ ፡ እንባ ፡ አዝለዋል

**get wet**
1. በሰበሰ. I got wet through and through. ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ በሰብሻለሁ
2. ረጠበ. My clothes got wet from my sweat. ልብሴ ፡ በላብ ፡ ረጥቧል
[See also 'weather']

**wet nurse** እያጠባች ፡ የምታሳድግ ፡ ሞግዚት
The woman had to hire a wet nurse for her baby. ሴትዮዋ ፡ ልጇን ፡ እያጠባች ፡ የምታሳድግ ፡ ሞግዚት ፡ መቅጠር ፡ ነበረባት

**whack** አጮለ
He whacked his child for being impudent. ስለ ፡ ብልግናው ፡ ልጁን ፡ አጮለው

**whale** ዓሣ ፡ ነባሪ
The ocean is the habitat of the whale. ውቅያኖ ስ ፡ የዓሣ ፡ ነባሪ ፡ መኖሪያ ፡ ነው

**wharf** የወደብ ፡ መድረክ
The boxes were piled up on the wharf. ሣጥኖቹ ፡ የወደቡ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ተቆልለዋል

**what ?**
1. ምን. What would you like for supper? ለራት ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ?
2. ምን ፡ ዓይነት. What's the color of the gloves? የእጅ ፡ ሹራቡ ፡ ቀለም ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ? What is that bird? ያ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ወፍ ፡ ናት ?
3. ምንድን. What is this tool for? የዚህ ፡ መሣሪ ያ ፡ አገልግሎት ፡ ምንድን ፡ ነው ?
4. ስንት. What time is it? ስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው ?
*Do you know what train we're supposed to take? በስንት ፡ ሰዓት ፡ ባቡር ፡ እንደምንሄድ ፡ ታ ውቃለህ ?

**what**
1. የ (with perfect); የም (with imperfect). That's just what I wanted to avoid. ልክ ፡ ይህን ን ፡ ነው ፡ እንዲደርስ ፡ ያልፈለግሁት
Give me what books you have on the subject! ስለ ፡ እርእስቱ ፡ ነገሩ ፡ ያለህን ፡ መጽሐፍ ፡ ስጠኝ
What little he said was full of wisdom. የተናገረ ው ፡ ትንሹ ፡ ነገር ፡ በጥበብ ፡ የተሞላ ፡ ነበር
What he says is not important. የሚለው ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ አይደለም
Borrow what books you need! የምትፈልገውን ፡ መጽሐፍ ፡ ያህል ፡ ተዋስ
Give me what paper you don't need! የማትፈልገ ውን ፡ ወረቀት ፡ ሁሉ ፡ ስጠኝ
2. ምን ፡ እንደም + (imperfect). I haven't the slightest idea what he wants. ምን ፡ እንደሚፈል ግ ፡ በፍጹም ፡ ለማወቅ ፡ አልቻልኩም
3. ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደም + (imperfect). I know what cookies you like. ምን ፡ ዓይነት ፡ ብስኩቶ ች ፡ እንደምትወድ ፡ አውቃለሁ

**what!**
1. እንዴ. What! You are late again? እንዴ ፤ አ ሁንም ፡ ዘገየህ ?
2. ምንኛ. What a pity! ምንኛ ፡ ያሳዝናል!
What few friends I have! ምንኛ ፡ ጥቂት ፡ ጓደኞች ፡ አሉኝ

3. እንዴት + (relative imperfect). What a strange coincidence! እንዴት ፡ የሚያስገርም ፡ አጋጣሚ ፡ ነው !
What beautiful flowers you have in your garden! ባትክልት ፡ ቦታህ ፡ እንዴት ፡ የሚያምሩ ፡ አበቦች ፡ አሉህ !

**what about?**
1. - ስ. What about your date? ቀጠሮህስ ?
2. ከምን ፡ ደረሰ. What about that job you applied for? የጠየቅኸው ፡ ሥራ ፡ ከምን ፡ ደረሰ ?

**what ever? ምን**
What ever happened to her? I haven't seen her for years. ምን ፡ አገኛት ? ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አላየኋትም

**what for? ለምን**
What is this thing used for? ይህ ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ያገለግላል ?
*What did you say that for? እሱን ፡ ያልክበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ?

**what if ብ** + imperfect + ስ
What if your friends don't get here at all? ጓደኞችህ ፡ እዚህ ፡ ሳይመጡ ፡ ቢቀሩስ ?
What if it rains when we're on the picnic? በሽርሽር ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ቢዘንብስ ?

**what is it like? እንዴት ፡ ነው**
What is the weather like this morning? ዛሬ ፡ ጧት ፡ ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ ነው ?

**what's more ከዚህም ፡ በላይ ፤ ከዚህም ፡ ሌላ**
(And) what's more, he is very efficient. ከዚህም ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ ቀልጣፋ ፡ ነው
What's more, I don't believe him. ከዚህም ፡ ሌላ ፡ እርሱን ፡ አላምነውም

**what of it? ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ?**
He didn't get there in time, but what of it? በጊዜው ፡ አልደረሰም ፤ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ?

**what then? ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረግ ?**
If he doesn't come, what then? ካልመጣ ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይደረግ ?

**what with**
*What with songs and games, the hours flew by. ስንዘፍንና ፡ ስንጫወት ፡ ሰዓቱ ፡ ቶሎ ፡ አለፈ

**what with all ይህ ፡ ሁሉ**
What with all I have to do, I can't be bothered with such silly things. ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ እያለብኝ ፡ እንደዚህ ፡ ባለው ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ለመቸገር ፡ አልፈልግም

**and what have you የመሳሰሉ**
He likes magazines, books, and what have you. መጽሔቶች ፡ መጻሕፍትና ፡ የመሳሰሉትን ፡ ይወዳል

**and what not ሌላም ፡ ነገር**
I have underwear and dresses and what not in that closet. ሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ የውስጥ ፡ ልብስ ፤ ቀሚስና ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ አለኝ
[See also 'degree, else, extent']

## whatever? ምንድን
Whatever made you do that? ይህን ፡ እንድታደርግ ፡ ያስገደደህ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

**whatever** (pron., adj.)
1. ምንም. I have no money whatever. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
There can be no doubt whatever about it. ስለሱ ፡ ምንም ፡ ጥርጣሬ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም
2. ማንኛውም. Whatever nonsense the newspaper prints, he believes. ጋዜጣው ፡ ላይ ፡ የሚጻፈውን ፡ ማንኛውንም ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ ያምናል
3. ምንም ፡ ነገር. Whatever you do, don't hurry! ምንም ፡ ነገር ፡ ስትሠራ ፡ አትቸኩል
4. የ + (verb). Do whatever you want. የፈለግኸውን ፡ ሥራ
5. እንደ + (verb). How much do I owe you? Whatever you say. እኔ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ አለህ ? አንተ ፡ እንዳልክ
6. (by repetition of the verb). Whatever others may say, you are right. ሌሎች ፡ ያሉትን ፡ ቢሉ ፡ አንተ ፡ ልክ ፡ ነህ
Whatever he does, is all right with me. የሚሠራውን ፡ ቢሠራ ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ ግድ ፡ የለኝም

**whatever happens የሆነ ፡ ቢሆን**
Keep calm whatever happens. የሆነ ፡ ቢሆን ፡ ረጋ ፡ በል

**any person whatever ማንም ፡ ሰው**
Any person whatever can tell you the way. ማንም ፡ ሰው ፡ መንገዱን ፡ ሊነግርህ ፡ ይችላል

## what's-his-name ማነው ፡ ስሙ
Old what's-his-name was looking for you. ሽማግሌው ፡ ማነው ፡ ስሙ ፡ ይፈልግህ ፡ ነበር

## whatsoever, no ~ ምንም + negative verb
I have no money whatsoever. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
I have no doubt whatsoever. ምንም ፡ ጥርጣሬ ፡ የለኝም

## wheat ስንዴ
The wheat is ripe. ስንዴው ፡ ደርሷል

## wheedle ተለማመጠ
The children wheedled their mother into letting them go to the picnic. ሽርሽር ፡ ለመሄ

ድ ፡ እንድትፈቅድላቸው ፡ ልጆቹ ፡ እናታቸውን ፡ ተለማመጡ

**wheel** (vt.) አሽከረከረ
The boy wheeled a cart. ልጁ ፡ ጋሪውን ፡ አሽከረከረ

**wheel** (vi.) ፊቱን ፡ አዞረ
The man wheeled to face me. ሰውዬው ፡ ሊያየኝ ፡ ፊቱን ፡ አዞረ

**wheel about** አዞረ
The rider wheeled his horse about. ጋላቢው ፡ ፈረሱን ፡ አዞረ

**wheel** (n.)
1. ጎማ ፤ መንኰራኵር. The wheels of the overturned car were sticking up in the air. የተገለበጠው ፡ መኪና ፡ ጎማዎች ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተሰቅለው ፡ ነበር
Many trucks have six wheels. ብዙ ፡ የጭነት ፡ መኪናዎች ፡ ስድስት ፡ መንኰራኵር ፡ አሉዋቸው
2. መሪ. She sat at the wheel waiting for him to get in the car. መሪው ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጣ ፡ እሱ ፡ መኪናው ፡ ውስጥ ፡ እስኪገባ ፡ ጠበቀች

**wheelbarrow** ኵርኵር
The wheelbarrow was full of wet cement. ኵርኵሩ ፡ በቦካ ፡ሲሚንቶ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**wheelchair** ተሽከርካሪ ፡ ወንበር
Since the car accident, he has to move about in a wheelchair. የመኪና ፡ አደጋ ፡ ከደረሰበት ፡ ወዲህ ፡ በተሽከርካሪ ፡ ወንበር ፡ መሄድ ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**wheeze** አቃተተ
The old man wheezed and coughed. ሽማግሌው ፡ እያቃተተ ፡ ሳለ

**whelp**
1. ቡችላ. The whelps were crying for the bitch. ቡችሎቹ ፡ ለእናታቸው ፡ ይጮኹ ፡ ነበር
2. ግልገል. The coat was made of the hide of wolf whelps. ኮቱ ፡ የተሠራው ፡ ከተኵላ ፡ ግልገሎች ፡ ቆዳ ፡ ነበር

**when ?** መቼ
When can I see you again? ዳግመኛ ፡ መቼ ፡ አገኝሃለሁ ?

**when**
1. ከ + (perfect). How can we finish when you don't help. አንተ ፡ ካልረዳኸን ፡ እንዴት ፡ ልንጨርስ ፡ እንችላለን ?
2. ስ + (imperfect). The rooster crowed when the sun rose. ፀሐይዋ ፡ ስትወጣ ፡ አውራ ፡ ዶሮው ፡ ጮኸ
You'd scarcely gone when he came. እሱ ፡ ሲመጣ ፡ ገና ፡ እግርህ ፡ መውጣቱ ፡ ነበር
How can I help them when they won't listen to me? እንሰማህም ፡ ሲሉኝ ፡ እንዴት ፡ ልረዳቸው ፡ እችላለሁ?
3. ብ + imperfect + ም. We have only three books when we need five. አምስት ፡ መጽሐፍ ፡ ቢያስፈልጉንም ፡ ያሉን ፡ ሦስት ፡ ብቻ ፡ ናቸው
4. ምን ፡ ጊዜ ፡ እንደ + (relative imperfect). They told us when to eat. ምን ፡ ጊዜ ፡ እንደምንበላ ፡ ነገሩን
*There are times when I enjoy being alone. ብቻዬን ፡ መሆን ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ ጊዜ ፡ አለ
*Sunday is the day when I can sleep late. እሑድ ፡ አርፍጄ ፡ ልተኛ ፡ የምችልበት ፡ ቀን ፡ ነው

**since when ?** ከመቼ ፡ ጀምሮ
Since when has he been missing? የጠፋው ፡ ከመቼ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ?

**till when ?** እስከመቼ
Till when can you stay? እስከመቼ ፡ ልትቆይ ፡ ትችላለህ ?

**whence, from ~ ?** ከየት
Do you know from whence she came? ከየት ፡ እንደመጣች ፡ ታውቃለህ ?
*Let him return to the country from whence he came. ወደ ፡ መጣበት ፡ አገር ፡ ይመለስ

**whenever ?** ምን ፡ ጊዜ
Whenever did he find time to write? ለመጻፍ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ አገኘ ?

**whenever** በ + perfect + ቁጥር ፡ (ጊዜ)
Come to see us whenever you have time. ጊዜ ፡ ባገኘህ ፡ ቁጥር ፡ ጠይቀን
I'll discuss it with you whenever you come. በመጣህ ፡ ጊዜ ፡ እንነጋገርበታለን

**where ?**
1. የት. Where are you going? የት ፡ ትሄዳለህ ?
Where is the nearest hotel? ቀረብ ፡ ያለው ፡ ሆቴል ፡ የት ፡ ነው ?
2. ወዴት. Where did he go next? ቀጥሎ ፡ ወዴት ፡ ሄደ ?
3. ከዬት. Where did you get the story? ወሬውን ፡ ከዬት ፡ አገኘኸው ?
*Where is he at fault? ጥፋቱ ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ነው ?

**where** (relative verb) + በት
She wants to live in a country where it never snows. በረዶ ፡ ፍጹም ፡ በማይጥልበት ፡ ሀገር ፡ ለመኖር ፡ ትፈልጋለች
This is the house where I used to live. እኖርበት ፡ የነበረው ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ ነው

They will be sent where they are needed most. በጣም ፡ ወደሚፈለጉበት ፡ ቦታ ፡ ይላካሉ
Where there is no rain, farming is difficult. ዝናብ ፡ በሌለበት ፡ ሀገር ፡ ግብርና ፡ በጣም ፡ ያዳግታል
I will go where you go. እሄድክበት ፡ እሄዳለሁ

**where ... from ?** ከዬት
Where does this chair come from? ይህ ፡ ወንበር ፡ ከየት ፡ መጣ ?
*Where does your friend come from? ጓደኛህ ፡ የየት ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ነው ?
[See also 'else']

**whereabouts**
1. የት. Whereabouts are we? የት ፡ ነን ?
2. የት ፡ እንዳለ. Can you tell me his whereabouts? የት ፡ እንዳለ ፡ ልትነግረኝ ፡ ትችላለህ ?

**whereas**
*He is fat, whereas she is thin. እሱ ፡ ወፍራም ፡ ሲሆን ፡ እሷ ፡ ግን ፡ ቀጭን ፡ ናት

**whereby** (relative verb) + በት
He devised a plan whereby he might escape. ሊያመልጥ ፡ የሚችልበትን ፡ ዘዴ ፡ ፈጠረ

**wherefore ?** ለምን
Wherefore did you leave? ለምን ፡ ሄድክ ?

**wherein ?** የት ፡ ላይ
Wherein am I mistaken? ስሕተቴ ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ?

**wherein** (relative verb) + በት
The book wherein he read the story belongs to me. ታሪኩን ፡ ያነበበበት ፡ መጽሐፍ ፡ የኔ ፡ ነው

**whereof**
*These are the things whereof I spoke. ያልኩህ ፡ ነገሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው

**whereon** (relative verb) + በት
The rock whereon he stood is not far from here. የቆመበት ፡ አለት ፡ ከዚህ ፡ ሩቅ ፡ አይደለም

**whereupon ?** በምን ፡ ላይ
Whereupon does he base his argument? ክርክሩን ፡ የመሠረተው ፡ በምን ፡ ላይ ፡ ነው ?

**whereupon** በዚያን ፡ ጊዜም
He ended his speech, whereupon everyone applauded. ንግግሩን ፡ ጨረሰ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አጨበጨበ

**wherever** የትም ፡ ብ + imperfect
Wherever you are, don't forget to write me! የትም ፡ ብትሆን ፡ ለኔ ፡ ደብዳቤ ፡ መጻፍ ፡ አትርሳ
Wherever you go in this part of the country, you'll find good roads. በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ የትም ፡ ብትሄድ ፡ ጥሩ ፡ መንገድ ፡ ታገኛለህ
*His eyes traveled after her wherever she went. በሄደችበት ፡ ሁሉ ፡ ዓይኑ ፡ ይከተላታል

**whet** (whetted) ሳለ
The farmer whets his ax before chopping wood. ዕንጨት ፡ ከመቍረጡ ፡ በፊት ፡ ገበሬው ፡ መጥረቢያውን ፡ ይስላል

**whet (one's) appetite** ወስፋቱን ፡ ከፈተ(ለት)
Exercise whets his appetite. ጅምናስቲክ ፡ ወስፋቱን ፡ ይከፍትለታል

**whether** (imperfect) + እንደሆነ
I don't know whether she will be able to come. እሷ ፡ መምጣት ፡ ትችል ፡ እንደሆን ፡ አላውቅም
I don't know whether we'll be on time for the bus. አውቶቡሱን ፡ ለማግኘት ፡ በጊዜ ፡ እንደርስ ፡ እንደሆን ፡ አላውቅም
*Does it make a difference to you whether I come. ? ብመጣ ፡ ባልመጣ ፡ ላንተ ፡ ልዩነት ፡ ያመጣል ?
*I'd like to know whether he's coming. መምጣት ፡ መቅረቱን ፡ ለማወቅ ፡ እፈልጋለሁ

**whether ... or**
*I don't know whether to accept or refuse. እሺ ፡ ወይም ፡ እምቢ ፡ ማለት ፡ እንዳለብኝ ፡ አላውቅም
*The question was whether to take the children to the funeral or leave them at home. ጥያቄው ፡ ልጆቹን ፡ ወደ ፡ ሥርዓተ ፡ ቀብሩ ፡ ይዞ ፡ መሄድ ፡ ወይም ፡ መተው ፡ ነበር

**whether ... or not**
*The race is beginning whether you are ready or not. ብትዘጋጅም ፡ ባትዘጋጅም ፡ እሽቅድምድሙ ፡ ይጀመራል
*He doesn't know whether the people there were armed or not. እዚያ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ መያዝ ፡ አለመያዛቸውን ፡ አያውቅም ፡ ነበር

**whetstone** መሳያ
He sharpens his knife on a whetstone. ቢላዋውን ፡ በመሳያ ፡ ይስላል

**whey** አጓት
Children like to drink whey. ልጆች ፡ አጓት ፡ መጠጣት ፡ ይወዳሉ

**which ?** የትኛው
Which is taller, the table or the desk? ከጠረጴዛውና ፡ ከዴስኩ ፡ የትኛው ፡ ይረዝማል ?

Which foreign language have you studied? ያጠናኸው ፡ የትኛውን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ነው ?

**which**

1. የትኛው ፡ እንደ + (relative imperfect). I know which I like best. የትኛውን ፡ ይበልጥ ፡ እንደም ፈልግ ፡ እኔ ፡ አውቃለሁ

Here are three boxes. Choose which one you like best. ሦስት ፡ ሣጥኖች ፡ እዚህ ፡ አሉ ። የት ኛውን ፡ ይበልጥ ፡ እንደምትወድ ፡ ምረጥ

2. (relative verb). Where are the books which I brought? ያመጣኋቸው ፡ መጽሐፎች ፡ የት ፡ አሉ ?

The hat (which) I wanted is sold. የፈለግሁት ፡ ባርኔጣ ፡ ተሸጧል

Read the book which looks most interesting. የሚያስደስት ፡ መስሎ ፡ የሚታይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አንብብ

**which is which**

*The twins are so much alike, I never know which is which. መንትዮቹ ፡ በጣም ፡ ስለሚ መሳሰሉ ፡ ልለያቸው ፡ ፍጹም ፡ አልችልም

**which one?** የትኛው

Which one is the right one? ትክክለኛው ፡ የት ኛው ፡ ነው ?

**which one of?** ማንኛ + suffix pronouns

Which one of you wants to go with me? ማንኛችሁ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መሄድ ፡ ትፈልጋላችሁ ?

**which one of** የትኛው ፡ እንደ + relative imperfect

Tell me which one of them is better. የትኛው ፡ እንደሚሻል ፡ ንገረኝ

**at which time?** በስንት ፡ ሰዓት

At which time will he come? At two or at five? በስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው ፡ የሚመጣው ? በስምንት ፡ ወይስ ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ?

**at which time** ያኔ

Don't call until 2, at which time I will be sure to be there. እስከ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አ ትደውል ። ያኔ ፡ ግን ፡ እርግጠኛ ፡ እዚያ ፡ እገኛለሁ

[See also 'way']

## whichever

1. (relative verb). Take whichever seat you want. እፈለግኸው ፡ መቀመጫ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥ

2. የትኛው(ንም) ፡ ብ + (imperfect). Whichever you choose, I'll buy it. የትኛውንም ፡ ብትመር ጥ ፡ እገዛዋለሁ

*Choose whichever desk you like! ደስ ፡ ያለህ ን ፡ ጠረጴዛ ፡ ምረጥ

*It's all the same whichever day you come. በፈለግኸው ፡ ቀን ፡ ብትመጣ ፡ ያው ፡ ነው

**whichever of**

*Whichever of you comes in first wins the prize. ከመካከላችሁ ፡ መጀመሪያ ፡ የደረሰ ፡ ሽልማቱን ፡ ያገኛል

**from whichever direction** ከየትም ፡ በኩል

From whichever direction he comes, we'll be ready for him. ከየትም ፡ በኩል ፡ ቢመጣ ፡ ተዘጋጅተን ፡ እንጠብቀዋለን

## whiff ብናኝ

A whiff of smoke blew in his face. የጢስ ፡ ብ ናኝ ፡ ፊቱ ፡ ላይ ፡ በነነ

## while (v.), ~ away አሳለፈ

I am whiling away my time playing tennis. ጊዜዬን ፡ የማሳልፈው ፡ ቴኒስ ፡ በመጫወት ፡ ነው

## while (conj.)

1. ስ + imperfect, or እለ. Jane was dressed in brown while Mary was dressed in blue. ጄን ፡ የለበሰችው ፡ ቡና ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ ሲሆ ን ፡ የሜሪ ፡ ግን ፡ ሰማያዊ ፡ ነበር

Some people live in luxury while others starve. አንዳንዶቹ ፡ በቅንጦት ፡ ሲኖሩ ፡ ሌሎቹ ፡ ይራባሉ

I want to come while the library is still open. ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ክፍቱን ፡ ሳለ ፡ ልመጣ ፡ እ ፈልጋለሁ

2. ብ + imperfect + ም. While I like the color of the hat, I do not like its shape. የባርኔጣውን ፡ ቀለም ፡ ብወድም ፡ ቅርጹን ፡ አልወደድኩትም

While she is not pretty, she has much charm. ቆንጆ ፡ ባትሆንም ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ አላት

3. በ + verb + ጊዜ. While I was speaking, he said nothing. እኔ ፡ በምናገርበት ፡ ጊዜ ፡ እ ሱ ፡ ምንም ፡ አልተናገረም

While in India he studied music. ህንድ ፡ ሀገር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሙዚቃ ፡ አጠና

4. ግን. John is tall while his parents are short. ቶም ፡ ረጅም ፡ ነው ። ወላጆቹ ፡ ግን ፡ አጭጮሮች ፡ ናቸው

*I want to arrive while it's still light. ሳይጨል ም ፡ ልደርስ ፡ እፈልጋለሁ

## while (n.)

**a little while** ትንሽ

Wait a little while! ትንሽ ፡ ቆይ

**a long while** ለረጅም ፡ ጊዜ ። ብዙ

He kept us waiting a long while. ለረጅም ፡ ጊ ዜ ፡ አስጠበቀን

I waited a long while for you. ብዙ ፡ ጠበቅሁህ

**a while** ትንሽ

You'll have to wait a while. ትንሽ ፡ መቆየት ፡ አለብህ

**a while ago** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት
He left a while ago. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሄደ

**all this while** ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ
Where have you been all this while? ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ የት ፡ ነበርክ ?

**for a long while** ለብዙ ፡ ጊዜ
I haven't seen him for a long while. ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ አላየሁትም

**for a while**
1. ለጊዜው. We are short of funds and cannot buy anything for a while. ገንዘብ ፡ ስላጠረን ፡ ለጊዜው ፡ ምንም ፡ ልንገዛ ፡ አንችልም
2. ለጥቂት ፡ ጊዜ. He has to give up all physical activity for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ አካላዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መተው ፡ አለበት

**in a little while** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ
I'll be back in a little while. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ እመለሳለሁ

**(a) short while ago** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት
He was here a short while ago. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እዚህ ፡ ነበረ

**worth (one's) while, make it ~**
1. ዋጋውን ፡ በሚገባ ፡ ከፈለ ፤ ዋጋውን ፡ ከፈለ. If you'll paint my house, I'll make it worth your while. ቤቴን ፡ ቀለም ፡ ብትቀባልኝ ፡ ዋጋህን ፡ በሚገባ ፡ እከፍልሃለሁ
He'll make it worth your while to wait. ብትቆይ ፡ ዋጋህን ፡ ይከፍልሃል
2. ለድካሙ ፡ በሚገባ ፡ ከፈለው. I will do it if he makes it worth my while. ለድካሜ ፡ በሚገባ ፡ ከከፈለኝ ፡ እሠራዋለሁ
[See also 'every, great, once']

**whim** ድንገት ፡ ደራሽ ፡ ፍላጎት
Her whim for African studies won't last long. ስለ ፡ አፍሪካ ፡ ለማጥናት ፡ ያላት ፡ ድንገት ፡ ደራሽ ፡ ፍላጎት ፡ ዘላቂ ፡ አይደለም

**on a whim** በድንገት ፡ ተነሣሥቶ
She went to Ethiopia on a whim. በድንገት ፡ ተነሣሥታ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄደች

**whimper**
1. ተነጫነጨ. The little boy whimpered when he couldn't find his mother. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ እናቱን ፡ ባጣ ፡ ጊዜ ፡ ተነጫነጨ
2. አጉረመረመ. The dog whimpered in fear of the fox. ውሻው ፡ ቀበሮውን ፡ በመፍራት ፡ አጉረመረመ

**whimsical** ጉደኛ
The English are rather whimsical at times. እንግሊዞች ፡ አንዳንዴ ፡ ጉደኞች ፡ ናቸው

**whimsy** ጉደኛነት
Lewis Carrol's whimsy is well known from his stories about Alice. የሉዊስ ፡ ከሮል ፡ ጉደኛነት ፡ ስለ ፡ አሊስ ፡ በጻፋቸው ፡ ተረቶች ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው

**whine** (v.)
1. ተነጫነጨ. The child was whining because his mother refused to give him candy. እናቱ ፡ ከረሜላ ፡ ስለከለከለችው ፡ ልጁ ፡ ይነጫነጭ ፡ ነበር
2. አለቀሰ. The dog whined outside the door. ውሻው ፡ ከመዝጊያው ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ አለቀሰ

**whine** (n.)
1. ቀጭን ፡ ድምፅ. The jet plane makes a high-pitched whine. ጄት ፡ አውሮፕላን ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ ያሰማል
2. መነጫነጭ. The child's whine annoyed me greatly. የልጁ ፡ መነጫነጭ ፡ በጣም ፡ አበሳጨኝ

**whip** (whipped), vt.
1. ገረፈ. He whipped the horse mercilessly. ፈረሱን ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ገረፈው
2. በኀይል ፡ አወዛወዘ. The wind was whipping the branches of the trees. ነፋሱ ፡ የዛፎቹን ፡ ቅርንጫፎች ፡ በኀይል ፡ ያወዛውዝ ፡ ነበር
3. መታ. The cook whipped the eggs. ወጥ ፡ ቤቷ ፡ እንቁላሉን ፡ መታች

**whip** (vi.) ተውለበለበ
The flag whipped in the breeze. ሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ለዘብ ፡ ባለው ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ተውለበለበ

**whip off** በድንገት ፡ አነሣ
He whipped off his hat. ባርኔጣውን ፡ በድንገት ፡ አነሣ

**whip up**
1. ፈጠረ. He tried to whip up enthusiasm for his plan. ስለ ፡ እቅዱ ፡ መሳካት ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ለመፍጠር ፡ ፈለገ
2. አነሣሣ. The speaker whipped up the crowd. ተናጋሪው ፡ ሕዝቡን ፡ አነሣሣው

**whip** (n.) ጅራፍ
The whip is made of leather. ጅራፉ ፡ የተሠራው ፡ ከቆዳ ፡ ነው

**whipping, give a ~** ገረፈ
The mother gave the child a whipping. እናቲቱ ፡ ልጁን ፡ ገረፈችው

**whirl**
1. ተሽከረከረ. The world whirls on its axis. ዓለም ፡ በዘንጓ ፡ ላይ ፡ ትሽከረከራለች

The dancers whirled around the room. ደናሾቹ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተሽከረከሩ
2. (= active) አሽከረከረ. +The leaves whirled in the wind. ነፋሱ ፡ ቅጠሉን ፡ አሽከረከረው
3. (= active) አዞረ. +My head is whirling. ራሴን ፡ ያዞረኛል

**whirl about** (vt.) እያሽከረከረ ፡ ወሰደ
The wind whirled the dead leaves about. ነፋሱ ፡ የረገፉትን ፡ ቅጠሎች ፡ እያሽከረከረ ፡ ወሰዳቸው

**whirl about** (vi.)
*He whirled about and faced me. በፍጥነት ፡ ወደኔ ፡ ዞረ

**whirl around** ተሽከረከረ
He whirled around like a top. እንደ ፡ እንዝርት ፡ ተሽከረከረ

**whirl around to face one** በፍጥነት ፡ ወደሱ ፡ ዞረ
He whirled around to face me when I came in. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ስገባ ፡ በፍጥነት ፡ ወደኔ ፡ ዞረ

**whirlpool** አዙሪት
The swimmer was caught in a whirlpool. ዋናተኛው ፡ ባዙሪት ፡ ተያዘ

**whirlwind** ዐውሎ ፡ ነፋስ
The whirlwind destroyed the village. ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ መንደሩን ፡ አፈረሰው

**whisk** (vt.)
1. በፍጥነት ፡ አነሣ. The servants whisked the dirty dishes from the table. የተበላባቸውን ፡ ሳሕኖች ፡ አሽከሮቹ ፡ በፍጥነት ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አነሡ
2. ጠራረገ. She whisked the crumbs from the table. ፍርፋሪውን ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ጠራረገች

**whisk** (vi.) ጥልቅ ፡ አለ
The mouse whisked into its hole. አይጧ ፡ ጉድጓዷ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ አለች

**whisk away** አባረረ
The horse whisked the flies away with its tail. ፈረሱ ፡ ዝንቦቹን ፡ በጭራው ፡ አባረረ

**whisk off** አጣድፎ ፡ ወሰደ
The police whisked him off to jail. ፖሊሶቹ ፡ አጣድፈው ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ወሰዱት

**whisk** (n.) ብሩሽ
We brushed our coats with a whisk. ኮታችንን ፡ በብሩሽ ፡ ጠረግን
[See also 'fly whisk']

**whisker(s)** ሪዝ
The cat's whisker was pulled out. የድመቷ ፡ ሪዝ ፡ ተነቀለ
He has black whiskers. ጥቁር ፡ ሪዝ ፡ አለው

**whisper** (v.)
1. ሹክ ፡ አለ ። አንሾካሾከ. She whispered it in my ear. በጆሮዬ ፡ ሹክ ፡ አለችኝ
You may whisper in the library, but do not talk out loud. ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ልታንሾካሹኩ ፡ ትችላላችሁ ፡ ግን ፡ ድምፃችሁን ፡ ከፍ ፡ አድርጋችሁ ፡ አትነጋገሩ
2. አፏጨ. The wind whispers in the trees. ነፋሱ ፡ በዛፎቹ ፡ መሀከል ፡ ያፏጫል
3. (= active) አንኰሻኰሸ. +The leaves whispered in the wind. ነፋሱ ፡ ቅጠሎቹን ፡ አንኰሻኰሻቸው

**it is whispered** ጭምጭምታ ፡ ነፈሰ
It is whispered that his business is failing. ንግዱ ፡ እየወደቀ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጭምጭምታ ፡ ይነፍሳል

**whisper** (n.) ሹክሹክታ
A whisper ran through the crowd. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ሹክሹክታ ፡ ተሰፋፋ
We spoke in whispers because it was late. ውድቅት ፡ ስለነበረ ፡ በሹክሹክታ ፡ ተነጋገርን

**whistle** (v.)
1. አፏጨ. Who's whistling outside? ከውጭ ፡ የሚያፏጨው ፡ ማነው ?
We could hear the bullets whistling past us. ጥይቶቹ ፡ እያፏጩ ፡ ባጠገባችን ፡ ሲያልፉ ፡ እንሰማ ፡ ነበር
2. ፊሽካ ፡ ነፋ. The policeman whistled us to stop. ፖሊሱ ፡ እንድንቆም ፡ ፊሽካ ፡ ነፋ

**whistle** (n.)
1. ፊሽካ. He signaled to us with his whistle. በፊሽካው ፡ ምልክት ፡ ሰጠን
2. ድምፅ. We heard the whistle of a steam engine. የከሰል ፡ ባቡር ፡ ድምፅ ፡ ሰማን

**whit** ቅንጣት
There was not one whit of truth in his statement. በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ቅንጣት ፡ እንኳ ፡ እውነት ፡ አልነበረበትም

**white** (n.) ነጭ ፡ ክፍል
The white of the eyes becomes yellow when one has jaundice. አንድ ፡ ሰው ፡ የወፍ ፡ በሽታ ፡ ሲይዘው ፡ የዓይኑ ፡ ነጭ ፡ ክፍል ፡ ቢጫ ፡ ይሆናል

**white of egg** ዞፍ
The white of the egg is used to make glue. ዞፍ ፡ ሙጫ ፡ ለመሥራት ፡ ያገለግላል

**be dressed in white**
He is dressed in white. ነጭ ፡ በነጭ ፡ ለብሶ ፡ ነበር

**wear white** ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለበሰ
The bride wore white. ሙሽራይቱ ፡ ነጭ ፡ ልብ ስ ፡ ለብሳለች

**white** (adj.) ነጭ
She wore a white dress. ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች

**white hair** የሸበተ ፡ ጸጉር
Grandmother has white hair. ሴት ፡ አያታች ን ፡ የሸበተ ፡ ጸጉር ፡ አላት

**white man** ነጭ
The white man settled in South Africa in 1690. በ፲፮፻፹፪ ዓ. ም. ነጮች ፡ ደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ሰፈሩ

**white people** ፈረንጆች
There are many white people in Ethiopia. ብዙ ፡ ፈረንጆች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አሉ

**be white** ነጣ
Since the clothes were thoroughly washed, they were white. ልብሱ ፡ በደንብ ፡ ስለታጠበ ፡ ነጣ

**go white** ገረጣ
Her face went white. ፊቷ ፡ ገረጣ

**turn white**
1. ሸበተ. His hair turned white. ጸጉሩ ፡ ሸበተ
2. ወደ ፡ ነጭነት ፡ ተለወጠ. The green cloth turned white from the sunlight. ከፀሐዩ ፡ ብርሃ ን ፡ የተነሣ ፡ አረንጓዴው ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ነጭነ ት ፡ ተለወጠ

**white-collar employee** የቢሮ ፡ ሠራተኛ
White-collar employees get paid more than laborers. የቢሮ ፡ ሠራተኞች ፡ ከቀን ፡ ሠራተኞ ች ፡ የበለጠ ፡ ይከፈላቸዋል

**whiten** (vt.) አነጣ
Water from the faucet whitens clothes. የቧምቧ ፡ ውኃ ፡ ልብስ ፡ ያነጣል

**whiten** (vi.) ነጣ
Animal bones were whitening in the sun. ከፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ የእንስሳቱ ፡ አጥንቶ ች ፡ ነጥተዋል

**whiteness** ንጣት
Her black hair accentuated the whiteness of her skin. ጥቁር ፡ ጸጉሯ ፡ የቆዳዋን ፡ ንጣት ፡ አጕላው

**white paper** አቋሙን ፡ የሚገልጽ ፡ መግለጫ
The government issued a white paper on the border problem. ስለ ፡ ድንበሩ ፡ ችግር ፡ መንግ ሥቱ ፡ አቋሙን ፡ የሚገልጽ ፡ መግለጫ ፡ አወጣ

**whitewash** (v.)
1. ኖራ ፡ ቀባ. How long will it take you to whitewash the garage? ጋራዡን ፡ ኖራ ፡ ለመቀ ባት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይፈጅብሃል ?
2. ተግባር ፡ ሸፋፈነ. The commission tried to whitewash the corrupt judge. ኮሚሲዮኑ ፡ የብል ሹውን ፡ ዳኛ ፡ ተግባር ፡ ለመሸፋፈን ፡ ሞከረ

**whitewash** (n.) ኖራ
The whitewash is peeling off the walls. ኖራው ፡ ከግድግዳው ፡ ላይ ፡ መቀረፍ ፡ ጀምሯል

**whither** ወዴት
Whither are you going? ወዴት ፡ በመሄድ ፡ ላ ይ ፡ ነህ ?

**whittle** በቢላዋ ፡ ፋቀ
The boy was whittling on a stick. ልጁ ፡ ዱላ ፡ በቢላዋ ፡ ይፍቅ ፡ ነበር

**whittle down** ቀነጣጠበ
They are trying to whittle down our salaries. ደሞዛችንን ፡ ለመቀነጣጠብ ፡ ይሞክራሉ

**whiz** (whizzed), ~ **by** ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ
The car whizzed by in a cloud of dust. መኪናው ፡ በአቧራው ፡ ውስጥ ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ

**who ?** ማን (sg.); እነማን (pl.) ፤ ማን ፡ ማን
The president is coming. Who? ፕሬዚዳንቱ ፡ እ የመጡ ፡ ናቸው ፤ ማን ?
Who was the first man to settle in this wilderness? በዚህ ፡ ጠፍ ፡ በረሃ ፡ መጀመሪያ ፡ ማን ፡ ማ ን ፡ ሰፈረ?
Who are those men? እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ እነማ ን ፡ ናቸው ?
I don't know who he is. ማን ፡ እንደሆነ ፡ አላ ውቅም

**who** (relative) የ + perfect; የም + imperfect
This is the man who rode with me. ይህ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ የተጓዘው ፡ ሰውዬ ፡ ነው
We saw the men who were working in the fields. እርሻው ፡ መካከል ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎ ች ፡ አየን
Who is not for us is against us. እኛን ፡ የማይደ ግፍ ፡ ተቃዋሚያችን ፡ ነው

**whoever ?** ማን + gerundive + ያውቃል
Whoever heard of such a thing? እንዲህ ፡ ያለ ውን ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሰምቶ ፡ ያውቃል ?

**whoever**
1. የ + (perfect). Whoever wants it may have it. የፈለገ ፡ ሊወስደው ፡ ይችላል
2. የ + perfect + ማንም ፡ ሰው ፡ ይሁን. Whoever told you that is lying. የነገረህ ፡ ማንም ፡ ሰ ው ፡ ይሁን ፡ ውሸቱን ፡ ነው
3. የም + imperfect + ማንኛውም ፡ ሰው. Whoever wants the pencil may have it. እርሳሱን ፡ የ ሚፈልግ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል

**whoever it may be** ማንም ፡ ቢሆን
Don't open the door, whoever it may be. ማንም ፡ ቢሆን ፡ በሩን ፡ እንዳትከፍት

**whole** (n.)
1. ሙሉ. Three thirds make a whole. ሦስት ፡ ሢሶ ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ይሆናል
2. ሙሉ ፡ አገር. The fifty separate states form a whole. አምሳዎቹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ግዛቶች ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ አገር ፡ ይሆናሉ

**whole** (adj.)
1. ሙሉ. I waited for a whole hour. አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ጠበቅሁ
I intend to stay a whole week. አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ለመቆየት ፡ አስቤያለሁ
2. (= adv.) በሙሉ. Can you eat a whole fish? አንድ ፡ ዓሣ ፡ በሙሉ ፡ ለመብላት ፡ ትችላለህ ?
I didn't see him the whole evening. ምሽቱን ፡ በሙሉ ፡ አላየሁትም
The whole village came to receive him. መንደሩ ፡ በሙሉ ፡ እሱን ፡ ለመቀበል ፡ መጣ
3. ደኅና. There isn't a whole plate in the house. ደኅና ፡ ሳሕን ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም
4. (= adv.) እንዳለ. Put whole carrots in the stew! ካሮቱን ፡ እንዳለ ፡ ወጡ ፡ ውስጥ ፡ ጨምሬው
5. (= adv.) እንዳለ ፡ ባንዴ. Snakes swallow their prey whole. እባብ ፡ የያዘውን ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ባንዴ ፡ ይውጣል
*Not one dish was left whole when the shelf broke. መደርደሪያው ፡ በተሰበረ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሳሕን ፡ እንኳን ፡ አልቀረም

**be whole** አልተሰበረም
The cup fell, but it's still whole. ሲኒው ፡ ቢወድቅም ፡ አልተሰበረም

**on the whole** በጠቅላላው
On the whole, I agree with you. በጠቅላላው ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**taken as a whole** በጠቅላላው ፡ ሲታይ
Taken as a whole, the problem is unsolvable. በጠቅላላው ፡ ሲታይ ፡ ለነገሩ ፡ መፍትሔ ፡ ማግኘት ፡ አይቻልም

**the whole of** በሙሉ
The whole of my money was stolen. ገንዘቤ ፡ በሙሉ ፡ ተሰረቀብኝ
[See also 'lot']

**wholehearted** ከልብ ፡ የመነጨ
The soldiers were given a wholehearted welcome. ወታደሮቹ ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ አቀባበል ፡ ተደረገላቸው

**wholeheartedly** በሙሉ ፡ ልብ
He did it wholeheartedly. በሙሉ ፡ ልብ ፡ ሠራው

**wholesale** (adj.)
1. በጅምላ ፡ የሚሸጡበት. He has a good position with a wholesale house. በጅምላ ፡ የሚሸጡበት ፡ መደብር ፡ ጥሩ ፡ ሥራ ፡ አለው
2. (= adv.) በጅምላ. What's the wholesale price? ዋጋው ፡ በጅምላ ፡ስንት ፡ ነው ?
3. እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ. Wholesale destruction was caused by the fire bombs. የእሳት ፡ ቦምቡ ፡ ፈንድቶ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ አደረሰ

**wholesale** (adv.) በጅምላ
They sell only wholesale. የሚሸጡት ፡ በጅምላ ፡ ብቻ ፡ ነው

**wholesome**
1. ለጤና ፡ የሚስማማ. This region has a wholesome climate. ይህ ፡ ቀበሌ ፡ ለጤና ፡ የሚስማማ ፡ ያየር ፡ ንብረት ፡ አለው
2. ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያልጐደለው. She reads only wholesome books. ግብረ ፡ ገብነት ፡ ያልጐደላቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ ታነባለች
*She has a wholesome face. መልኳ ፡ ጤናዋ ፡ የተሟላ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል

**be wholesome** ለሰውነት ፡ ጥሩ ፡ ነው
This food is wholesome, so eat it! ይህ ፡ ምግብ ፡ ለሰውነት ፡ ጥሩ ፡ ስለሆነ ፡ ብላ

**wholly**
1. ሙሉ ፡ በሙሉ. I wholly agree with you. ካንተ ፡ ጋር ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እስማማለሁ
2. እስከነአካቴው. Few men are wholly bad. እስከነአካቴው ፡ መጥፎ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ናቸው

**whom ?** ማንን
Whom do you want? ማንን ፡ ትፈልጋለህ ?

**whom,** expressed by a relative clause
The man whom you see there is my teacher. ያ ፡ የምታየው ፡ ሰውዬ ፡ መምህሬ ፡ ነው

**to whom ?** ለማን
To whom did you give it? ለማን ፡ ሰጠኸው ?

**to whom,** expressed by a relative clause
The boy to whom I spoke is my cousin. ያነጋገርኩት ፡ ልጅ ፡ የአጐቴ ፡ (የአክስቴ) ፡ ልጅ ፡ ነው

**whoop** ጩኸት
When he sighted land, the sailor let out a whoop of joy. የብስ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ መርከበኛው ፡ የደስታ ፡ ጩኸት ፡ ለቀቀ

**whooping cough** ትክትክ
Children have whooping cough quite often. ልጆች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትክትክ ፡ ይይዛቸዋል

**whore** ሴተኛ ፡ አዳሪ
It is forbidden for whores to be near schools. ሴተኛ ፡ አዳሪዎች ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ አካባቢ ፡ እንዳይገኙ ፡ ተከልክለዋል

**whose ?** የማን
Whose watch is this? ይህ ፡ የማን ፡ ሰዓት ፡ ነው ?
Tell me whose is best. የማን ፡ እንደሚበልጥ ፡ ንገረኝ

**whose** (relative clause)
The house whose windows are broken is for sale. መስኮቱ ፡ የተሰበረው ፡ ቤት ፡ የሚሸጥ ፡ ነው

**whosoever,** expressed by a relative clause
Whosoever seeks shall find. የሚፈልግ ፡ ያገኛል

**why ?**
1. ለምን. You said I should do it. Why? መሥራት ፡ አለብህ ፡ ትለኛለህ ፤ ለምን ?
Why was he late? ለምን ፡ ዘገየ ?
2. ለምን ፡ እንደ + (verb). Do you know why he was late? ለምን ፡ እንደዘገየ ፡ ታውቃለህ ?
There are good reasons why he left. ለምን ፡ እንደሄደ ፡ ጥሩ ፡ ምክንያት ፡ አለው
The reason why he did it is not known. ለምን ፡ ይህን ፡ እንዳደረገ ፡ ምክንያቱ ፡ አልታወቀም

**why !** እንዴ
Why, it's quite easy! እንዴ! ይህማ ፡ ቀላል ፡ ነው

**why not ?**
Why not go tomorrow ? ምን ፡ አለበት ፤ ነገ ፡ ብንሄድ ?

**why ! why !** ኧረግ
Why! Why! The cage is empty! ኧረግ! ወጥመዱ ፡ ባዶ ፡ ነው

**that's why** ስለዚህ
That's why I didn't call you. ስለዚህ ፡ ነው ፡ ያልጠራሁህ

**wick** ክር
Turn up the wick of the oil lamp! የፋኖሱን ፡ ክር ፡ ወጣ ፡ አድርገው
Don't pull the wick from the candle! የሻማውን ፡ ክር ፡ አትምዘዘው

**wicked**
1. ክፉ. He is a wicked man. እሱ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ነው
A wicked blow on the head rendered him unconscious. ራሱ ፡ ላይ ፡ የተመታው ፡ ክፉ ፡ ምት ፡ ሕይወቱን ፡ አሳተው
2. ግፍ. Tormenting that poor cat is wicked. ያቺን ፡ ምስኪን ፡ ድመት ፡ ማሠቃየት ፡ ግፍ ፡ ነው
3. የጭካኔ. The wicked deeds of Herod are still remembered. የሄሮድስ ፡ የጭካኔ ፡ ተግባሮች ፡ አሁንም ፡ ይታወሳሉ
4. እርጉም. The wicked witch gave the child a baleful glance. እርጉሟ ፡ አስማተኛ ፡ ልጁን ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተችው

**wickedness** ክፋት
His wickedness brought the condemnation of the world upon him. ክፋቱ ፡ የመላውን ፡ ዓለም ፡ ውግዘት ፡ አወረደበት

**wicker** ቀርቃኻ
The basket for storing corn is made of wicker. የበቆሎ ፡ ማከማቻው ፡ ቅርጫት ፡ የተሠራው ፡ ከቀርቃኻ ፡ ነው

**wickerwork** ስፌት
She is skilled in wickerwork. በስፌት ፡ የታወቀች ፡ ናት

**wide**
1. ሰፊ. This road is very wide. ይህ ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ ሰፊ ፡ ነው
A trip around the world gives wide experience. ዓለምን ፡ መዞር ፡ ሰፊ ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጣል
2. (= noun) ስፋት. The window is five feet wide. የመስኮቱ ፡ ስፋት ፡ አምስት ፡ ጫማ ፡ ነው
Is the coat wide enough for you? የኮቱ ፡ ስፋት ፡ በቂህ ፡ ነው ?
3. የራቀ. The shot was wide of the mark. ተኩሱ ፡ ከዒላማው ፡ የራቀ ፡ ነበር

**wide selection** ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት
We have a wide selection of shoes. ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ጫማዎች ፡ አሉን

**with wide eyes** ዓይኑን ፡ አፍጥጦ
The child stared with wide eyes. ልጁ ፡ ዓይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ተመለከተ
[See also 'distribution, far, open, variety']

**wide-awake** ንቁ
He is a wide-awake boy with many interests. ብዙ ፡ ምኞት ፡ ያለው ፡ ንቁ ፡ ልጅ ፡ ነው

**be wide-awake** በፍጹም ፡ ነቃ
I was wide-awake when the sun rose. ፀሐይ ፡ ስትወጣ ፡ በፍጹም ፡ ነቅቼ ፡ ነበር

**widely**
1. በጣም. They differ widely in opinions. በአስተያየት ፡ በጣም ፡ ይለያያሉ
2. በሰፊው. His merits have been widely recognized. መልካም ፡ ሥራው ፡ በሰፊው ፡ ታውቆለታል

**widen** (vt.) አሰፋ
They're going to widen the street. መንገዱን ፡ ሊያሰፉት ፡ ነው
Reading widens our horizons. ማንበብ ፡ ዕውቀታችንን ፡ ያሰፋዋል

**widen** (vi.) ሰፋ
The river will widen next rainy season. በሚመጣው ፡ ክረምት ፡ ወንዙ ፡ ይሰፋል

**wider** ሰፋ ፡ ያለ
Leave a wider margin on the left side! በግራ ፡ በኩል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ኅዳግ ፡ ተው

**widespread**
1. ሰፊ. The invention found widespread acceptance. አዲስ ፡ የተፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ሰፊ ፡ ተቀባይነት ፡ አገኘ
2. ሰፋ ፡ ያለ. There is widespread damage from the forest fire. ከጫካው ፡ ቃጠሎ ፡ የተነሣ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ ደርሷል
3. በሰፊው ፡ የተለመደ. Adoration of the Virgin Mary is widespread in Ethiopia. ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ማክበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ የተለመደ ፡ ነው
4. የተዛመተ. It is a widespread belief that black cats bring bad luck. ጥቁር ፡ ድመቶች ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ያመጣሉ ፡ የሚል ፡ የተዛመተ ፡ እምነት ፡ አለ
*The bird's widespread wings are a sign it will attack. የወፏ ፡ ክንፍ ፡ በጣም ፡ መዘርጋቱ ፡ የምታጠቃ ፡ መሆኗን ፡ ያመለክታል

**be widespread**
1. በብዛት ፡ ተገኘ. Sorghum is widespread in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ማሽላ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል
2. ተሰራጨ. How widespread is this view? ይህ ፡ አስተያየት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተሰራጭቷል ?
3. በሰፊው ፡ አለ. Discrimination is widespread in South Africa. ደቡብ ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ የቀለም ፡ ልዩነት ፡ በሰፊው ፡ አለ
4. ተስፋፋ. The cult of Apollo was widespread. የአፖሎ ፡ አምልኮ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር

**widow** ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴት
The widow has six children. ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴትዮ ፡ ስድስት ፡ ልጆች ፡ አሏት

**widower** ሚስቱ ፡ የሞተችበት ፡ ሰው
A widower needs a housekeeper. ሚስቱ ፡ የሞተችበት ፡ ሰው ፡ ቀላቢት ፡ ያስፈልገዋል

**width**
1. ስፋት. The width of this room is twelve feet. የዚህ ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ ነው
The room is nine feet in width. የክፍሉ ፡ ስፋት ፡ አራት ፡ ጫማ ፡ ነው
2. ይህን ፡ ያህል ፡ የሚሰፋ. I need two widths of this material. ከዚህ ፡ ጨርቅ ፡ ሁለት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚሰፋ ፡ እፈልጋለሁ

**wield** ተጠቀመ(በት)
The soldiers wield the sword with great skill. ወታደሮቹ ፡ ጐራዴያቸውን ፡ በረቀቀ ፡ ዘዴ ፡ ይጠቀሙበታል
He wields a great amount of power. ሥልጣኑን ፡ በኀይል ፡ ይጠቀምበታል

**wife** (wives)
1. ሚስት. The wife is in charge of the house. ሚስት ፡ የቤት ፡ ኀላፊ ፡ ናት
2. ባለቤት. My wife is in the hospital. ባለቤቴ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ነች
*He made her his wife. አገባት

**take a wife** ሚስት ፡ አገባ
Why don't you take a wife? ለምን ፡ ሚስት ፡ አታገባም ?

**wig** ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጸጉር
Women like to wear wigs now. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጸጉር ፡ ማድረግ ፡ ይወዳሉ

**wiggle**
1. ተጥመለመለ. The worm wiggles on the hook. ትሉ ፡ በመንጠቆው ፡ ላይ ፡ ይጥመለመላል
2. ተቍነጠነጠ. The child wiggles in his chair. ሕፃኑ ፡ ወምበሩ ፡ ላይ ፡ ይቍነጠነጣል

**wild**
1. ባለጌ. The children are too wild. ልጆቹ ፡ በጣም ፡ ባለጌዎች ፡ ናቸው
2. አረመኔ. He is reading about the wild tribes of ancient times. ስለ ፡ ጥንት ፡ አረመኔ ፡ ጐሳዎች ፡ እያነበበ ፡ ነው
3. የጫካ. The wild men's genitals were covered by a cloth strip. የጫካ ፡ ሰዎቹ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ በጨርቅ ፡ ቁራጭ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር
4. ወፍ ፡ ዘራሽ. The wild flowers blossom at the end of the rainy season. ወፍ ፡ ዘራሽ ፡ አበቦች ፡ ክረምት ፡ ሲወጣ ፡ ያብባሉ
5. ሰው ፡ ያልሰፈረበት. Wild land affords refuge for game. ሰው ፡ ያልሰፈረበት ፡ መሬት ፡ ላውሬዎች ፡ መጠጊያ ፡ ይሆናል
6. ያልተገራ. Your children are too wild; they scratched my furniture while playing. ልጆችህ ፡ ያልተገሩ ፡ ናቸው ፤ ሲጫወቱ ፡ የቤት ፡ እቃዬን ፡ አበላሹብኝ

7. የሚዳ ፤ ያልተገራ. There are many wild horses in this region. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ብዙ ፡ የሚዳ ፡ ፈረሶች ፡ አሉ
We loosed the wild horse. ያልተገራውን ፡ ፈረስ ፡ ለቀቅነው
8. የማይጨበጥ. He has a wild plan for getting rich. ሀብታም ፡ ለመሆን ፡ የማይጨበጥ ፡ እቅድ ፡ አለው
9. ከእውነት ፡ የራቀ. He made so many wild allegations that no one will believe him. ብዙ ፡ ከእውነት ፡ የራቁ ፡ ነገሮች ፡ ደረሱ ፡ ስለሚ ል ፡ ማንም ፡ አያምነውም
10. ታላቅ. The audience received the speech with wild applause. አዳማጮቹ ፡ ለንግግሩ ፡ ታ ላቅ ፡ ጭብጨባ ፡ አደረጉ

**wilds** ዱር
They have a farm way out in the wilds. ራቅ ፡ ብለው ፡ ከዱር ፡ ውስጥ ፡ እርሻ ፡ አላቸው

**wild region** በረሃ
Airplanes now fly over the wild regions of the Far North. ራቅ ፡ ብለው ፡ ሰሜን ፡ በሚገኙ ት ፡ በረሃዎች ፡ ላይ ፡ አሁን ፡ አውሮፕላኖች ፡ ይበራሉ

**wild state** አውሬነት
Many tamed animals revert to a wild state when set free. ብዙ ፡ ለማዳ ፡ እንስሳዎች ፡ በተለ ቀቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አውሬነት ፡ ይመለሳሉ

**be wild about** ነፍሱ ፡ እስኪወጣ ፡ ወደደ
My boy is wild about ice cream. ልጄ ፡ አይስክ ሬም ፡ ነፍሱ ፡ እስኪወጣ ፡ ይወዳል

**make a wild guess** ዓይኑን ፡ ጨፍኖ ፡ ገመተ
I'll make a wild guess: your car cost $2,500. ዓይኔን ፡ ጨፍኜ ፡ ልገምት ፤ መኪናህ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ታወጣለች

**run wild** አውሬ ፡ ሆነ
The dog ran wild after its master died. ጌታው ፡ ከሞተበት ፡ በኋላ ፡ ውሻው ፡ አውሬ ፡ ሆነ

**(allow to) run wild** ስድ ፡ ለቀቀ
They allow their children to run wild. ልጆቻቸ ውን ፡ ስድ ፡ ይለቋቸዋል
[See also 'animal, beast']

## wilderness
1. በረሃ ፤ ጠፍ ፡ በረሃ. The only settlement in the wilderness was a penal colony. በበረሃ ው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ መኖሪያ ፡ የወንጀለኞ ች ፡ ብቻ ፡ ነበር
Who was the first man to settle in this wilderness? በዚህ ፡ ጠፍ ፡ በረሃ ፡ መጀመሪያ ፡ ማን ፡ ማ ን ፡ ሰፈረ ?
2. ጫካ. The boy scouts cleared a path through the wilderness. እስካውቶቹ ፡ ጫካውን ፡ መን ጥረው ፡ መንገድ ፡ አበጁ

## wildfire ሰደድ ፡ እሳት
The wildfire destroyed many trees before it was put out. ሰደድ ፡ እሳቱ ፡ ከመጥፋቱ ፡ በፊ ት ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ አወደመ
The news spread like wildfire. ወሬው ፡ እንደ ፡ ሰደድ ፡ እሳት ፡ ተሰራጨ

## wildlife የዱር ፡ አራዊት
There is abundant wildlife in these forests. በዚህ ፡ ደን ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ አሉ

## wile ብልሃት
The witch by her wiles persuaded the boy to go with her. አስማተኛዋ ፡ በብልሀቷ ፡ አግባብ ታ ፡ ልጁ ፡ ከሷ ፡ ጋር ፡ እንዲሄድ ፡ አደረገችው

## will (v.)
1. ተናዘዘ. He willed all his property to the city. ያለውን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ለከተማው ፡ ተናዘዘ
2. ቈረጠ. She willed to keep awake. ነቅታ ፡ ለ መቆየት ፡ ቈረጠች
*Fate has willed it otherwise. ዕድል ፡ አይሁን ፡ ብሎታል

**will (vi.)** ተመኘ
We cannot always do as we will. ሁልጊዜ ፡ እ ንደምንመኘው ፡ አናደርግም

## will (auxiliary)
1. (imperfect). I will come when I am ready. ሲመቸኝ ፡ እመጣለሁ
2. (simple imperfect). Will you open the door? መዝጊያውን ፡ ትከፍት ?
3. አለ(በት). You will do it at once! አሁኑኑ ፡ መ ፈጸም ፡ አለብህ
4. ቻለ. This jar will hold three liters. ይህ ፡ ማሰ ሮ ፡ ሦስት ፡ ሊትሮ ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል

**will have** ፈለገ
Ask him if he will have some cake. ጥቂት ፡ ኬ ክ ፡ ይፈልግ ፡ እንደሆነ ፡ ጠይቀው

## will (n.)
1. ኑዛዜ. They read his will and found that he had disinherited everybody. ኑዛዜውን ፡ ካነበቡ ፡ በኋላ ፡ ለቤተሰቦቹ ፡ ምንም ፡ አለማውረሱን ፡ ተረዱ
2. ፍላጎት. If the patient has a will to live, he will recover. በሽተኛው ፡ የመኖር ፡ ፍላጎት ፡ ካለው ፡ ይድናል
3. መንፈስ. He has no will of his own; his wife makes all the decisions. በራሱ ፡ መንፈስ ፡ አ ይመራም ፤ የምታዘው ፡ ሚስቱ ፡ ናት

4. ሙሉ ፡ ልብ. He went at his work with a will. ሥራውን ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ ጀመረ
5. ፈቃድ. Thy will be done. ፈቃድህ ፡ ይፈጸም
I did it of my own free will. ያደረግሁት ፡ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ ነው
6. ፈቃደኛነት. I will include an extra payment to show good will. በጎ ፡ ፈቃደኛነቴን ፡ ለማሳየት ፡ ትርፍ ፡ እከፍላለሁ
7. ውዴታ. He was named chairman against his will. ያለ ፡ ውዴታው ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ተመረጠ
8. ስሜት. A friendly smile generates good will. የወዳጅነት ፡ ፈገግታ ፡ መልካም ፡ ስሜትን ፡ ያተርፋል
*Where there's a will, there's a way. ቁራጥና ፡ ጨኪስ ፡ መውጫ ፡ አያጣም

**at will** እንደልቡ ፤ በፈቃዱ
They come and go at will. እንደልባቸው ፡ (በፈቃዳቸው) ፡ ይመላለሳሉ

**good will** ጥሩ; **ill will** መጥፎ
Most men feel good will toward their friends and ill will toward their enemies. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለወዳጆቻቸው ፡ ጥሩ ፤ ለጠላቶቻቸው ፡ ደግሞ ፡ መጥፎ ፡ ይመኛሉ

**leave a will** ተናዘዘ
He died without leaving a will. ሳይናዘዝ ፡ ሞተ
[See also 'force, free']

## willful
1. ሐሳበ ፡ ግትር. She is very willful, and so it's hard to control her. ሐሳበ ፡ ግትር ፡ ስለሆነች ፡ እሷን ፡ መቈጣጠር ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. ችኮ. The willful boy will not obey. ችኮው ፡ ልጅ ፡ አይታዘዝም
3. (= adv.) ሆን ፡ ብሎ. His willful lies only create more dissension. ሆን ፡ ብሎ ፡ የሚዋሸው ፡ የበለጠ ፡ ቅሬታ ፡ ያስከትላል

## willing ፍቃደኛ ፤ ፈቃደኛ
I'm willing to try anything. ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ለመሞከር ፡ ፍቃደኛ ፡ (ፈቃደኛ) ፡ ነኝ
[See also 'perfectly']

## willingly
1. በፍቃድ. She came willingly, so why is she complaining to us now? በፍቃዷ ፡ ነው ፡ የመጣችው ፤ አሁን ፡ ምን ፡ ትነጫነጭብኛለች ?
2. በፈቃደኝነት. He did not impose his advice on me, but I listened to him willingly. ምክሩን ፡ እንድቀበል ፡ አላስገደደኝም ፤ ግን ፡ በፈቃደኝነት ፡ አዳመጥኩት

## willingness
*He sounded them out regarding their willingness to come along. ለመምጣት ፡ ይፈልጉ ፡ እንደሆነ ፡ አሳባቸውን ፡ ለማወቅ ፡ ጠየቀ

## will power ቁራጥነት
It takes will power to give up smoking. ሲጋራ ፡ ማጤስን ፡ መተው ፡ ቁራጥነትን ፡ ይጠይቃል

## willy-nilly በውድም ፡ ሆነ ፡ በግድ
Willy-nilly he will pay what he owes. በውድም ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ ያለበትን ፡ ይከፍላል

## wilt
1. ጠወለገ. The flowers will wilt if they are not in water. አበቦቹ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ካልሆኑ ፡ ይጠወልጋሉ
2. ጉልበቱ ፡ ፈሰሰ. We wilted under the tropical sun. ሐሩሩ ፡ ፀሐይ ፡ ውስጥ ፡ ጉልበታችን ፡ ፈሰሰ

## win (won)
1. አሸነፈ. We won the battle. ጦርነቱን ፡ አሸነፍን
Which team do you think will win? የትኛው ፡ ቡድን ፡ የሚያሸንፍ ፡ ይመስልሃል ?
2. ረታ. He won his case in court. ሙግቱን ፡ ረታ
3. አገኘ. Win a prize by making the highest score! ከፍተኛውን ፡ ነጥብ ፡ በማግኘት ፡ ሽልማት ፡ አግኝ
4. ወጣ(ለት). We are in luck; our chance in the lottery won. ታድለናል ፤ የሎተሪ ፡ ዕጣ ፡ ወጣልን
5. አፈራ. She won new friends. አዲስ ፡ ጓደኞች ፡ አፈራች
6. አተረፈ. He won renown as a courageous fighter. ጀግና ፡ ተዋጊ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ዝና ፡ አተረፈ
7. ማረከ. The speaker soon won his audience. ተናጋሪው ፡ ወዲያውኑ ፡ አድማጮቹን ፡ ማረከ
8. ደረሰ. The climbers won the top of the hill. ተራራ ፡ ወጪዎቹ ፡ ኮረብታው ፡ ጫፍ ፡ ደረሱ

**win (one's) heart** ልብ ፡ ማረከ
His childlike frankness wins the heart of everybody. እንደ ፡ ሕፃን ፡ የዋህ ፡ መሆኑ ፡ የማንኛቸውንም ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ ይማርካል

**win (someone over) to one's side** ወደሱ ፡ ሳበው ፤ አግባባ
The power of his argument won many to his side. የክርክሩ ፡ ብርቱነት ፡ ብዙዎቹን ፡ ወደሱ ፡ ሳባቸው
I have won him over to our side. በኛ ፡ በኩል ፡ እንዲሆን ፡ አግባብቼዋለሁ
[See also 'favor, recognition, respect, success, title']

**wince** ተሸመቀቀ
I winced when he hit my hand. እጄን ፡ ሲመታኝ ፡ ተሸመቀቅሁ

**wind** (wound), vt.
1. ጠመጠመ. Wind it around my finger! ጣቴ ፡ ላይ ፡ ጠምጥመው
2. አጠነጠነ. She wound the thread on the spindle. ክሩን ፡ እንዝርቱ ፡ ላይ ፡ አጠነጠነች
3. ሞላ. I forgot to wind my watch. ሰዓቴን ፡ መሙላት ፡ ረሳሁ
*She winds him around her little finger. እጇ ፡ ውስጥ ፡ ነው

**wind** (vi.)
1. ተጠማዞ ፡ አለፈ. The road winds through the mountains. መንገዱ ፡ በተራሮቹ ፡ መሃል ፡ ተጠማዞ ፡ ያልፋል
2. ተጠማዘዘ. A lazy stream winds through the meadow. ዝግተኛው ፡ ምንጭ ፡ ሜዳው ፡ ላይ ፡ ይጠማዘዛል

**wind on the spool** አዳወረ
Wind the thread on a spool! ክሩን ፡ አዳውረው

**wind up** (vt.)
1. አጠነጠነ. Will you help me wind up this yarn? ይህን ፡ የሱፍ ፡ ክር ፡ እንዳጠነጥን ፡ አግዘኝ
2. ደመደመ. He wound up his speech with an appeal to everyone's patriotism. የሁሉንም ፡ የሀገር ፡ ፍቅር ፡ ስሜት ፡ በመቀስቀስ ፡ ንግግሩን ፡ ደመደመ
3. አጠናቀቀ. They gave him two weeks' time in which to wind up his affairs. ጉዳዩን ፡ የሚያጠናቅቅበት ፡ የሁለት ፡ ሳምንት ፡ ጊዜ ፡ ሰጡት

**wind up** (vi.) አበቃ
The meeting will wind up before dark. ስብሰባው ፡ ከመምሸቱ ፡ በፊት ፡ ያበቃል
*My plan wound up in the wastepaper basket. እቅዴ ፡ መጨረሻው ፡ ከንቱ ፡ ሆነ

**(be) wound up** ጭንቅ ፡ አለው
He is so wound up, he can't relax or stop talking. ጭንቅ ፡ ስላለው ፡ ሊዝናና ፡ ወይም ፡ ዝም ፡ ሊል ፡ አልቻለም

**wind (one's) way through** እየተጠማዘዘ ፡ ሄደ
We wound our way through the narrow streets. በጠባቦቹ ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፡ እየተጠማዘዝን ፡ ሄድን

**wind (its) way to** እየተጥመዘመዘ ፡ ከ - - - ገባ
The river winds its way to the sea. ወንዙ ፡ እየተጥመዘመዘ ፡ ከባሕር ፡ ይገባል

**wind, be winded** ትንፋሹ ፡ ተቈረጠ ፤ ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ
The fat man was winded by walking up the steep hill. ቀጥ ፡ ያለውን ፡ ኮረብታ ፡ በመውጣቱ ፡ ወፍራሙ ፡ ሰው ፡ ትንፋሹ ፡ ተቈረጠ ፡ (ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ)

**wind** (n.)
1. ነፋስ. There was a violent wind last night. ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ነበር
2. ትንፋሽ. He regained his wind after a short rest. ጥቂት ፡ ካረፈ ፡ በኋላ ፡ ትንፋሹ ፡ መለስ ፡ አለ

**(the) wind blows** ነፈሰ
How the wind is blowing today! ዛሬ ፡ ምንኛ ፡ ይነፍሳል!
*We won't act until we see how the wind blows. ሁኔታው ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ሳናውቅ ፡ ምንም ፡ አናደርግም

**break wind** ፈሳ
Don't break wind in public! በሰው ፡ መሃል ፡ አትፍሳ

**get wind of**
1. ዐወቀ. Don't let mother get wind of our plans to give her a gift! ስጦታ ፡ ልናበረክትላት ፡ ያለንን ፡ እቅድ ፡ እናታችን ፡ እንድታውቅ ፡ አታድርግ
2. ጭምጭምታ ፡ ሰማ. I got wind of the cabinet reshuffle yesterday. የሚኒስትሮች ፡ መለዋወጥ ፡ ይደረጋል ፡ የሚል ፡ ጭምጭምታ ፡ ትናንት ፡ ሰማሁ

**in the wind**
*There is something in the wind. አንድ ፡ ነገር ፡ ሊሆን ፡ ነው
[See also 'second']

**windbreak** ከነፋስ ፡ መከላከያ
The boys pitched their tent next to the stone wall, so that it would serve as a windbreak. ከነፋስ ፡ መከላከያ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ልጆቹ ፡ ድንኳናቸውን ፡ ድንጋይ ፡ ግድግዳ ፡ ሥር ፡ ተከሉ

**windfall**
*He received a windfall of $200,000. እግዜር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ጣለለት

**winding** ጠምዛዛ
High speed on a winding road is dangerous. በጠምዛዛ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ መንዳት ፡ አደገኛ ፡ ነው

**wind instrument** [በነፋስ ፡ የሚሠራ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**windmill** የነፋስ ፡ ወፍጮ
Windmills are animated by the wind. የነፋስ ፡ ወፍጮዎች ፡ የሚንቀሳቀሱት ፡ በነፋስ ፡ ኀይል ፡ ነው

**window** መስኮት
This room has two windows. ይህ ፡ ክፍል ፡ ሁለት ፡ መስኮት ፡ አለው
[See also 'sill']

**windowpane** የመስኮት ፡ መስታወት
The windowpane was cracked. የመስኮቱ ፡ መስታወት ፡ ተሰንጥቋል

**windowshopping, go ~**
She likes to go windowshopping. ባትገዛም ፡ እቃዎቹን ፡ መመልከት ፡ ትወዳለች

**windpipe** [ከአፍ ፡ ወደ ፡ ሳምባ ፡ የነፋስ ፡ መተላለፊያ]

**windshield** የመኪና ፡ የፊት ፡ መስታወት
The windshield is tinted green. የመኪናው ፡ የፊት ፡ መስታወት ፡ ትንሽ ፡ አረንጓዴነት ፡ አለው

**windshield wiper** የመኪና ፡ የዝናብ ፡ መጥረጊያ
The windshield wiper does not work. የመኪናው ፡ የዝናብ ፡ መጥረጊያ ፡ ተበላሽቷል

**windstorm** ኀይለኛ ፡ ነፋስ
The windstorm destroyed the roof. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ጣራውን ፡ አፈረሰው

**wind vane** [የነፋስን ፡ አቅጣጫ ፡ የሚያሳይ ፡ መጠቆሚያ]

**windy**
1. ነፋሻ. It was very windy yesterday. ትላንትና ፡ በጣም ፡ ነፋሻ ፡ ነበር
2. ነፋስ ፡ የሚበዛበት. March is a windy month. መጋቢት ፡ ነፋስ ፡ የሚበዛበት ፡ ወር ፡ ነው
3. ገለባ. His windy talk impresses no one. ገለባ ፡ ንግግሩ ፡ ለማንም ፡ ስሜት ፡ አይሰጥም

**wine** ወይን ፡ ጠጅ
I like to drink wine. ወይን ፡ ጠጅ ፡ መጠጣት ፡ እወዳለሁ

**wing** (v.)
1. ወረወረ. The soldier winged his arrow at the target. ወታደሩ ፡ ቀስቱን ፡ ወደ ፡ ዒላማው ፡ ወረወረ
2. ጨረፍ ፡ አድርጎት ፡ አለፈ. He is not badly hurt; the bullet only winged him. በጣም ፡ አልተጐዳም ፤ ጥይቱ ፡ ጨረፍ ፡ አድርጎት ፡ ነው ፡ ያለፈው

**wing (one's) way** በረረ
The bird winged its way to the south. ወፏ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በረረች

**wing** (n.) ክንፍ
The pigeon broke its wing. የእርግቧ ፡ ክንፍ ፡ ተሰበረ
The office is in the west wing of the building. ቢሮው ፡ ሕንጻው ፡ ውስጥ ፡ በስተምዕራብ ፡ ከሚገኘው ፡ ክንፍ ፡ ነው

**on the wing** ሲበር
It's hard to shoot a bird on the wing. ወፍ ፡ ስትበር ፡ ተኩሶ ፡ ለመግደል ፡ ያስቸግራል

**take under one's wing** ተንከባከበ
The teacher took the new student under his wing. አስተማሪው ፡ አዲሱን ፡ ተማሪ ፡ ተንከባከበው

**take wing** በረረ
The birds took wing at our approach. ስንጠጋቸው ፡ ወፎቹ ፡ በረሩ

**wink** (vt.) ጠቀሰ
He winked his eye to indicate he was not serious. ሲቀልድ ፡ መሆኑን ፡ ለማመልከት ፡ በዓይኑ ፡ ጠቀሰ

**wink** (vi.)
1. ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ አለ. We could see the lights of the city winking in the distance. የከተማው ፡ መብራት ፡ ከሩቁ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ሲል ፡ ይታየናል
2. ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አለ. The lights of a passing ship winked. የሚያልፈው ፡ መርከብ ፡ መብራት ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አለ
The stars winked. ኮከቦቹ ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ አሉ
3. በዓይኑ ፡ ጠቀስ ፡ አደረገ. She winked as she passed. ስታልፍ ፡ በዓይኗ ፡ ጠቀስ ፡ አደረገች

**wink at it** አይቶ ፡ እንዳላየ ፡ ሆነ
Mother knows that we help ourselves to cookies now and then, but she winks at it. እናታችን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብስኩቱን ፡ እንደምንበላ ፡ ታውቃለች ፡ ግን ፡ አይታ ፡ እንዳላየች ፡ ትሆናለች

**wink** (n.) ጥቅሻ
She gave me a knowing wink. ያልኩት ፡ የገባት ፡ መሆኗን ፡ በጥቅሻ ፡ ገለጸችልኝ
*I didn't sleep a wink last night. ትናንትና ፡ ማታ ፡ ባይኔ ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይዞር ፡ አደርኩ

**in a wink** ባንድ ፡ አፍታ
I'll be there in a wink. ባንድ ፡ አፍታ እዚያ ፡ እገኛለሁ

**winner** አሸናፊ
The winner will get a gold cup. አሸናፊው ፡ የወርቅ ፡ ዋንጫ ፡ ያገኛል

**winning**
1. አሸናፊ. The winning team is given a large silver cup. ላሸናፊው ፡ ቡድን ፡ ትልቅ ፡ የብር ፡ ዋንጫ ፡ ተሰጠ
2. የሚማርክ. She has a winning smile. የሚማርክ ፡ ፈገግታ ፡ አላት

**winnow**
1. አዘራ. The farmers winnow the grain after they thresh it. ገበሬዎቹ ፡ እህሉን ፡ ከወቁ ፡ በኋላ ፡ ያዘሩታል
2. ለየ. You have to winnow truth from his statement. ከሰጠው ፡ አስተያየት ፡ እውነቱን ፡ መለየት ፡ አለብህ

**winsome** ቆንጆ
She is rather winsome, don't you think? ቆንጆ ፡ ነች ፡ አይመስልህም ?

**winter** ክረምት
The European and the Ethiopian winters are not the same. የፈረንጅና ፡ ያበሻ ፡ ክረምት ፡ አንድ ፡ አይደለም

**wipe**
1. ወለወለ. I'll wash the dishes if you wipe them. አንተ ፡ ሳሕኖቹን ፡ ከወለወልካቸው ፡ እኔ ፡ አጥባቸዋለሁ
Wipe the table after you remove the dishes! ሳሕኖቹን ፡ ካነሣሣህ ፡ በኋላ ፡ ጠረጴዛውን ፡ ወልውለው
2. ጠረገ. He wiped the spittle from the floor. አክታውን ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ጠረገ
We wipe our shoes on the mat. ጫማችንን ፡ ሰሌኑ ፡ ላይ ፡ እንጠርጋለን
Wipe your nose with this handkerchief! በዚህ ፡ መሐረብ ፡ አፍንጫህን ፡ ጥረግ
*Wipe that smile off your face! አትገልፍጥ

**wipe away** ጠረገ(ለት)
She wiped her child's tears away. የልጇን ፡ እንባ ፡ ጠረገችለት

**wipe off** ጠረገ
First let me wipe off the dust of the table! መጀመሪያ ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አቧራውን ፡ ልጥረገው

**wipe out**
1. አወደመ. The earthquake wiped out the whole town. የመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ከተማውን ፡ በሙሉ ፡ አወደመው
2. አጠፋ. An all-out effort is needed to wipe out illiteracy. መሀይምነትን ፡ ለማጥፋት ፡ ሰፊ ፡ ጥረት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል

**wipe up** ጠረገ
Wipe up the spilled milk with a rag! የፈሰሰውን ፡ ወተት ፡ በጨርቅ ፡ ጥረገው

**wire** (v.)
1. በሽቦ ፡ አሰረ. He wired the two pieces together. ሁለቱን ፡ ቁራጮች ፡ በሽቦ ፡ አሰረ
2. ቴሌግራም ፡ አደረገ(ለት). He wired me to meet him at the railway station. ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ እንድጠብቀው ፡ ቴሌግራም ፡ አደረገልኝ

**be wired**
Is the house wired? ቤቱ ፡ ሲሠራ ፡ የኮረንቲ ፡ ገመድ ፡ ግድግዳው ፡ ውስጥ ፡ ተቀብሯል ?

**wire** (n.)
1. ሽቦ. The wire isn't strong enough. ሽቦው ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ አይደለም
The broken electric wire was making sparks. የተበጠሰው ፡ የኮረንቲ ፡ ሽቦ ፡ ብልጭ ፡ ብልጭ ፡ ይል ፡ ነበር
2. ቴሌግራም. Send him a wire! ቴሌግራም ፡ አድርግለት

**live wire** የኮረንቲ ፡ ሽቦ
Don't touch that live wire without rubber gloves! ያለ ፡ ላስቲክ ፡ ጓንት ፡ ያንን ፡ የኮረንቲ ፡ ሽቦ ፡ አትንካ

**pull wires** አማላጅ ፡ ላከ
He pulled wires to get his son transferred to Washington. ልጁ ፡ ወደ ፡ ዋሽንግተን ፡ እንዲዛወርለት ፡ አማላጅ ፡ ላከ
[See also 'barbed']

**wireless set** ሬዲዮን
The wireless set is broken. ሬዲዮኑ ፡ ተሰብሯል

**wisdom**
1. ጠቢብነት ፤ ጥበብ. His wisdom is known throughout the world. ጠቢብነቱ ፡ (ጥበቡ) ፡ በዓለም ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. ጥልቅነት. I challenge the wisdom of his decision. የሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ጥልቅነት ፡ እጠራጠራለሁ
*Some old men possess a lot of wisdom. አንዳንድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በጣም ፡ ብልሆች ፡ ናቸው

**wisdom tooth** በመጨረሻ ፡ የሚበቅል ፡ የመንጋጋ ፡ ጥርስ
The dentist pulled out his wisdom teeth. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚበቅለውን ፡ የመንጋጋ ፡ ጥርሱን ፡ አወለቀለት

**wise**
1. ጠቢብ ፤ ብልህ. He is very intelligent, but

not very wise. የመማር ፡ ችሎታው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ግን ፡ ብልህ ፡ (ጠቢብ) ፡ አይደለም
2. በጣም ፡ ዐዋቂ. He is a wise man. በጣም ፡ ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ነው
3. ጥሩ. You have made a very wise decision. ጥሩ ፡ ውሳኔ ፡ አድርገሃል

**-wise** በ --- በኩል
Moneywise he is doing well. በገንዘብ ፡ በኩል ፡ ጥሩ ፡ ይዟል

**wisely** ጥሩ
He wisely decided not to fight the truck driver. ከጭነት ፡ መኪና ፡ ነጂው ፡ ጋር ፡ ላለመደባደብ ፡ መምረጡ ፡ ጥሩ ፡ አድርጓል

**wiser**
*I was no wiser after reading that article. ያንን ፡ ጽሑፍ ፡ አንብቤ ፡ ምንም ፡ አላተረፍኩ

**wish** (v.)
1. ተመኘ. I wish that I could be there. እዚያ ፡ ብሆን ፡ እመኛለሁ
You may get whatever you wish. የምትመኘውን ፡ ሁሉ ፡ ልታገኝ ፡ ትችላለህ
I wouldn't wish that awful job on my worst enemy. ያን ፡ አስጠሊ ፡ ሥራ ፡ ለክፉ ፡ ጠላቴም ፡ አልመኘው
2. ተመኘ(ለት). We wished him luck on his trip. መልካም ፡ ጉዞ ፡ እንዲሆንለት ፡ ተመኘንለት
I wish you a Merry Christmas. መልካም ፡ የገና ፡ በዓል ፡ እመኝልሃለሁ
3. ፈለገ. Do you wish to go home? ወደ ፡ ቤት ፡ ለመሄድ ፡ ትፈልጋለህ ?

**wish for** ተመኘ
What do you wish for most? ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የምትመኘው ፡ ምንድነው ?

**(could) wish for**
*He has everything a woman could wish for. ሴት ፡ ከወንድ ፡ ልትመኘው ፡ የምትፈልገው ፡ ሁሉ ፡ አለው

**I wish...** ምነው ፡ በ + perfect
I wish I knew where I put my glasses! መነጽሬን ፡ የጣልኩበትን ፡ ምነው ፡ ባወቅኩ

**I wish I could**
*I wish I could tell you the whole story. ታሪኩን ፡ በሙሉ ፡ ብነግርህ ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር
[See also 'farewell']

**wish** (n.) ምኞት
My wish is easily satisfied. ምኞቴ ፡ በቀላሉ ፡ ይረካል
I send you my best wishes. መልካም ፡ ምኞቴን ፡ እገልጽልሃለሁ

*He has no wish to go. ለመሄድ ፡ ፈቃደኛ ፡ አይደለም

**wishful, ~ thinking** የሕልም ፡ እንጀራ
It is wishful thinking to feel that you will get a scholarship with your low grades. በዚህ ፡ ዝቅተኛ ፡ ውጤትህ ፡ ነጻ ፡ ትምህርት ፡ አገኛለሁ ፡ ማለት ፡ የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ነው

**wishy-washy** ወላዋይ
She is wishy-washy, so you can't depend on her. ወላዋይ ፡ ስለሆነች ፡ ልትተማመንባት ፡ አትችልም

**wistful** የመጓጓት
Though she refused, her wistful expression showed that she really wanted it. እምቢ ፡ ብትል ፡ እንኳ ፡ የመጓጓት ፡ አስተያየቷ ፡ በእርግጥ ፡ መፈለጓን ፡ አመለከተ

**wistfully** በጉጉት
The small child looked wistfully at the plate of cookies. ሕፃኑ ፡ ብስኩት ፡ ያለበትን ፡ ሳሕን ፡ በጉጉት ፡ ተመለከተ

**wit**
1. ቀልድ. What I like about him especially is his wit. ከሁሉም ፡ ነገሩ ፡ የምወደው ፡ ቀልዱን ፡ ነው
2. ቀልደኛነት. That was a representative example of his wit. የቀልደኛነቱ ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ይህ ፡ ነው
3. ወግ. His speech glittered with wit. ንግግሩ ፡ በወግ ፡ የደመቀ ፡ ነበር
4. የማሰብ ፡ ችሎታ. That poor man hasn't wit enough to earn a living. ያ ፡ ምስኪን ፡ ሠርቶ ፡ ለመብላት ፡ እንኳን ፡ የማሰብ ፡ ችሎታ ፡ የለውም

**wits** አእምሮ
People with quick wits learn easily. ንቁ ፡ አእምሮ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀላሉ ፡ ይማራሉ

**at one's wit's end**
*I'm at my wit's end with this problem. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚቻለኝን ፡ ሁሉ ፡ አድርጌ ፡ አቅቶኛል

**(be) out of one's wits** ግራ ፡ ገባው
He was out of his wits with fear. በፍርሃት ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ ነበር
*The snake scared her out of her wits. እባቡ ፡ አስደንግጧት ፡ ያለችበትን ፡ አታውቅም ፡ ነበር

**witch**
1. ጠንቋይ ፤ አስማተኛ. In olden days, people believed in witches. ድሮ ፡ ሰዎች ፡ በጠንቋይ ፡ ያምኑ ፡ ነበር

The witch gave the man a philter which turned him into a frog. አስማተኛዋ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪትነት ፡ የሚለውጥ ፡ መድኃኒት ፡ በሰውዬው ፡ ላይ ፡ አደረገችበት
2. ዛር. She frightened the child because she looked like a witch. ዛር ፡ ስለምትመስል ፡ ልጁን ፡ አስደነገጠችው

**witchcraft** ጥንቈላ
They still use witchcraft for curing diseases. በሽታን ፡ ለማዳን ፡ አሁንም ፡ በጥንቈላ ፡ ይጠቀማሉ

**witch doctor** ጠንቋይ
The witch doctor can cure your wound. ጠንቋዩ ፡ ቁስልህን ፡ ሊያድንህ ፡ ይችላል

**with**
1. ከ --- ጋር. I'll have lunch with him today. ዛሬ ፡ ምሳዬን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እበላለሁ
Don't argue with him! ከሱ ፡ ጋር ፡ አትከራከር
I won't have anything to do with her. ከሷ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ጉዳይ ፡ የለኝም
2. በ. Write your name with a pencil! ስምህን ፡ በእርሳስ ፡ ጻፍ
She met him with a smile. በፈገግታ ፡ ተቀበለችው
He has been with this company for years. በዚህ ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አገልግሏል
He was trembling with fear. በፍርሃት ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር
He did it with pleasure. በደስታ ፡ አደረገው
He shook with cold. በብርድ ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ነበር
We are pleased with the house. በቤቱ ፡ ተደስተናል
3. በ --- አማካይነት. The circus clown keeps his equilibrium with a pole. የሰርከሱ ፡ ተዋናይ ፡ ሚዛኑን ፡ በዘንግ ፡ አማካይነት ፡ ይጠብቃል
4. በ -- ዘንድ. His behavior will discredit him with the public. ምግባሩ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ያስገምተዋል
5. በበኩል. It's all right with me. በበኩሌ ፡ ግድ ፡ የለኝም
6. ከ --- የተነሣ. The boards of the floor were cracked with age. የወለሉ ፡ ሳንቃዎች ፡ ከማርጀታቸው ፡ የተነሣ ፡ ተሰነጣጥቀዋል
7. ለ --- አደራ. He left the dog with his sister when he went away. ሲሄድ ፡ ውሻውን ፡ ለእኅቱ ፡ አደራ ፡ ሰጠ
8. (gerundive). With all the work he's done, he still isn't finished. ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡ ገና ፡ አልጨረሰም
9. ስ + (imperfect). With the approach of sunset, it became chilly. የፀሐይ ፡ መጥለቂያ ፡ ሲቃረብ ፡ መቀዝቀዝ ፡ ጀመረ
With the coming of spring, the birds returned. ጸደይ ፡ ሲደርስ ፡ ወፎቹ ፡ ተመለሱ
10. ባለ + (noun). I want a coat with two pockets. ባለሁለት ፡ ኪስ ፡ ኮት ፡ እፈልጋለሁ
*With all her faults, I love her still. ብዙ ፡ ጉድለት ፡ ቢኖርባትም ፡ እንኳ ፡ አሁንም ፡ እወዳታለሁ
*With him, it's all a matter of money. ከገንዘብ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ አያውቅም
*With that remark, he left. እንደዚያ ፡ ብሎ ፡ ሄደ
*The English fought with the Germans against France. እንግሊዞች ፡ ጀርመን ፡ ፈረንሳይን ፡ ወጉ
*Do you want sugar with your tea? ሻይህ ፡ ውስጥ ፡ ስኳር ፡ እንዲጨመርልህ ፡ ትፈልጋለህ ?
*Are you with me or against me? ደጋፊዬ ፡ ነህ ፡ ወይስ ፡ ተቃዋሚዬ?

**be with one**
*I shall be with you in a few minutes. ከጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በኋላ ፡ አነጋግርሃለሁ

**have (something) with one** ያዘው
I don't have the book with me. መጽሐፉን ፡ አልያዝኩትም

**take (something) with one** ይዞ ፡ ሄደ
He took the book with him. መጽሐፉን ፡ ይዞ ፡ ሄደ
[See also 'what']

**withdraw** (withdrew), vt.
1. አነሣ. I withdraw the motion. ያቀረብኩትን ፡ ሐሳብ ፡ አነሣለሁ
2. አስወጣ. He withdrew his child from school. ልጁን ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ አስወጣ
3. አወጣ. I withdrew $10 from the bank. ከባንክ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ አወጣሁ
4. ሰረዘ. He withdrew the charge, and the man was released from jail. ክሱን ፡ ስለሰረዘ ፡ ሰውዬው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ ተለቀቀ
5. አሸሸ. She withdrew her hand from the hot iron. እጇን ፡ ከጋለው ፡ ካውያ ፡ አሸሸች
6. (= intr.) ተጸጸተ. He withdrew his unkind words. በተናገረው ፡ መጥፎ ፡ ቃል ፡ ተጸጸተ

**withdraw** (vi.)
1. ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈገ. The troops withdrew under heavy fire. ወታደሮቹ ፡ ከባድ ፡ ተኩስ ፡ ስለወረደባቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈጉ
2. ወደ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ሄደ. After dinner, the ladies withdrew. ከራት ፡ በኋላ ፡ ሴቶቹ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ሄዱ

3. ተገለለ. He withdrew from society. ከኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ተገለለ
[See also 'circulation']

**withdrawal** መውጣት
The withdrawal of troops marked the end of the war. የወታደሮቹ ፡ መውጣት ፡ የጦርነቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ

**make a withdrawal** ገንዘብ ፡ አወጣ
After making a withdrawal from the bank, he bought a ticket. ከባንክ ፡ ገንዘብ ፡ አውጥቶ ፡ ቲኬት ፡ ገዛ

**withdrawn** የገለልተኝነት
He has a withdrawn manner. የገለልተኝነት ፡ ጠባይ ፡ አለው

**withdrew,** see **withdraw**

**withheld,** see **withhold**

**wither** (vt.) አጨማደደ
Age has withered the old lady's face. እርጅና ፡ ያሮጊቷን ፡ ፊት ፡ አጨማዶታል

**wither** (vi.)
1. ጠወለገ. The plants withered in the hot sun. በፀሐይ ፡ ምክንያት ፡ አትክልቶቹ ፡ ጠወለጉ
2. መነመነ. Her hopes withered when she saw the stern expression on his face. ፊቱን ፡ ሲያጠቁር ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተስፋዋ ፡ ሁሉ ፡ መነመነ

**withhold** (witheld)
1. ከመግለጽ ፡ ተቈጠበ. He withheld his consent until I agreed to make a down payment. የመጀመሪያ ፡ ክፍያ ፡ ለመክፈል ፡ እስክስማማ ፡ ፈቃደኛነቱን ፡ ከመግለጽ ፡ ተቈጠበ
2. ያዘ. He withheld payment until the damaged goods were replaced. የተበላሹት ፡ እቃዎች ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ ክፍያውን ፡ ያዘ
3. አገለለ. The captain withholds his men from attack. ሻምበሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ከውጊያ ፡ ያገላቸዋል
4. ገታ. He withheld his anger. ንዴቱን ፡ ገታ

**be withheld** ተነፈገ
Freedom is a right which cannot be withheld. ነጻነት ፡ ሊነፈግ ፡ የማይቻል ፡ መብት ፡ ነው

**within** (prep.)
1. በ - - - ውስጥ. I expect an answer within three days. በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ መልስ ፡ እጠባበቃለሁ
Speeding is forbidden within the city limits. በከተማው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ከተወሰነ ፡ ፍጥነት ፡ በላይ ፡ መንዳት ፡ ክልክል ፡ ነው
2. በ - - ተራርቆ. The letters came within a few days of each other. ደብዳቤዎቹ ፡ በጥቂት ፡ ቀናት ፡ ተራርቀው ፡ ደረሱ
3. (= adv.) ራቅ ፡ ብሎ. We live within a mile of the station. ከጣቢያው ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ራቅ ፡ ብለን ፡ እንኖራለን
4. (= adv.) በማይበልጥ ፡ ርቀት. They live within a mile of the school. ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ በማይበልጥ ፡ ርቀት ፡ ይኖራሉ
*We're within walking distance of the theater. ቤታችን ፡ ከቲያትሩ ፡ ቤት ፡ የሚያስኬደው ፡ ጥቂት ፡ ነው

**within** (adv.) ከውስጥ
They will decorate your house within and without. ቤትህን ፡ ከውስጥም ፡ ከውጭም ፡ ያጌጡታል
He seemed calm, but within all was turmoil. የረጋ ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ ከውስጥ ፡ ጦፏል
*It is warm outside, but cold within. ደጁ ፡ ሞቃት ፤ ቤቱ ፡ ግን ፡ ብርድ ፡ ነው
[See also 'hearing, limit, memory, reach']

**without** (prep.)
1. ከ - - ውጭ. Soldiers are camped within and without the city walls. ወታደሮች ፡ ከከተማው ፡ አጥር ፡ ውስጥም ፡ ውጭም ፡ ሰፍረዋል
2. ያለ. Can I get in without a ticket? ያለ ፡ ቲኬት ፡ መግባት ፡ እችላለሁ ?
He was dismissed without reason. ያለ ፡ ምክንያት ፡ አስወጡት
You will have to do without luxuries. ያለቅንጦት ፡ ለመኖር ፡ መቻል ፡ አለብህ
3. ሳ + (negative imperfect). She left the room without saying a word. ምንም ፡ ሳትናገር ፡ ከቤት ፡ ወጣች
She went out without a hat. ባርኔጣ ፡ ሳታደርግ ፡ ከቤት ፡ ወጣች
Please bill me without delay! ሳትዘገይ ፡ ሒሳቡን ፡ ላክልኝ
*It is true without any doubt. ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የሌለበት ፡ እውነት ፡ ነው

**without** (adv.)
1. ከውጭ. The wind howled without, but within the house it was quiet and warm. ከውጭ ፡ ነፋሱ ፡ ያጕረመርም ፡ ነበር ፤ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ጸጥ ፡ ያለና ፡ የሞቀ ፡ ነበር
2. ከውጭ ፡ በኩል. The curtains are white without and green within. መጋረጃው ፡ ከውጭ ፡ በኩል ፡ ነጭ ፡ ከውስጥ ፡ ደግሞ ፡ አረንጓዴ ፡ ነው
[See also 'delay, reservation, reserve']

**withstand** (withstood)
1. ቻለ. They withstood the heat of the desert. የበረኻውን ፡ሙቀት ፡ ቻሉት
2. ሊገታ ፡ ቻለ. They withstood all temptations to leave the job. ሥራውን ፡ ለመልቀቅ ፡ የነበራቸውን ፡ ፍላጎት ፡ ሊገቱት ፡ ቻሉ
3. ተቋቋመ. Their durable friendship withstood many a heated argument. ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ጓደኝነታቸው ፡ ብዙ ፡ የተፋፋመ ፡ ክርክርን ፡ ተቋቍሟል
4. ተከላከለ. The soldiers steeled themselves to withstand the attack. ወታደሮቹ ፡ ውጊያውን ፡ ለመከላከል ፡ ታጠቁ

**withstood,** see **withstand**

**witless** (= adv.) በማይገባ ፡ አኳኋን
He made some witless remark to the minister and got fired for it. በማይገባ ፡ አኳኋን ፡ ሚኒስትሩን ፡ ስለተናገረው ፡ ከሥራው ፡ ተወገደ

**witness** (v.) አየ
Did you witness the accident? አደጋው ፡ ሲደርስ ፡ አይተሃል ?

**witness** (n.)
1. ምስክር. The witnesses haven't been examined yet. ምስክሮቹ ፡ ገና ፡ አልተጠየቁም
2. ማስረጃ. This receipt is witness that the bill was paid. ደረሰኙ ፡ ሒሳቡ ፡ ለመከፈሉ ፡ ማስረጃ ፡ ነው

**bear witness against** መሰከረበት
He saw me hitting the man and bore witness against me. ሰውዬውን ፡ ስደበድብ ፡ አይቶኝ ፡ ስለነበረ ፡ መሰከረብኝ

**bear witness to**
1. መሰከረ ፤ መሰከረ(ለት). Her tears bear witness to her sadness. እንባዋ ፡ ማዘኗን ፡ ይመሰክራል
I will bear witness to his character. ስለጠባዩ ፡ እመሰክርለታለሁ
2. ምስክር ፡ ሆነ. She bore witness to his crimes. ለወንጀሉ ፡ ምስክር ፡ ሆነች

**give witness on behalf of** ለ --- መሰከረ(ለት)
He gave witness on behalf of the accused. ለተከሳሹ ፡ መሰከረለት

**wittingly** ሆን ፡ ብሎ
He wittingly offended the judge. ዳኛውን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ አናደደው

**witty** ቀልደኛ
They always laugh when he is around because he is so witty. በጣም ፡ ቀልደኛ ፡ ስለሆነ ፡ እሱ ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ይሥቃሉ

**wives,** see **wife**

**wizard**
1. ጠንቋይ. The wizard cast a spell on the young woman. ጠንቋዩ ፡ በወጣቷ ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ አስማት ፡ አደረገባት
2. እሳት. He is a wizard at solving math problems. ሒሳብ ፡ ሲሠራ ፡ እሳት ፡ ነው

**wizened** የተሸበሸበ
He kissed his old mother's wizened cheeks. የአሮጊት ፡ እናቱን ፡ የተሸበሸቡ ፡ ጉንጮች ፡ ሳመ

**wobble**
1. ተውተረተረ. The baby wobbled a little and fell down. ሕፃኑ ፡ ትንሽ ፡ ተውተርትሮ ፡ ወደቀ
2. ተንቀጠቀጠ. The steering wheel wobbles. የመኪናው ፡ መሪ ፡ ይንቀጠቀጣል

**wobbly, feel** ~
1. ተብረከረከ. My legs feel wobbly because I was sick in bed so long. ታምሜ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልጋ ፡ ስለሰነበትኩ ፡ እግሬ ፡ ይብረከረካል
2. ዋገርቀ. The chair feels wobbly; don't sit in it! ወንበሩ ፡ የሚዋኘርቅ ፡ ስለሆነ ፡ አትቀመጥበት

**woe** ሐዘን
They expressed their woe in loud cries. ሐዘናቸውን ፡ በእሪታ ፡ ገለጹ

**woe to!** ወዮለት
Woe to those who break the law! ሕግን ፡ የሚጥሱ ፡ ወዮላቸው

**woeful**
1. አሳዛኝ. She cried upon hearing the woeful tale. አሳዛኙን ፡ ወሬ ፡ ስትሰማ ፡ አለቀሰች
2. ፍጹም. His woeful ignorance kept him from getting the job. ፍጹም ፡ ድንቁርናው ፡ ሥራውን ፡ ከማግኘት ፡ አገደው

**woke,** see **wake**

**wolf** (wolves) ተኵላ
The wolves attacked the hunters. ተኵላዎች ፡ አዳኞቹን ፡ አጠቋቸው

**wolves,** see **wolf**

**woman** (women) ሴት
The woman goes to the market. ሴትዮዋ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ትወጣለች
A woman doctor will examine your wife. ሚስትህን ፡ ሴት ፡ ሐኪም ፡ ትመረምራታለች
[See also 'aged, old, young']

**womanhood**
1. የሴትነት ፡ ባሕርይ. Her womanhood was highly regarded by all. የሴትነት ፡ ባሕርይዋ ፡ በ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የተደነቀ ፡ ነው
2. ሴቶች. Joan of Arc was an honor to womanhood. ጆን ፡ ኦፍ ፡ አርክ ፡ የሴቶች ፡ ክብር ፡ ነበረች
3. ሴት. She is undoubtedly the cream of womanhood. ያለጥርጥር ፡ የሴት ፡ ቁንጮ ፡ ነች

**grow to womanhood** ትልቅ ፡ ሴት ፡ ሆነች
The little girl we knew has grown to womanhood. የምናውቃት ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ ትልቅ ፡ ሴት ፡ ሆናለች

**womanish** እንደ ፡ ሴት
He has a womanish way of speaking. አነጋገሩ ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ ነው

**womankind** ሴቶች
Womankind has the responsibility of rearing children. ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የማሳደግ ፡ ኀላፊነ ት ፡ አለባቸው

**womanly**
1. የሴቶች ፡ ባሕርይ ፡ የሆነ. She has much womanly sympathy for those who need help. እርዳታ ፡ ለ ሚያስፈልጋቸው ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሴቶች ፡ ባ ሕርይ ፡ የሆነ ፡ ርኅራኄ ፡ አላት
2. የሴትነት ፡ ባሕርይ ፡ ያላት. Mother is a womanly person. እናታችን ፡ የሴትነት ፡ ባሕርይ ፡ ያላት ፡ ሰው ፡ ነች

**womb** ማሕፀን
It is questionable whether the child in the womb has a soul. በማሕፀን ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ፅ ንስ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የሌለው ፡ መሆኑ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው

**women**, see **woman**

**womenfolk** ሴቶች
The womenfolk do all the preparing of meals here. እዚህ ፡ ምግብ ፡ የሚያዘጋጁት ፡ ሴቶች ፡ ናቸው

**won**, see **win**

**wonder** (v.)
1. ተደነቀ. I shouldn't wonder if it were true. እውነት ፡ ቢሆን ፡ አልደነቅም
2. አስገረመ(ው). +I don't wonder at her refusing to marry him. አላገባውም ፡ ማለቷ ፡ አያስገርመኝም
3. ተጠራጠረ. I often wonder whether it's right. ልክ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እጠራጠራለሁ
4. ብሎ ፡ አሰበ. They wondered what was in the package. ጥቅሉ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ምን ፡ ይሆ ን ፡ ብለው ፡ አሰቡ
*I wonder what time it is. ስንት ፡ ሰዓት ፡ ይሆን ?
*I wonder what he'll do now. አሁን ፡ ምን ፡ ያ ደርግ ፡ ይሆን ?

**wonder** (n.)
1. አስገራሚ ፡ ነገር ፤ አስደናቂ ፡ ነገር. Television is one of the wonders of modern science. ዘመና ዊ ፡ ሳይንስ ፡ ከፈጠራቸው ፡ አስገራሚ ፡ ነገሮች ፡ (አስደናቂ ፡ ነገሮች) ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ቴሌቪዥ ን ፡ ነው
2. አድናቆት. We gazed in wonder at the pyramids. ፒራሚዶቹን ፡ አተኩረን ፡ በአድና ቆት ፡ ተመለከትን
3. (= adj.) አስደናቂ. It's a wonder that you got here at all. እዚህ ፡ መድረስህ ፡ አስደናቂ ፡ ነው

**and small wonder** (noun) + አያስደንቅም
He failed his exam and small wonder. በፈተና ፡ መውደቁ ፡ አያስደንቅም

**be filled with wonder** ተደነቀ
The shepherds were filled with wonder by the vision. እረኞቹም ፡ በታያቸው ፡ ተአምር ፡ ተደነቁ
**no wonder** (noun) + አያስደንቅም ፤ (noun) + አያስገርምም
No wonder it's cold, the window is open. መብረዱ ፡ አያስደንቅም ፤ መስኮቱ ፡ ክፍት ፡ ነው
He was taken ill and no wonder; he's been working 16 hours a day for years. መታመሙ ፡ አያስገርምም ፤ ለብዙ ፡ ዓመት ፡ በቀን ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ይሠራ ፡ ነበር

**work wonders**
1. ግሩም ፡ ሆነ. His plan worked wonders. እቅ ዱ ፡ ግሩም ፡ ሆነ
2. ፍቱን ፡ ሆነ. This medicine works wonders for cold. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ለጉንፋን ፡ ፍቱን ፡ ነው

**wonderful**
1. ግሩም. The dinner was wonderful. እራቱ ፡ ግሩ ም ፡ ነበር
She is a wonderful cook. ግሩም ፡ ወጥቤት ፡ ነች
2. አስደናቂ. The traveler had wonderful adventures. መንገደኛው ፡ አስደናቂ ፡ ጀብዱ ፡ ፈ ጸመ

**wonderfully** በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን
The woodwork is wonderfully carved. ከዕንጨ ት ፡ የተሠራው ፡ ነገር ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ተቀርጿል

**wondrous** የሚያስደንቅ
It is a wondrous sight. ለዓይን ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው

**wont** (n). ልማድ
He rose late, as was his wont. እንደ ፡ ልማዱ ፡ አርፍዶ ፡ ተነሣ
*He went to bed much earlier than was his wont. አለወትሮው ፡ በጊዜ ፡ ተኛ

**be wont to** የ --- ልማድ ፡ አለው ፤ ልማዱ ፡ ነው
He is wont to read the paper at breakfast. በቁርስ ፡ ላይ ፡ ጋዜጣ ፡ የማንበብ ፡ ልማድ ፡ አለው
He was wont to agree. መስማማት ፡ ልማዱ ፡ ነበር

**won't,** negative imperfect
I won't do it unless you pay me. ካልከፈልከኝ ፡ በስተቀር ፡ አልሠራውም

**woo**
1. ሊያባብል ፡ ሞከረ. He wooed her by giving her gifts. ገጸ ፡ በረከት ፡ በመስጠት ፡ ሊያባብላት ፡ ሞከረ
2. ሊያግባባ ፡ ሞከረ. The politician wooed his audience with promises. የፖለቲካ ፡ ዐዋቂው ፡ ተስፋ ፡ በመስጠት ፡ አድማጮቹን ፡ ሊያግባባቸው ፡ ሞከረ
3. ፈለገ. He wooed fame. ዝና ፡ ፈለገ

**wood** ዕንጨት
What kind of wood is it? ምን ፡ ዓይነት ፡ ዕንጨት ፡ ነው ?

**woods** ጫካ
Is there a path through the woods? በጫካው ፡ ውስጥ ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ አለ ?

**beat the woods** አውሬዎቹን ፡ ቀሰቀሰ
The servant began to beat the woods for game. አሽከርዬው ፡ ለአደን ፡ አውሬዎቹን ፡ መቀስቀስ ፡ ጀመረ
[See also 'pulp, shaving, sliver']

**wooded**
1. ጫካ ፡ የለበሰ. The wooded valleys and hills of Illubabor are quite beautiful. በኢሉባቦር ፡ የሚገኙ ፡ ጫካ ፡ የለበሱት ፡ ኮረብታዎችና ፡ ሸለቆዎች ፡ በጣም ፡ ውብ ፡ ናቸው
2. ጫካማ. We drove through wooded country on our way home. ወደ ፡ ቤታችን ፡ ስንመለስ ፡ ጫካማ ፡ አገር ፡ አቋረጥን

**wooden** የዕንጨት
The pan has a wooden handle. መጥበሻው ፡ የዕንጨት ፡ እጀታ ፡ አለው

**woodpile** የተከመረ ፡ ማገዶ
There is a woodpile in back of the house. ጓሮ ፡ የተከመረ ፡ ማገዶ ፡ አለ

**woodwork** ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ነገር
The woodwork is wonderfully carved. ከዕንጨት ፡ የተሠራው ፡ ነገር ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ተቀርጿል

**woody** ዛፍ ፡ የለበሰ
The woody hillside prevents the rain from washing away the soil. ዛፍ ፡ የለበሰው ፡ የኮረብታው ፡ ጐን ፡ ዝናብ ፡ አፈሩን ፡ እንዳያጥበው ፡ ይከላከላል

**become woody** እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ጠጠረ
Radishes become woody when they get old. ቀይ ፡ ሥር ፡ ሲቆይ ፡ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ይጠጥራል

**woof** ማግ
The warp and the woof make up the fabric of the cloth. ልብስ ፡ የሚሆነው ፡ ድርና ፡ ማግ ፡ ነው

**wool** ሱፍ
The blanket is made of pure wool. ብርድ ፡ ልብሱ ፡ የተሠራው ፡ ከንጹሕ ፡ ሱፍ ፡ ነው

**woolen** ከሱፍ ፡ የተሠራ
He bought a woolen tie. ከሱፍ ፡ የተሠራ ፡ ክራቫት ፡ ገዛ

**woolen sweater** ሱፍ ፡ ሹራብ
I bought a woolen sweater. ሱፍ ፡ ሹራብ ፡ ገዛሁ

**woolens** ሱፍ ፡ ልብስ
You must wear woolens in the winter. በክረምት ፡ ሱፍ ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ አለብህ

**word** (v.)
1. አቀረበ. You had better word your suggestion more politely. ሐሳብህን ፡ በበለጠ ፡ ትሕትና ፡ ብታቀርብ ፡ ይሻላል
2. ጻፈ. He worded his message clearly. መልእክቱን ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ጻፈ
*How do you want to word the telegram? የቴሌግራሙ ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ እንዲሆን ፡ ትፈልጋለህ ?

**word** (n.)
1. ቃል (pl. ቃላት). We have to learn fifty new words for tomorrow. ለነገ ፡ ሌላ ፡ ኀምሳ ፡ አዳዲስ ፡ ቃላት ፡ ማጥናት ፡ አለብን
2. ነገር. Have you had any word from your son lately? ከልጅህ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሰማኸው ፡ ነገር ፡ አለ ?

3. መልእክት. Leave word for me at the office if you can't come. ልትመጣ ፡ ካልቻልክ ፡ እቢሮ ዬ ፡ መልእክት ፡ ተውልኝ
4. ትእዛዝ. Father's word is law. ያባታችን ፡ ትእ ዛዝ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው
5. አነጋገር. He is honest in word and deed. ባነጋገሩም ፡ ሆነ ፡ ባድራጎቱ ፡ ሐቀኛ ፡ ነው
6. ወሬ. No word has come from the battle front. ከጦሩ ፡ ግንባር ፡ ምንም ፡ ወሬ ፡ አልደረሰም
He is not given to words. ወሬ ፡ አይወድም

**word for word** ቃል ፡ በቃል
Don't translate word for word! ቃል ፡ በቃል ፡ አትተርጒም

**be as good as one's word** እንዳለ ፡ አደረሰ
She said she would finish the dress today, and was as good as her word. ልብሱን ፡ ዛሬ ፡ እ ጨርሳለሁ ፡ ብላ ፡ እንዳለችው ፡ አደረሰች

**by word of mouth** በቃል
The story was transmitted by word of mouth. ታሪኩ ፡ የተላለፈው ፡ በቃል ፡ ነው

**exchange words**
They exchanged bitter words. ክፉ ፡ ቃል ፡ ተ ነጋገሩ

**give (one's) word** ቃል ፡ ገባ
He gave his word that he would finish the job. ሥራውን ፡ እንደሚጨርስ ፡ ቃል ፡ ገባ

**give (one's) word of honor** ቃል ፡ ገባ(ለት) ፤ የ መሐላ ፡ ቃል ፡ ሰጠ
I give you my word of honor that I will return. እንደምመለስ ፡ ቃል ፡ እገባልሃለሁ
He gave his word of honor not to lie. ላይዋሽ ፡ የመሐላ ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ

**have a word with** ተነጋገረ
They had words with me about the matter. ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ተነጋግረው ፡ ነበር
*May I have a word with you? እንዳፍታ ፡ ላነ ጋግርህ ?

**have words**
They had words yesterday. ትናንት ፡ ተሰዳድበ ው ፡ ነበር

**in a word** ባጭሩ
In a word, no. ባጭሩ ፤ አይሆንም

**in so many words** ቁርጥ ፡ አድርጎ
In so many words he told me to leave at once. ያኔውኑ ፡ እንድሄድ ፡ ቁርጥ ፡ አድርጎ ፡ ነገረኝ

**keep (one's) word** ቃሉን ፡ አከበረ
The boy kept his word. ልጁ ፡ ቃሉን ፡ አከበረ

**last word**
*This book is the last word on the subject. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የመጨረሻው ፡ ከፍ ተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያለው ፡ ነው
*She had the last word as always. እንደወትሮ ው ፡ እሷ ፡ እንዳለችው ፡ ሆነ

**leave word** ምልክት ፡ ተወ
He left word that he would be back soon. ቶሎ ፡ እመለሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ትቷል

**make (one) eat his words**
*They told him he would never succeed at anything, but he made them eat their words. ምንጊዜም ፡ አይሳካልህም ፡ ብለው ፡ ነግረውት ፡ ካሰበበት ፡ ደርሶ ፡ አሳፈራቸው

**mark my words!** ምን ፡ አለ ፡ በለኝ
Mark my words! He will be a great man someday. ምን ፡ አለ ፡ በለኝ ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ ትል ቅ ፡ ሰው ፡ ይሆናል

**my word!** ይገርማል
My word! Your children have certainly grown. ይገርማል! ልጆችህ ፡ በእውነት ፡ ትልልቅ ፡ ሆነዋል

**of few words** ብዙ ፡ የማይናገር
He is a man of few words but of profound thoughts. ብዙ ፡ የማይናገር ፡ ግን ፡ ሐሳበ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው

**put in a good word for one**
I'll put in a good word for you with the minister. በሚኒስትሩ ፡ ፊት ፡ ስላንተ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ እናገርልሃለሁ

**send word** ላከ(በት)
Please send me word of your safe arrival! ደኅና ፡ መድረስህን ፡ ላክብኝ

**take my word!** እመነኝ
Take my word for it, he's a liar. እመነኝ ፤ ው ሸታም ፡ ነው

**upon my word** ሙት ፤ እምላለሁ
Upon my word, this is the worst mess I've ever seen. ሙት ፤ ይህ ፡ አይቼ ፡ የማላውቀው ፡ ዓ ይነት ፡ ብልሽት ፡ ነው
Upon my word, I never said it. እምላለሁ ፤ ይህን ን ፡ አላልኩም
[See also 'breathe, fail, hard, mark, measured, mince, play, polite, sense, sharp']

**wording**
1. አጻጻፍ. The wording of this letter is not clear. የዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ አጻጻፍ ፡ ግልጽ ፡ አይደ ለም
The wording of the treaty is very difficult to understand. የስምምነቱን ፡ አጻጻፍ ፡ አንብቦ ፡ ለ መረዳት ፡ ያስቸግራል

2. ቃላትን ፡ መምረጥ. Careful wording helps you make clear to others what you really mean. ቃላትን ፡ በጥንቃቄ ፡ መምረጥ ፡ ለማለት ፡ የምት ፈልገውን ፡ ለሌሎች ፡ በግልጽ ፡ ለማስረዳት ፡ ይ ረዳሃል

**wordy** የተንዛዛ
His wordy explanations confuse people more than they explain anything. የተንዛዛ ፡ ማስረጃው ፡ ጉዳዩን ፡ ከማብራራት ፡ ይልቅ ፡ ሰዎችን ፡ ያደናግራል

**wore,** see **wear**

**work** (vt.)
1. አሠራ. He works his employees very hard. ሠራተኞቹን ፡ በኀይል ፡ ያሠራቸዋል
2. ሠራ. Do you know how to work an adding machine? በሒሳብ ፡ መኪና ፡ መሥራት ፡ ታውቃለህ ?
He worked the clay into a vase. ከጭቃ ፡ የ አበባ ፡ ማስቀመጫ ፡ ሠራ
3. አዳበረ. The farmers worked the soil. ገበሬዎቹ ፡ መሬቱን ፡ አዳበሩት

**work** (vi.)
1. ሠራ. I work from eight to five. ከሁለት ፡ እስ ከ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ እሠራለሁ
The mechanic is just now working on your car. ሜካኒኩ ፡ አሁን ፡ ያንተን ፡ መኪና ፡ መሥራት ፡ ይዟል
The elevator doesn't work. ሊፍቱ ፡ አይሠ ራም
He is working his way through college. እየሠራ ፡ የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ይማራል
2. ተጽዕኖ ፡ አለው. His music works on the mind of the listener. ሙዚቃው ፡ ባድማጮቹ ፡ አእምሮ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ አለው

**work away** ያለማቋረጥ ፡ ሠራ
He worked away until the job was done. ሥራው ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሠራ

**work for** ጣረ
Doctors work for the preservation of our health. ሐኪሞች ፡ ጤናችንን ፡ ለመጠበቅ ፡ ይጥራሉ

**work hard** በጣም ፡ ጣረ
They worked hard for peace. ለሰላም ፡ በጣም ፡ ጣሩ

**work in** ሥራውን ፡ ተለማመደ
Give him a chance to work in! ሥራውን ፡ እንዲ ለማመድ ፡ ዕድል ፡ ስጠው

**work (one) in** አስገባ
The dentist was very busy, but said he would be able to work me in late in the afternoon. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ በጣም ፡ ሥራ ፡ በዝቶበታል ፤ ሆ ኖም ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ እንደምንም ፡ ብዬ ፡ አስገባ ሃለሁ ፡ ብሎኛል

**work off**
*Work off your anger by taking a walk! ንዴትህ ፡ እንዲበርድልህ ፡ ተንሸራሸር

**work on** አግባባ
We are working on him to give us the day off. ቀኑን ፡ ዕረፍት ፡ እንዲሰጠን ፡ ለማድረግ ፡ እሱን ፡ እያግባባን ፡ ነው

**work out** (vt.)
1. ሠራ. I can work out these math problems. እነዚህን ፡ የሒሳብ ፡ ጥያቄዎች ፡ ልሠራ ፡ እችላለሁ
2. ፈጠረ. They're working out a new method for irrigating the land. መሬቱን ፡ በመስኖ ፡ ለ ማጠጣት ፡ አዲስ ፡ ዘዴ ፡ በመፍጠር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**work out** (vi.)
1. ሠራ. How do you think this idea would work out? ይህ ፡ ሐሳብ ፡ እንዴት ፡ የሚሠራ ፡ ይመስልሃል ?
2. ደረሰ. How did things work out? ነገሩ ፡ ከም ን ፡ ደረሰ ?
3. ተቃና(ለት). Their marriage just didn't work out. ጋብቻቸው ፡ ምንም ፡ አልተቃናላቸውም
4. ተሳካ(ለት). His plan did not work out. እቅዱ ፡ አልተሳካለትም
5. ተዋጣ. The new secretary did not work out. አዲሷ ፡ ጸሐፊ ፡ አልተዋጣችም

**(be) worked out** ተተነተነ
The plan is well worked out. እቅዱ ፡ በደንብ ፡ ተተንትኗል

**work over** አጠና
For my history class I worked over 20 volumes of Roman history. ለታሪክ ፡ ትምህርቴ ፡ ስለ ፡ ሮ ም ፡ ታሪክ ፡ ሀያ ፡ መጻሕፍት ፡ አጠናሁ

**work (oneself) too hard**
He works himself too hard. ራሱን ፡ በሥራ ፡ ያደክማል

**work up** ቀስ ፡ በቀስ ፡ አደገ
He worked up to a better job. ቀስ ፡ በቀስ ፡ ወደ ፡ ተሻለ ፡ ሥራ ፡ አደገ
*I'll have to work up an appetite. ሊያስርበኝ ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ አለብኝ

**work (one's) way through** ጥሶ ፡ አለፈ
I have to work my way through the crowd. በተሰ በሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መሀከል ፡ ጥሼ ፡ ማለፍ ፡ አለብኝ
[See also 'feverishly, rage, steam']

**work** (n.)
1. ሥራ. The work isn't interesting. ሥራው ፡ አያስ ደስትም

His work is teaching. ሥራው ፡ አስተማሪነት ፡ ነው
Don't phone him at work! በሥራው ፡ ላይ ፡ እያለ ፡ አትደውልለት
2. ጽሑፍ. Hamlet is Shakespeare's best-known work. በጣም ፡ የታወቀው ፡ የሼክስፒር ፡ ጽሑፍ ፡ ሀምሌት ፡ ነው
3. ሥዕል. The artist considers that picture to be his greatest work. ሠዓሊው ፡ ከሠራቸው ፡ ሥዕሎች ፡ ሁሉ ፡ ለዚያ ፡ ሥዕል ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ ይሰጠዋል
*He put in one hour's work before breakfast. ከቁርስ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሠራ

**works**
1. ሥራዎች. New public works are being planned. አዲስ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ታቅደዋል
All works of art should be protected against damage. የሥነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ከጉዳት ፡ መጠበቅ ፡ አለባቸው
2. መጻሕፍት. Have you read all of Shakespeare's works? የሼክስፒርን ፡ መጻሕፍት ፡ በሙላ ፡ አንብበሃል ?
3. ፋብሪካ. The iron works is shut down. የብረት ፡ ፋብሪካው ፡ ተዘግቷል

**hard work** ልፋት
After years of hard work, he finally arrived. ከብዙ ፡ ዓመት ፡ ልፋት ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ተሳካለት

**(be) out of work** ሥራ ፡ ፈታ
He has been out of work since the factory closed. ፋብሪካው ፡ ከተዘጋ ፡ ጀምሮ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፈታ ፡ ነው

**(it) takes a lot of work** ብዙ ፡ ደከመ
It took a lot of work to convince him that we were right. ልክ ፡ መሆናችንን ፡ እሱን ፡ ለማሳመን ፡ ብዙ ፡ ደከምን

**work** (adj.) የሥራ
Wear your work clothes when you come. ስትመጣ ፡ የሥራ ፡ ልብስህን ፡ ልበስ
[See also 'respite, short, swamp']

## workable
*This machine is in workable condition. ይህ ፡ መኪና ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል

## workday የሥራ ፡ ቀን
On a workday I must get up early. በሥራ ፡ ቀን ፡ በጧት ፡ መነሣት ፡ አለብኝ

## worker ሠራተኛ
There are two hundred workers in this factory. እዚህ ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሠራተኞች ፡ አሉ

## working (n.)
*Do you understand the working of this machine? ይህ ፡ መኪና ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራ ፡ ይገባሃል ?

**working** (adj.)
1. ሠራተኛ. The working girls have formed a club. ሠራተኞቹ ፡ ልጃገረዶች ፡ ክበብ ፡ አቋቋሙ
The working class is large in number. ሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ ቁጥሩ ፡ ከፍተኛ ፡ ነው
2. የሥራ. His working clothes were soiled with mud. የሥራ ፡ ልብሶቹ ፡ በጭቃ ፡ ተበክለዋል
May I call you during working hours? በሥራ ፡ ሰዓት ፡ ልደውልልህ ?

**working order, keep in good ~** በሚገባ ፡ ያዘ; **put in ~** እንዲሠራ ፡ አደረገ
Keep the car in good working order! መኪናዋን ፡ በሚገባ ፡ ያዝ
Put the machine in working order! መሣሪያውን ፡ እንዲሠራ ፡ አድርገው

## working man ሠራተኛ
A working man needs some kind of insurance. ሠራተኛ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ዋስትና ፡ ያስፈልገዋል

## workman (workmen) ሠራተኛ
The workmen are on strike. ሠራተኞቹ ፡ አድማ ፡ ላይ ፡ ናቸው

## workmanship አሠራር
We admired the workmanship of the churches of Lalibela. የላሊበላን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አሠራር ፡ አደነቅን

## workout የሰውነት ፡ ልምምድ
He had a good workout running in the field before breakfast. ከቁርስ ፡ በፊት ፡ሜዳው ፡ ላይ ፡ በመሮጥ ፡ ጥሩ ፡ የሰውነት ፡ ልምምድ ፡ አገኘ

**give a workout** ሞከሮ ፡ አየ
The mechanic gave the car a thorough workout after repairing it. ሜካኒኩ ፡ መኪናውን ፡ ከሠራ ፡ በኋላ ፡ በሚገባ ፡ ሞክሮ ፡ አየ

## workshop የመሣሪያ ፡ ቦታ
The workshop has all the machinery needed for car repairs. የመሣሪያው ፡ ቦታ ፡ ለመኪና ፡ ጥገና ፡ የሚያስፈልጉት ፡ መሣሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ አሉት

## world (n.)
1. ዓለም. If you are good in this world, you'll be rewarded in the next. በዚህ ፡ ዓለም ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ ከሠራህ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ዋጋህን ፡ ታገኛለህ

He has traveled all over the world. ዓለምን ፡ በ ሙሉ ፡ ዞሯል
She retired from the world to enter a convent. ዓለምን ፡ ንቃ ፡ ገዳም ፡ ገባች
2. ሰዎች. The world of sport was grieved by his death. የሱ ፡ መሞት ፡ የስፖርት ፡ ሰዎች ን ፡ ሁሉ ፡ አሳዘነ
All the world is interested in space travel. ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በጠፈር ፡ ጉዞ ፡ ይደሰታሉ
*The business world was surprised by the devaluation. በገንዘቡ ፡ ዋጋ ፡ መቀነስ ፡ በንግ ድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ተሸበሩ
*The plant world is dependent on sunlight. የዕፀዋት ፡ ሕይወት ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ላይ ፡ የተ መሠረተ ፡ ነው

**(a) world of**
*My holiday did me a world of good. ዕረፍቴ ፡ በጣም ፡ አድርጎ ፡ ጠቀመኝ
*Your visit did me a world of good. ጉብኝትህ ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ አተረፈልኝ

**(be) brought into the world** ተወለደ
He was brought into the world by a midwife. ባዋላጅ ፡ እርዳታ ፡ ተወለደ

**for the world** ምንም ፡ ቢሆን
I wouldn't hurt her feelings for the world. ምንም ፡ ቢሆን ፡ እሷን ፡ አላስቀይማትም

**in the world** ኧረ ፡ ለመሆኑ
Who in the world is he? ኧረ ፡ እሱ ፡ ለመሆኑ ፡ ማነው ?
*Where in the world have you been? የት ፡ ጠ ፋህ ?

**(be) out of this world** ታይቶ ፡ አይታወቅም
This food is out of this world. ይህ ፡ ምግብ ፡ ታ ይቶ ፡ አይታወቅም

**think the world of** ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ አለው
My father thinks the world of you. አባቴ ፡ ላን ተ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ አለው

**world** (adj.)
*We don't have a world language as yet. እስካሁን ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ የሚግባባበት ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ የለንም
[See also 'western']

## worldly ዓለማዊ
He is attached to worldly pleasures. ዓለማዊ ፡ ደ ስታን ፡ ይወዳል

## world powers ኀያላን ፡ መንግሥታት
Russia and the U.S. are world powers. አሜሪካ ና ፡ ሩሲያ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው

## worldwide
1. በመላው ፡ ዓለም ፡ የታወቀ. The association is worldwide. ማኅበሩ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የታወ ቀ ፡ ነው
2. ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሆነ. They set up a worldwide organization of Ethiopian studies. ዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥናት ፡ ማኅበር ፡ አቋቋሙ

## worm ትል
The worm was crawling on the ground. ትሉ ፡ እመሬቱ ፡ ላይ ፡ እየተሳበ ፡ ይሄድ ፡ ነበር

## (be) worm-eaten
1. ነቀዘ. The wood is worm-eaten. ዕንጨቱ ፡ ነቅዟል
2. ትል ፡ በላው. The apple is worm-eaten. ቱፋ ው ፡ ትል ፡ የበላው ፡ ነው

## wormy የነቀዘ
The wormy wood broke, and the house collapsed. የነቀዘው ፡ ዕንጨት ፡ ተሰብሮ ፡ ቤቱ ፡ ተደረመሰ

## worn, see wear

## worn (adj.) ያለቀ
A beggar in a worn, tattered coat is at the door. ያለቀና ፡ የተበጣጠሰ ፡ ካፖርት ፡ የለበሰ ፡ ለማኝ ፡ እደጅ ፡ ቆሟል

**be worn down** ተበላ
The stone steps were worn down by many feet. የድንጋዩ ፡ ደረጃዎች ፡ ከእግር ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ተበልተው ፡ ነበር

## worn-out ያለቀ
Throw away this worn-out pair of shoes! እነዚህን ፡ ያለቁ ፡ ጫማዎች ፡ ጣላቸው

**be worn-out** ደከመ
He looks worn-out. የደከመው ፡ ይመስላል

## worried (adj.) የተጨነቀ
The worried mother cried until her child was found. የተጨነቀችው ፡ እናት ፡ ልጇ ፡ እስከተገ ኘ ፡ ድረስ ፡ ታለቅስ ፡ ነበር
*He has a worried look. ሐሳብ ፡ የገባው ፡ ይመ ስላል

## worrisome
1. የተጨነቀ. The worrisome parents are constantly calling the police to find their child. የተጨነቁት ፡ ወላጆች ፡ ፖሊስ ፡ ልጃቸውን ፡ እንዲፈልግላቸው ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ ይደውሉ ፡ ነበር

2. የመጨነቅ. His worrisome behavior irritates me. የመጨነቅ ፡ ጠባዩ ፡ ያበሳጨኛል

**worry** (worried), vt.

1. አስቸገረ. She was always worrying her husband for more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ሁልጊዜ ፡ በመጠየቅ ፡ ባሏን ፡ አስቸገረችው
He worried me with foolish questions. ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ጥያቄዎች ፡ እየጠየቀ ፡ አስቸገረኝ
2. አሳሰበ. The future doesn't worry him. የወደፊቱ ፡ ምንም ፡ አያሳስበውም

**worry** (vi.) አሰበ ፤ ተጨነቀ
Don't worry! He will come soon. አታስብ ፤ ቶሎ ፡ ይመጣል
He is a very fearful person; he is always worrying about something. እሱ ፡ በጣም ፡ ፈሪ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይጨነቃል

**worry about** ተጨነቀ(በት)
You have nothing to worry about. ምንም ፡ የምትጨነቅበት ፡ ነገር ፡ የለም

**be worried** ሐሳብ ፡ ያዘው
I'm worried because I haven't heard from him in a week. ላንድ ፡ ሳምንት ፡ የሱን ፡ ወሬ ፡ ስላልሰማሁ ፡ ሐሳብ ፡ ይዞኛል

**worry** (worries), n. ሐሳብ ፤ ስጋት
Worry made his hair grey prematurely. ሐሳብ ፡ ያለጊዜው ፡ አሸበተው
Her face clouded with worry. ፊቷ ፡ በሐሳብ ፡ ጠቈረ
She got sick from worry. ከስጋት ፡ የተነሣ ፡ ታመመች

**give worry** አስጨነቀ
Her son gave her a great deal of worry. ልጇ ፡ ብዙ ፡ አስጨነቃት

**worse** የባሰ
First reports were bad, but worse soon followed. የመጀመሪያዎቹ ፡ መግለጫዎች ፡ መጥፎ ፡ ነበሩ ፤ ወዲያውኑ ፡ ደግሞ ፡ የባሱ ፡ ተከተሉ
Your work is bad, but mine is much worse. ሥራህ ፡ መጥፎ ፡ ነው ፤ የኔ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ የባሰ ፡ ነው

**worse than ever** ከምን ፡ ጊዜውም ፡ የባሰ
It's raining worse than ever. ከምን ፡ ጊዜውም ፡ የባሰ ፡ ዝናብ ፡ እየጣለ ፡ ነው

**be worse**
1. ባሰ(በት). The sick man seems worse today. የታመመው ፡ ሰውዬ ፡ ዛሬ ፡ የባሰበት ፡ ይመስላል
2. ከፋ. The actuality is worse than you suspect. እርግጡ ፡ አንተ ፡ ከምትጠረጥረው ፡ ይከፋል

**be worse off** እንዲያውም ፡ ባሰ(በት)
He is even worse off now because he has a broken leg. አሁን ፡ እግሩ ፡ ስለተሰበረ ፡ እንዲያውም ፡ ብሶበታል

**change for the worse** ባሰ(በት)
The weather changed for the worse. ያየሩ ፡ ጠባይ ፡ ባሰበት

**feel worse** ባሰ(በት)
He is feeling worse this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ብሶበታል

**get worse**
1. ተበላሸ. The nation got better materially but worse spiritually. አገሪቱ ፡ በሀብት ፡ ስትሻሻል ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ እየተበላሸች ፡ ሄደች
2. ጸና(በት). As the months went on, his illness got worse. ጊዜው ፡ እየገፋ ፡ ሲሄድ ፡ በሽታው ፡ እየጸናበት ፡ ሄደ

**get worse and worse** እየባሰ ፡ ሄደ
Her condition is getting worse and worse. ሁኔታዋ ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**grow worse and worse** እየባሰ ፡ ሄደ
The storm grew worse and worse. ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**make things worse** ነገሩን ፡ አባሰ
You are only making things worse by arguing. ክርክርህ ፡ ነገሩን ፡ ያብሰዋል

**none the worse**
*I like a man none the worse for being candid. እውነቱን ፡ ስለተናገረ ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ አልጠላውም

**be none the worse** ምንም ፡ አልጐዳውም
He is none the worse for having been imprisoned all year. ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ መታሰሩ ፡ ምንም ፡ አልጐዳው
[See also 'bad, turn out']

**worsen** (vt.) አባሰ(በት)
Smoking will worsen your cough. ማጨስ ፡ ሳልህን ፡ ያብስብሃል

**worsen** (vi.) ባሰ
The patient's condition continues to worsen. የበሽተኛው ፡ ሁኔታ ፡ እየባሰ ፡ ሄደ

**worship** (worshiped, or worshipped), v.
1. አመለከ. They worship gods. ባማልክት ፡ ያመልካሉ
A miser worships money. ጩቅ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ያመልካል
2. ሰገደ. The Israelites were punished for worshipping graven images. እስራኤላውያን ፡ ለተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ በመስገዳቸው ፡ ተቀጥተው ፡ ነበር

3. አስቀደሰ. Where do you worship? የምታስቀድ
ሰው ፡ የት ፡ ነው ?
4. በጣም ፡ ወደደ. She worships her mother. እናቷ
ን ፡ በጣም ፡ ትወዳለች

**worship** (n.)
1. ማምለክ. The worship of God is fostered by
many religions. ብዙ ፡ ሃይማኖቶች ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ማምለክን ፡ ይደግፋሉ
2. ከፍተኛ ፡ ክብር ፡ መስጠት. Hero worship is
common among young men. ለጀግና ፡ ከፍተኛ ፡
ክብር ፡ መስጠት ፡ በወጣቶች ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡
ነው

**place of worship** የመጸለያ ፡ ቦታ
Places of worship should never be closed.
የመጸለያ ፡ ቦታዎች ፡ ፈጽሞ ፡ መዘጋት ፡ የለባቸውም
[See also 'divine, house ']

**worshipper** ምእመን (pl. ምእመናን)
The worshippers gathered at the shrine.
ምእመናኑ ፡ በቅዱስ ፡ ቦታ ፡ ተሰበሰቡ

**worst** (n.) የባሰ
But wait, I haven't told you the worst. ኧ
ረ ፡ ቆይ ፤ ገና ፡ የባሰውን ፡ አልነገርኩህም
The destruction of Kara Qore by an earthquake
was the worst in recent times. የካራ ፡ ቆሬ ፡ በመ
ሬት ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ መጥፋት ፡ በቅር
ብ ፡ ጊዜ ፡ ከደረሱት ፡ ጥፋቶች ፡ ሁሉ ፡ የባሰ ፡
ነበር
*He got the worst of the argument. በክርክሩ ፡
ተሸነፈ

**worst** (adj.)
1. ከ - - ሁሉ ፡ በጣም ፡ የከፋ. It's thè worst
accident I can remember. ከማስታውሰው ፡ አደ
ጋ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የከፋ ፡ ነው
2. ከፋ. I wouldn't wish that awful job on my
worst enemy. ያን ፡ አስጠሊ ፡ ሥራ ፡ ለከፋ ፡ ጠ
ላቴም ፡ አልመኘው
*I got the worst piece. ለኔ ፡ መጥፎው ፡ ደረሰኝ

**worst** (adv.)
*He acts worst when he is tired. በደከመ ፡ ጊዜ ፡
ከምንጊዜም ፡ የባሰ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ይሠራል

**at worst** ግፋ ፡ ቢል
At worst, the storm may last a week. ግፋ ፡ ቢ
ል ፡ ዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ቢቆይ ፡ ነው

**be worst off** ባሰ(በት)
Of the three, he is worst off. ከሦስቱ ፡ እሱ ፡ የ
ባሰበት ፡ ነው

**for the worst**
I am prepared for the worst. ከሁሉ ፡ የከፋ ፡ ነ
ገር ፡ ቢመጣም ፡ ተዘጋጅቻለሁ

**if worst comes to worst** የባሰ ፡ ቢብስ
If worst comes to worst, we can always sell
our property. የባሰ ፡ ቢብስ ፡ ምንጊዜም ፡ ንብረ
ታችንን ፡ ልንሸጥ ፡ እንችላለን

**(be) worsted** ተሸነፈ
He was badly worsted in the fight. በጥሉ ፡ ላይ ፡
ክፉኛ ፡ ተሸነፈ

**worth** (n.)
1. ምንነት ፤ ዋጋ. You can't tell a man's worth by
the color of his skin. የሰውን ፡ ምንነት ፡ በቆዳ
ው ፡ ቀለም ፡ ልታውቅ ፡ አትችልም
The intrinsic worth of a man cannot be
measured by his wealth. የሰው ፡ ልጅ ፡ እውነተ
ኛ ፡ ዋጋው ፡ በሀብቱ ፡ መጠን ፡ ሊመዘን ፡ አይች
ልም
2. ጥቅም. We should read books of real worth.
እውነተኛ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጡ ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፡
አለብን
3. ግምት. What is it worth to you? ምን ፡ ግም
ት ፡ ትሰጠዋለህ ?
*I know his worth as a friend. ለጓደኝነት ፡ የቱን ፡
ያህል ፡ እንደሆነ ፡ አውቀዋለሁ

**worth of**
*Give me fifty cents' worth of salt. የኀምሳ ፡ ሳ
ንቲም ፡ ጨው ፡ ስጠኝ

**worth** (adj.) የሚገባ
This is a movie worth seeing. ይህ ፡ ሊታይ ፡ የ
ሚገባው ፡ ፊልም ፡ ነው
The matter isn't worth mentioning. ነገሩ ፡ መጠ
ቀስ ፡ የሚገባው ፡ አይደለም

**be worth**
1. አወጣ. I paid 300 dollars for it, but it's
worth more now. የከፈልኩት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡
ብር ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ይበልጥ ፡ ያወጣል
That horse is worth five hundred dollars.
ያ ፡ ፈረስ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያወጣል
2. አለው. He is worth a million dollars. አንድ ፡
ሚሊዮን ፡ ብር ፡ አለው
3. ይገባል. It's worth the trouble. ቢጨነቁለት ፡
ይገባል
4. ዋጋ ፡ አለው. The frame itself is worth more
than the picture. ከሥዕሉ ፡ ይልቅ ፡ ከፈፉ ፡ ብቻው
ን ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ አለው
5. ጠቀመ. Is the book worth reading? መጽሐፉን ፡
ቢያነቡት ፡ ይጠቅማል?
*It isn't worth the effort. የጥረቱን ፡ ያህል ፡ አ
ይሆንም

**for what it is worth** እንዳለ
I pass the news on to you for what it is worth.
ወሬውን ፡ እንዳለ ፡ ላንተ ፡ አስተላልፍልሃለሁ

**(one's) money's worth**
*We certainly got our money's worth from our car. በእርግጥ ፡ ለመኪናችን ፡ ያወጣንበትን ፡ ያህል ፡ አገልግሎት ፡ አገኘን
[See also 'while']

**worthless** ዋጋ ፡ ቢስ ፤ የማይረባ
He squandered his money on worthless things. ለዋጋ ፡ ቢስ ፡ (ለማይረባ) ፡ እቃ ፡ ገንዘቡን ፡ አ ባከነ

**be worthless** ዋጋ ፡ የለውም
This money is worthless because it is counterfeit. ይህ ፡ የሐሰት ፡ ገንዘብ ፡ ስለሆነ ፡ ዋጋ ፡ የለ ውም

**worthwhile** የሚረባ
A worthwhile book is more valuable than many films. የሚረባ ፡ መጽሐፍ ፡ ከብዙ ፡ ፊልም ፡ የበለጠ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው

**be worthwhile** ዋጋ ፡ አለው ፤ ጠቀመ
Does your job seem worthwhile? ሥራህ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ይመስልሃል ?
The question has narrowed down to this: is it worthwhile or not? ጉዳዩ ፡ በዚህ ፡ ተወስ ኗል ፤ ዋጋ ፡ አለው ፡ ወይስ ፡ የለውም ?
Is it worthwhile retreading the tire? ጎማውን ፡ ማሳደስ ፡ ይጠቅማል ?

**be hardly worthwhile** ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው
All this fussing about such a small matter is hardly worthwhile. ስለዚህ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መቸገር ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ነው

**worthy**
1. ዋጋ ፡ ያለው. This is for a worthy cause. ይህ ፡ ዋጋ ፡ ላለው ፡ ዓላማ ፡ ነው
2. እርዳታ ፡ የሚያስፈልገው. She helps only the worthy poor. እርዳታ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ድ ሆች ፡ ብቻ ፡ ትረዳለች

**worthy of** የሚገባ
His courage was worthy of high praise. ጀግንነቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ምስጋና ፡ የሚገባው ፡ ነው

**make (one) worthy** ብቁ ፡ አደረገ
His rectitude makes him worthy to be a judge. ታማኝነቱ ፡ ለዳኝነት ፡ ብቁ ፡ አደረገው
[See also 'note, notice']

**would**
1. imperfect (affirmative, negative). He said he would come in ten minutes. በዐሥር ፡ ደቂ ቃ ፡ ውስጥ ፡ እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ነበር
I thought that would happen. ይህ ፡ ይደርሳል ፡ ብዬ ፡ አስቤ ፡ ነበር
He would never take the job. ምንም ፡ ቢሆን ፡ ሥራውን ፡ አይቀበልም
2. simple imperfect + ነበር. The children would play for hours in the park. ልጆቹ ፡ በመ ናፈሻው ፡ ቦታ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር
He would have helped if you had asked him. ጠይቀኸው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይረዳህ ፡ ነበር
*Please, would you hand me that book. ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ ታቀብለኝ

**would like** ይፈልግ ፡ ነበር; (negative) አይፈልግም
I would like to go with you, but I can't. ካንተ ፡ ጋር ፡ ለመሄድ ፡ እፈልግ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አልችልም
I wouldn't like anyone to steal my bike. ቢስኪሌቴን ፡ ማንም ፡ እንዲሰርቀኝ ፡ አልፈልግም

**would rather**
*Would you rather go to the theater? ወደ ፡ ቲያ ትሩ ፡ ብትሄድ ፡ ይሻል ፡ ይሆን ?
*We would rather live in the country. ባላገር ፡ ብንኖር ፡ ይሻለናል

**would that**
*Would that I had bought the farm when it was so cheap! ምነው ፡ ርካሽ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የእርሻውን ፡ መሬት ፡ በገዛሁ ፡ ኖሮ

**would-be** ወደፊት ፡ ለመሆን ፡ የሚመኝ
Several would-be actors came to the theater. አንዳንድ ፡ ወደፊት ፡ ተዋናይ ፡ ለመሆን ፡ የሚመ ኙ ፡ ወደ ፡ ቲያትሩ ፡ መጡ

**wound**, see **wind**

**wound** (v.)
1. አቈሰለ. The hunter wounded the animal with one shot. አዳኙ ፡ እንስሳውን ፡ ባንድ ፡ ጥ ይት ፡ አቈሰለው
2. ስሜቱን ፡ ጐዳ. His cruel words wounded him. መጥፎ ፡ ንግግሩ ፡ ስሜቱን ፡ ጐዳው

**wound** (n.) ቊስል
It will be a couple of months before the wound in his leg is healed. የእግሩ ፡ ቊስል ፡ እስኪድን ፡ ድረስ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ይፈጃል

**be a wound to** አጐደፈ(በት)
The loss of his job was a wound to his pride. ሥራውን ፡ ማጣቱ ፡ ክብሩን ፡ አጐደፈበት

**wounded** (adj.) የቈሰለ
An annuity is paid to all wounded patriots. ለቈሰሉት ፡ አርበኞች ፡ ሁሉ ፡ አበል ፡ ይከፈላቸዋል

**wounded man** ቊስለኛ
The wounded man soon died. ቊስለኛው ፡ ወዲ ያውኑ ፡ ሞተ

**be wounded** ቈሰለ
Several men were wounded in the brawl.
በጥሉ ፡ ጊዜ ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ቈሰሉ

**wove**, see **weave**

**wrang**, see **wring**

**wrangle** ተጨቃጨቀ
The children are always wrangling about
something. ሕፃናቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ነ
ገር ፡ እንደተጨቃጨቁ ፡ ነው

**wrap** (wrapped)
1. ጠቀለለ. She wrapped the baby in a blanket.
ሕፃኑን ፡ በብርድ ፡ ልብስ ፡ ጠቀለለችው
Please wrap the gift! ስጦታውን ፡ ትጠቀልለው
2. ጠመጠመ. She wrapped a scarf around her
head. ራሷ ፡ ላይ ፡ ያንገት ፡ ፎጣ ፡ ጠመጠመች
**be wrapped** ተሸፈነ
The incident is wrapped in mystery. ጉዳዩ ፡ ባል
ታወቀ ፡ ምስጢር ፡ የተሸፈነ ፡ ነው

**wrap around one** አለበሰ
She wrapped a blanket around the baby.
ሕፃኑን ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ አለበሰችው

**wrap oneself in**
1. ለበሰ. Wrap yourself in a blanket while
I dry your clothes. ልብስህን ፡ እስካደርቅልህ ፡
ድረስ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ ልበስ
2. ደረበ. She wrapped herself in a shawl.
ያንገት ፡ ልብስ ፡ ደረበች

**wrap up** ጠቀለለ
Shall I wrap it (up) for you? ልጠቅልልህ ?

**(be) wrapped up**
*She's wrapped up in her children. ሐሳቧ ፡
ልጆቿ ፡ ናቸው

**(be all) wrapped up** ተዋጠ
He is all wrapped up in his work. በሥራው ፡ ተ
ውጧል
[See also 'shroud']

**wrap(s)** ተደራቢ
Scarfs, coats, and furs are wraps. ፎጣ ፤ ካፖርት
ትና ፡ ባለ ፡ ጸጉር ፡ ልብስ ፡ ተደራቢዎች ፡ ናቸው

**wrapper** መጠቅለያ
The newspaper is mailed in a paper wrapper.
ጋዜጣው ፡ በወረቀት ፡ መጠቅለያ ፡ ተደርጎ ፡ ተላከ

**wrapping** ሽፋን
Can you get the wrapping off? ሽፋኑን ፡ ልታነ
ሣው ፡ ትችላለህ ?

**wrapping paper** መጠቅለያ ፡ ወረቀት
I need more wrapping paper for the package.
ለጥቅሉ ፡ ተጨማሪ ፡ መጠቅለያ ፡ ወረቀት ፡ እፈ
ልጋለሁ

**wrath** ቁጣ
A soft answer turns away wrath. የለሰለሰች ፡
ምላሽ ፡ ቁጣን ፡ ታበርዳለች

**be full of wrath** በጣም ፡ ተናደደ
She was full of wrath against the landlord.
በቤቱ ፡ ጌታ ፡ በጣም ፡ ተናዳ ፡ ነበር

**wreath** የአበባ ፡ ጉንጉን
He placed a wreath on the grave. በመቃብሩ ፡
ላይ ፡ የአበባ ፡ ጉንጉን ፡ አስቀመጠ

**wreathe** ጐነጐነ
The children wreathed flowers to put on the
soldier's grave. ልጆቹ ፡ በወታደሩ ፡ መቃብር ፡
ላይ ፡ ለማኖር ፡ አበባ ፡ ጐነጐኑ

**be wreathed in** ተሞላ
His face was wreathed in smiles. ፊቱ ፡ በፈገግ
ታ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**wreck** (v.)
1. እንክትክት ፡ አደረገ. A tree fell on my car
and wrecked it. ዛፍ ፡ መኪናዬ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡
እንክትክት ፡ አደረጋት
2. አመድ ፡ አደረገው. The crash wrecked the car.
ግጭቱ ፡ መኪናዋን ፡ አመድ ፡ አደረጋት
3. አፈራረሰ. The explosion wrecked the whole
plant. ፈንጂው ፡ ፋብሪካውን ፡ በሙሉ ፡ አፈ
ራረሰው
4. አፈረሰ. Wrecking an altar is a sacrilege.
ታቦት ፡ ማፍረስ ፡ የረከሰ ፡ ተግባር ፡ ነው
5. ሰባበረ. He was so nervous that he all but
wrecked the machine. ከመርበትበቱ ፡ የተነሣ ፡
መኪናዋን ፡ ሊሰባብራት ፡ ምንም ፡ አልቀረው
6. ጐዳ. Poor habits can wreck one's health.
መጥፎ ፡ ልማድ ፡ የሰውን ፡ ጤንነት ፡ ይጐዳል
7. አጉል ፡ አደረገ. The rain wrecked our plans
for the picnic. ዝናቡ ፡ ለሽርሽር ፡ ያለንን ፡ እ
ቅድ ፡ አጉል ፡ አደረገብን
8. አበላሸ. His extravagance wrecked his
business. ገንዘብ ፡ ማባከኑ ፡ ጉዳዩን ፡ አበላሸው

**be wrecked** እንክትክቱ ፡ ወጣ
The car was completely wrecked. መኪናዋ ፡ በፍ
ጹም ፡ እንክትክቷ ፡ ወጣ

**wreck** (n.)
1. ፍርስራሽ. The bodies are still buried in the
wreck. ሬሳዎቹ ፡ ገና ፡ ፍርስራሹ ፡ ውስጥ ፡ እንደ
ተቀበሩ ፡ ናቸው

2. አደጋ. Were any killed in the wreck? ባደጋው ፡ የሞቱ ፡ ነበሩ ?
3. በግጭት ፡ የተሰባበረ ፡ ነገር. She averted her eyes from the wreck. በግጭቱ ፡ ከተሰባበረው ፡ ነገር ፡ ዓይኗን ፡ ዞር ፡ አደረገች
4. (የመርከብ) ፡ አሰባበር. I heard an authentic account of the wreck given by one of the ship's officers. ስለ ፡ መርከቡ ፡ አሰባበር ፡ ከመርከቡ ፡ መኰንኖች ፡ አንዱ ፡ የሰጠውን ፡ የሚታመን ፡ መግለጫ ፡ ሰማሁ
5. ጤና ፡ ያጣ ፡ ሰው. He is a wreck from overwork. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ከመሥራት ፡ የተነሣ ፡ ጤና ፡ ያጣ ፡ ሰው ፡ ነው

**wreck of** የተሰባበረ
The wrecks of three ships were cast upon the shore by the waves. ሦስት ፡ የተሰባበሩ ፡ መርከቦች ፡ በሞገድ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ተወርውረዋል

**be a nervous wreck** ናላው ፡ ዞረ
After taking care of his children for awhile, I am a nervous wreck. ልጆቹን ፡ ስጠብቅለት ፡ ቆይቼ ፡ ናላዬ ፡ ዞረ

**cause the wreck** (= be wrecked) ወደመ
+Heavy rains caused the wreck of crops. አዝመራው ፡ በከባድ ፡ ዝናም ፡ ምክንያት ፡ ወደመ
[See also 'train']

**wreckage** ባደጋ ፡ የተጨረመተ
He was pinned under the wreckage of his car. ባደጋው ፡ ከተጨረመተው ፡ መኪና ፡ ሥር ፡ ተቀርቅሮ ፡ ነበር

**wrecked** (adj.) የተሰበረ ፤ የተጐዳ
The wrecked cars were towed away by the police. የተሰበሩትን ፡ (የተጐዱትን) ፡ መኪናዎች ፡ ፖሊሶች ፡ ጐትተው ፡ ወሰዱቸው

**wrench** (vt.)
1. መንጥቆ ፡ ወሰደ. He wrenched the book from my hands. መጽሐፉን ፡ ከእጇ ፡ መንጥቆ ፡ ወሰደ
2. (= vi.) ወለቀ. +I wrenched my shoulder trying to push my car. መኪናዬን ፡ እገፋለሁ ፡ ብዬ ፡ ትከሻዬ ፡ ወለቀ
3. (= vi.) ወለም ፡ አለው. +She wrenched her knee when she fell. በወደቀች ፡ ጊዜ ፡ ጉልበቷ ፡ ወለም ፡ አላት

**wrench off** በኀይል ፡ ጠምዝዞ ፡ ሰበረ
He wrenched the knob off when he was trying to open the door. መዝጊያውን ፡ ለመክፈት ፡ ሲሞክር ፡ እጀታውን ፡ በኀይል ፡ ጠምዝዞ ፡ ሰበረው

**wrench** (n.) ኪያቬ
I need a wrench to tighten this bolt. ብሎኑን ፡ ለማጥበቅ ፡ ኪያቬ ፡ ያስፈልገኛል

**wrest**
1. በጉልበት ፡ ነጠቀ. He wrested the knife from the crazy man. ሰንጢውን ፡ ከእብዱ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በጉልበት ፡ ነጠቀ
2. በኀይል ፡ ነጠቀ. The army wrested power from the dictator. ሰራዊቱ ፡ የአምባገነኑን ፡ ሥልጣን ፡ በኀይል ፡ ነጠቀው

**wrest a living** ጥሮ ፡ ግሮ ፡ ኖረ
The farmer wrests a living from the soil. ገበሬው ፡ በእርሻ ፡ ጥሮ ፡ ግሮ ፡ ይኖራል

**wrestle** ታገለ
He wrestled with the thief, but the thief broke loose. ሌባውን ፡ ታግሎት ፡ ነበር ፤ ግን ፡ አመለጠው
I've been wrestling with this problem for hours. ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ከዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ጋር ፡ ስታገል ፡ ነበር

**wrestler** ታጋይ ፤ ትግለኛ
The wrestler grappled with his opponent. ታጋዩ ፡ ከተቃዋሚው ፡ ጋር ፡ ተናነቀ
The champion wrestler seems invincible. ሻምፒዮኑ ፡ ትግለኛ ፡ የማይበገር ፡ ይመስላል

**wrestling** ትግል
I like to watch wrestling. ትግል ፡ መመልከት ፡ እወዳለሁ

**wrestling match** የትግል ፡ ግጥሚያ
Today we watched a wrestling match. ዛሬ ፡ የትግል ፡ ግጥሚያ ፡ አየን

**wretch**
1. ምስኪን. The wretch was begging for bread by the roadside. ምስኪኑ ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ ሆኖ ፡ ዳቦ ፡ ይለምን ፡ ነበር
2. እርጉም. Some wretch stole my books. አንድ ፡ እርጉም ፡ መጽሐፎቼን ፡ ሰረቀ

**wretched**
1. ጨቋኝ. The wretched tyrant reduced the prosperous city to a poor village. ጨቋኙ ፡ ገዢ ፡ የበለጸገችውን ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ድኽነት ፡ አወረዳት
2. ምስኪን. The wretched people were begging for food. ምስኪኖቹ ፡ ሰዎች ፡ ምግብ ፡ ይለምኑ ፡ ነበር
3. መጥፎ. A wretched meal of boiled potatoes was all I received. ያገኘሁት ፡ ምግብ ፡ መጥፎ ፡ የተቀቀለ ፡ ድንች ፡ ብቻ ፡ ነው

**feel wretched** ደኅንነት ፡ አይሰማውም
I still feel wretched even though I got off the plane some hours ago. ከአውሮፕላን ፡ ከወረድኩ ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ሰዓት ፡ ቢሆንም ፡ አሁንም ፡ ደኅንነት ፡ አይሰማኝም

**wriggle**

1. ተቍነጠነጠ. The little children wriggled in their seats from boredom. ትንንሾቹ ፡ ልጆች ፡ ከመሰልቸት ፡ የተነሣ ፡ መቀመጫቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ተቍነጠነጡ
2. ተጥመለመለ. The worm wriggled on the hook. ትሉ ፡ መንጠቆው ፡ ላይ ፡ ይጥመለመል ፡ ነበር

**wriggle out**
1. ተጥመልምሎ ፡ ወጣ. The worm wriggled out of my hand when I tried to put it on the hook. መንጠቆው ፡ ላይ ፡ ልሰካው ፡ በሞከርኩ ፡ ጊዜ ፡ ትሉ ፡ ከእጄ ፡ ውስጥ ፡ ተጥመልምሎ ፡ ወጣ
2. በዘዴ ፡ አመለጠ. That boy can wriggle out of any difficulty. ያ ፡ ልጅ ፡ ከማንኛውም ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ በዘዴ ፡ ሊያመልጥ ፡ ይችላል

**wring** (wrang, wrung)
1. አሻሸ. He stood there crying and wringing his hands. እዚያው ፡ ቆሞ ፡ እጁን ፡ እያሻሸ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር
2. ጠመዘዘ. Wring the clothes before you hang them up! ልብሶቹን ፡ ከማስጣትህ ፡ በፊት ፡ ጠምዝዛቸው
3. አጥብቆ ፡ ጨበጠ. He wrung his old friend's hand in joy at seeing him. የድሮ ፡ ጓደኛውን ፡ በማየቱ ፡ ተደስቶ ፡ እጁን ፡ አጥብቆ ፡ ጨበጠ
4. አስተፋ. The beggar could wring money from a miser with his sad story. አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ በመንገር ፡ ለማኝ ፡ ከጩቅ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያስተፋ ፡ ይችላል
*The police wrung a confession out of him. ፖሊሶች ፡ በማስገደድ ፡ አሳመኑት

**wring (one's) heart** ልቡን ፡ በኀይል ፡ ነካ
Her sad story wrung our hearts. አሳዛኝ ፡ ታሪኩ ፡ ልባችንን ፡ በኀይል ፡ ነካው

**wring out** ጠመዘዘ
Wring out your wet shirt! እርጥቡን ፡ ሸሚዝህን ፡ ጠምዝዘው

**wring water from** ጨመቀ
The maid wrung water from the wet towel. ገረዲ ፡ እርጥቡን ፡ ፎጣ ፡ ጨመቀችው

**wrinkle** (vt.)
1. አጨማደደ. Rain wrinkles clothing. ዝናብ ፡ ልብስ ፡ ያጨማዳል
2. አኰማተረ. He wrinkled his forehead. ግንባሩን ፡ አኰማተረ

**wrinkle** (vi.) ተጨማደደ
This silk wrinkles easily. ይህ ፡ ሐር ፡ በቀላሉ ፡ ይጨማደዳል

**be wrinkled** ቆዳው ፡ ተሸበሸበ
The aged man was wrinkled and bent. ሽማግሌው ፡ ቆዳቸው ፡ ከመሸብሸቡም ፡ በላይ ፡ ጐብጠዋል
[See also 'seam']

**wrinkle** (n.)
1. ሽብሽብ. There was dirt in the wrinkles of her forehead. በግንባሯ ፡ ሽብሽብ ፡ ውስጥ ፡ ጉድፍ ፡ ነበር
2. የተጨማደደ. She ironed out the wrinkles in her dress. የተጨማደደውን ፡ ልብሷን ፡ በተኵስ ፡ አስተካከለችው

**be full of wrinkles** ተጨማደደ
Her face is full of wrinkles. ፊቷ ፡ ተጨማዷል
[See also 'seam']

**wrist** የእጅ ፡ አንጓ
I dislocated my wrist when trying to lift the heavy box. ከባዱን ፡ ሣጥን ፡ አነሣለሁ ፡ ብዬ ፡ የእጄን ፡ አንጓ ፡ ወለም ፡ አለኝ

**wrist watch** የእጅ ፡ ሰዓት
Buy me a wrist watch! የእጅ ፡ ሰዓት ፡ ግዛልኝ

**writ** ማዘዣ
A writ from the judge ordered the man's release from jail. የዳኛው ፡ ማዘዣ ፡ ሰውዬው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ እንዲለቀቅ ፡ አዘዘ

**write** (wrote), vt.
1. ጻፈ. Write me a letter! ደብዳቤ ፡ ጻፍልኝ
2. ደረሰ. Dickens wrote novels. ዲክንስ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪኮችን ፡ ደረሰ
Mozart wrote symphonies. ሞዛርት ፡ ሲምፎኒ ፡ ሙዚቃ ፡ ደረሰ

**write** (vi.)
1. ጻፈ. He writes with a pen. በብዕር ፡ ይጽፋል
This pen doesn't write. ይህ ፡ ብዕር ፡ አይጽፍም
2. ጽሑፍ ፡ አቀረበ. He writes for the newspaper. ለጋዜጣው ፡ ጽሑፍ ፡ ያቀርባል

**be written**
1. ተጻፈ. The letter was written in Greek. ደብዳቤው ፡ በግሪክ ፡ ተጻፈ
2. ተነበበ. Joy was written all over her face. ደስታ ፡ በፊቷ ፡ ላይ ፡ ይነበብ ፡ ነበር

**write down** ጻፈ
Write down that telephone number before you forget it! ያንን ፡ የስልክ ፡ ቁጥር ፡ ሳትረሳው ፡ ጻፈው

**write off**
*He wrote it off as something bought on the installment plan which would never be paid for. በዱቤ ፡ የሸጠውን ፡ እንደማይከፈለው ፡ ያህል ፡ ቈጠረው

**(be) written off** ዋጋ ፡ ተከፍሎ ፡ አለቀ
The new equipment was written off in three years. ያዲሱ ፡ እቃ ፡ ዋጋ ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ተከፍሎ ፡ አለቀ

**write out** ጻፈ
Please write out that check for me before I go. እስቲ ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ቼኩን ፡ ጻፍልኝ

**(be) written up** ተጻፈ
His adventures were written up in the papers. የደረሰበት ፡ ነገር ፡ በጋዜጣዎች ፡ ተጻፈ

**writer** ደራሲ
My son wants to become a writer. ልጄ ፡ ደራሲ ፡ ለመሆን ፡ ይፈልጋል

**write-up** የተጻፈ ፡ ሐተታ
The write-up of his activities covered a whole page. ስለሱ ፡ ሥራዎች ፡ የተጻፈው ፡ ሐተታ ፡ አንድ ፡ ሙሉ ፡ ገጽ ፡ ወሰደ

**writhe**
1. ተጥመለመለ. The snake writhed along the branch. እባቡ ፡ ቅርንጫፉ ፡ ላይ ፡ እየተጥመለመለ ፡ ሄደ
2. ተንፈራፈረ. The wounded man writhed in pain. የቈሰለው ፡ ሰው ፡ በሥቃይ ፡ ተንፈራፈረ

**writing**
1. መጻፍ. I don't get around to writing. ለመጻፍ ፡ ጊዜ ፡ የለኝም
2. ጽሕፈት. I can't read his writing. የሱን ፡ ጽሕፈት ፡ ለማንበብ ፡ አልችልም
He is busy with his writing. ጽሕፈት ፡ ይዞ ፡ ይጣደፋል
3. ጽሑፍ. You had better put your agreement in writing. ስምምነታችሁን ፡ በጽሑፍ ፡ ብታሰፍሩት ፡ ይሻላል
The writings of this author are translated into several languages. የዚህ ፡ ደራሲ ፡ ጽሑፎች ፡ በብዙ ፡ ቋንቋዎች ፡ ተተርጕመዋል

**writing material** መጻፊያ
Vellum is used as writing material. ብራና ፡ ለመጻፊያ ፡ ያገለግላል

**wrong** (v.) በደለ (ተበደለ)
He wronged me when he said I had stolen it. ሰርቀሃል ፡ ስላለኝ ፡ በድሎኛል
He felt wronged. የተበደለ ፡ መሆኑ ፡ ተሰማው

**wrong** (n.)
1. ስሕተት. Can't you differentiate between right and wrong? ትክክለኛውን ፡ ከስሕተት ፡ ለመለየት ፡ አትችልም ?
2. በደል. The wrong she had suffered made her bitter. የደረሰባት ፡ በደል ፡ በጣም ፡ አማረራት
3. ጥፋት. I have done no wrong, officer. I was going only five miles an hour. ጌታዬ ፤ ምንም ፡ ጥፋት ፡ አላደረግሁም ፤ እነዳ ፡ የነበረው ፡ በሰዓት ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ ብቻ ፡ ነበር

**wrong** (adj.)
1. የተሳሳተ. He caught himself before he said the wrong thing. የተሳሳተ ፡ ነገር ፡ ከመናገሩ ፡ በፊት ፡ ራሱን ፡ ገታ
She dialed the wrong number. የተሳሳተ ፡ ቁጥር ፡ ደወለች
2. ስሕተት ፡ የሆነ. He had six wrong answers on the test. በፈተናው ፡ ላይ ፡ ስድስት ፡ ስሕተት ፡ የሆኑ ፡ መልሶች ፡ ሰጠ
3. የማይስማማ. Red is the wrong color for her. ቀይ ፡ ለሷ ፡ የማይስማማት ፡ ቀለም ፡ ነው
4. የሌላ ፡ ሰው. In a moment of abstraction, he grabbed the wrong hat. በሐሳብ ፡ ተውጦ ፡ ሳለ ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ባርኔጣ ፡ ወሰደ
5. የማይሆን. The policeman tagged the car for parking on the wrong side of the street. መኪናውን ፡ እማይሆን ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስላቆመ ፡ ፖሊሱ ፡ መጥሪያ ፡ ሰጠው
6. ሌላ. Without my glasses, I blundered into the wrong room. መነጽሬን ፡ ሳላደርግ ፡ ቀርቼ ፡ በስሕተት ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ
7. (= noun) ኀጢአት. Killing is wrong. መግደል ፡ ኀጢአት ፡ ነው
8. (= noun) ብልሽት. What's wrong with the car? መኪናው ፡ ምን ፡ ብልሽት ፡ ደረሰበት ?
9. (= noun) ያልሆነ ፡ ነገር. I sensed right away that something was wrong. ያልሆነ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተሰማኝ
10. (= noun) ስሕተት. The answer is wrong anyway you look at it. በየትኛውም ፡ አንጻር ፡ ብትመለከተው ፡ መልሱ ፡ ስሕተት ፡ ነው

**be wrong**
1. ተሳሳተ. I am afraid you are wrong. የተሳሳትክ ፡ ይመስለኛል
2. ተበላሸ. The clock is wrong. ሰዓቱ ፡ ተበላሽቷል

**be wrong with**
*Something is wrong with the telephone. ስልኩ ፡ የተበላሸ ፡ ነገር ፡ አያጣም
*Is anything wrong with you? የሆንከው ፡ ነገር ፡ አለ ?

**do a wrong** በደለ
You do an honest man a wrong to call him a liar. ሐቀኛውን ፡ ሰው ፡ ዋሾ ፡ ብትለው ፡ ትበድለዋለህ

**do something wrong**
1. አሳሳተ. You did it wrong again. አሁንም ፡ አሳሳትክ
2. አሳስቶ ፡ ሠራ. I showed you how to do it, but you did it wrong again. እንዴት ፡ እንደምትሠራው ፡ አሳይቼህ ፡ ነበር ፤ ግን ፡ እንደገና ፡ አሳስተህ ፡ ሠራህ

**do wrong** አጠፋ
I have done no wrong. ምንም ፡ አላጠፋሁም

**get wrong**
Don't get me wrong! የምለው ፡ ይግባህ

**go wrong**
1. ተበላሸ. He went wrong as a result of associating with criminals. ከወንጀለኞቹ ፡ ጋር ፡ ከመወዳጀቱ ፡ የተነሣ ፡ ተበላሸ
2. አልቀናውም. I had a very trying day; everything seemed to go wrong. ቀኑ ፡ ለኔ ፡ አልሆነኝም ፤ ምንም ፡ ነገር ፡ አልቀናኝ
*Everything went wrong today. ዛሬ ፡ የተጣጋ ፡ ቀን ፡ ነው (or, ዛሬ ፡ ግሬ ፡ የገባው ፡ ቀን ፡ ነው)

**go (the) wrong way** መንገዱን ፡ ተሳሳተ
You're going the wrong way; turn around! መንገዱን ፡ ተሳስተሃል ፤ ተመለስ

**(be) in the wrong** ተሳሳተ
He admitted that he was in the wrong. መሳሳቱን ፡ አመነ

**turn out to be wrong** ሳይዝለት ፡ ቀረ
His forecast turned out to be wrong. ትንቢቱ ፡ ሳይዝለት ፡ ቀረ

**(in the) wrong direction** አላቅጣጫ
You're heading in the wrong direction. አላቅጣጫው ፡ ነው ፡ የምትሄደው
[See also 'rub']

**wrongdoer** ጥፋተኛ
Wrongdoers will be punished. ጥፋተኞች ፡ ይቀጣሉ

**wrongdoing** መጥፎ ፡ ተግባር ፡ መፈጸም
The thief was guilty of wrongdoing. ሌባው ፡ መጥፎ ፡ ተግባር ፡ በመፈጸሙ ፡ ጥፋተኛ ፡ ነበር

**wrongly** ተሳስቶ
He wrongly assumed that I was an Ethiopian. ተሳስቶ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አድርጎ ፡ ገመተኝ
[See also 'rightly']

**wrote**, see **write**

**wrought** የተሠራ
Beautifully wrought furniture is expensive. አምሮ ፡ የተሠራ ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ ውድ ፡ ነው

**be wrought** ተሠራ
The gate was wrought with great skill. መዝጊያው ፡ በታላቅ ፡ ጥበብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**(be) wrought-up** ተበሳጨ
He was wrought-up over his bills. በሚከፍለው ፡ ሒሳብ ፡ ተበሳጨ

**wrung**, see **wring**

**wry**
*She made a wry face to show her disgust. መጸየፏን ፡ ለመግለጽ ፡ ፊቷን ፡ ኮሶ ፡ አስመሰለች

# X

**xenophobia** [የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፡ የመጥላት ፡ስሜት]

# Y

**yacht** [ለሽርሽር ፡ ወይም ፡ ለእሽቅድምድም ፡ የሚያገለግል ፡ ጀልባ]

**yam** የስኳር ፡ ድንች
Some people eat roasted yams and pork. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የተጠበሰ ፡ የስኳር ፡ ድንችና ፡ የአሳማ ፡ ሥጋ ፡ ይበላሉ

**yank** ጐተት ፡ ጐተት ፡ አደረገ
He yanked the rope. ገመዱን ፡ ጐተት ፡ ጐተት ፡ አደረገው

**yank out** በድንገት ፡ ነቀለ
The dentist yanked out the aching tooth. የጥርስ ፡ ሐኪሙ ፡ የበሽተኛውን ፡ ጥርስ ፡ በድንገት ፡ ነቀለው

**yap** (yapped) አለዘነ
The dog is yapping. ውሻው ፡ ያለዝናል

**yard**
1. አጥር ፡ ግቢ. The house has a yard for the children to play in. ቤቱ ፡ ለልጆቹ ፡ መጫወቻ ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ አለው
2. ቦታ. The chicken yard is bare of grass. የዶሮዎቹ ፡ ቦታ ፡ ሣር ፡ የለበትም
3. ያርድ. The yard is 3 ft. long. አንድ ፡ ያርድ ፡ ሦስት ፡ ጫማ ፡ ይረዝማል
[See also 'lumber yard']

**yardstick** ያርድ
He measured the cloth with a yardstick. ጨርቁን ፡ በያርድ ፡ ለካ

**yarn**
1. ሱፍ ፡ ክር. I need some yarn to knit a sweater. ሹራብ ፡ ለመሥራት ፡ ሱፍ ፡ ክር ፡ ያስፈልገኛል
2. እየፈጠረ ፡ የሚያወራ ፡ ታሪክ. The sailors' yarns are very interesting. መርከበኞቹ ፡ እየፈጠሩ ፡ የሚያወሩቸው ፡ ታሪኮች ፡ በጣም ፡ ያስደስታሉ
[See also 'spin']

**yawn** (v.)
1. አዛጋ. He yawned to show that he was sleepy. እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ለማሳየት ፡ አዛጋ
2. አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ታየ. The canyon yawned beneath our feet. ገደሉ ፡ ከበታቻችን ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**year** ዓመት
Will he come back next year? በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ይመለሳል ?

**years** ዕድሜ
He is old for his years. በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ አርጅቷል

**year after year** በያመቱ
He visits his relatives year after year. ዘመዶቹን ፡ በያመቱ ፡ ይጠይቃል

**years ago** ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት
That happened years ago. ያ ፡ የሆነው ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው

**year before last** አቻምና
The year before last it was very dry. አቻምና ፡ በጣም ፡ ደረቅ ፡ ነበር

**year by year** በያመቱ
Grain exports increase year by year. ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚላክ ፡ እህል ፡ በያመቱ ፡ ይጨምራል

**year in, year out** ከዓመት ፡ ዓመት
Year in, year out, the same routine. ከዓመት ፡ ዓመት ፡ ያው ፡ ይደጋገማል

**Year of Grace** ዓመተ ፡ ምሕረት
The Year of Grace means the Ethiopian year. ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ ማለት ፡ ነው

**academic year** የትምህርት ፡ ዓመት
The academic year is nine months long. የትምህርቱ ፡ ዓመት ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ነው

**all year round** ዓመቱን ፡ በሙሉ
They live in the country all year round. ዓመቱን ፡ በሙሉ ፡ የሚኖሩት ፡ ባላገር ፡ ነው

**for years** ለብዙ ፡ ዓመታት ፤ ብዙ ፡ ዓመታት
I haven't seen him for years. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አላየሁትም
We lived there for years. እዚያ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ኖርን

**in years** ለብዙ ፡ ዓመታት
I haven't seen him in years. ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ አላየሁትም

**last year** ዓምና
Last year I was in 6th grade. ዓምና ፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፡ ነበርኩ

**the year round** ከዓመት ፡ ዓመት
These birds are resident here the year round. እነዚህ ፡ ወፎች ፡ ከዓመት ፡ ዓመት ፡ እዚህ ፡ ይኖራሉ

**this year** በዚህ ፡ ዓመት ፤ ዘንድሮ
There was much rain this year. በዚህ ፡ ዓመት ፡ (ዘንድሮ) ፡ ብዙ ፡ ዝናብ ፡ ነበር
[See also 'early, get on, half, lean, leap year, mature, over, well']

**yearbook** ዓመታዊ ፡ መጽሔት
A yearbook lists all the companies in the country. ዓመታዊው ፡ መጽሔት ፡ በገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ኩባንያዎች ፡ ሁሉ ፡ ይዘረዝራል

**yearling** አንድ ፡ ዓመት ፡ የሞላው
Yearling calves are sold at a high price. አንድ ፡ ዓመት ፡ የሞላቸው ፡ ጥጃዎች ፡ በከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣሉ

**yearlong** ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚቆይ
There are few yearlong religious observances. ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚቆዩ ፡ ጥቂት ፡ የሃይማኖት ፡ በዓላት ፡ አሉ

**yearly** (adj.)
1. የዓመት. His yearly income is $10,000. የዓመት ፡ ገቢው ፡ ዐሥር ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ነው
Last month I took my yearly vacation. ባለፈው ፡ ወር ፡ የዓመት ፡ ፈቃዴን ፡ ወሰድኩ
2. (= adv.) በያመቱ. My uncle pays us a yearly visit. አጐቴ ፡ በያመቱ ፡ ይጠይቀናል
He sent me his yearly greetings. በያመቱ ፡ የሚልክልኝን ፡ የመልካም ፡ ምኞት ፡ መግለጫ ፡ ላከልኝ
3. (= adv.) ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ. The earth makes a yearly revolution around the sun. መሬት ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይን ፡ ትዞራለች

**yearly** (adv.)
1. በዓመት. How much money does he make yearly? በዓመት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ያገኛል ?
2. በያመቱ. This company sends out calendars to its customers yearly. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ ለደንበኞቹ ፡ በያመቱ ፡ የቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ ያድላል

**yearn**
1. ናፈቀ ፤ ጓጓ. I yearn to return home again. ወደ ፡ ቤት ፡ ለመመለስ ፡ ናፍቆያለሁ ፡ (ጓጕቻለሁ)
2. ራራ. Her heart yearned for the starving children. ለተራቡት ፡ ልጆች ፡ ልቧ ፡ ራራ

**yearning** ናፍቆት
His yearning for his country is well described in the book. ስለ ፡ አገሩ ፡ ያለው ፡ ናፍቆት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ ተገልጿል

**yeast** እርሾ
She prepared the yeast for baking bread. ዳቦውን ፡ ለመጋገር ፡ እርሾ ፡ አዘጋጀች

**yell** (v.) ጮኸ
We heard someone yelling for help. አንድ ፡ ሰው ፡ ለርዳታ ፡ ሲጮኽ ፡ ሰማን
He yelled with pain. ስላመመው ፡ ጮኸ

**yell for help** ኡ ፡ ኡ ፡ አለ
He yelled for help in vain. ኡ ፡ ኡ ፡ ያለው ፡ በከንቱ ፡ ነበር

**yell** (n.) ጩኸት
He let out a yell when he stepped on a thorn. እሾህ ፡ ሲወጋው ፡ ጩኸቱን ፡ ለቀቀ

**give a loud yell** ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ጮኸ
The lusty baby gave a loud yell as soon as he became hungry. የፋፋው ፡ ሕፃን ፡ ወዲያው ፡ እንደራበው ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ጮኸ

**yellow** (v.) ብጫ ፡ ሆነ
Paper yellows with age. ወረቀት ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ ብጫ ፡ ይሆናል

**yellow** (adj.) ብጫ ፤ ቢጫ
The cover of the book is yellow. የመጽሐፉ ፡ ልባስ ፡ ብጫ ፡ (ቢጫ) ፡ ነው

**be yellow** ፈራ
Don't be so yellow! That dog won't bite you. እስከዚህ ፡ አትፍራ ፤ ውሻው ፡ አይነክስህም

**yellow fever** ብጫ ፡ ወባ
I had yellow fever. ብጫ ፡ ወባ ፡ ይዞኛል

**yelp** አለቀሰ
The dog yelped with pain. ከሥቃይ ፡ የተነሣ ፡ ውሻው ፡ አለቀሰ

**yes**
1. አዎ ፤ አዎን. Can you read this? Yes. ይህን ፡ ልታነብ ፡ ትችላለህ ? አዎ ፡ (አዎን)
2. እሺ. Yes sir, I'll do it right away. እሺ ፡ ጌታዬ ፤ አሁኑኑ ፡ እሠራዋለሁ
Come here at once! Yes sir! ወዲህ ፡ ና ፡ ቶሎ! እሺ
He said "yes" when I asked him. ብጠይቀው ፡ እሺ ፡ አለ

**yesterday** ትላንትና ፤ ትናንትና ፤ ትናንት ፤ ትላንት
Yesterday it rained. ትላንት ፡ ዘነበ

**the day before yesterday** ከትናንትና ፡ ወዲያ
You came the day before yesterday. የመጣኸው ፡ ከትናንትና ፡ ወዲያ ፡ ነበር
[See also 'late']

**yet** (adv.)
1. ገና. You'll drive me crazy yet. አንተ ፡ ገና ፡ ታሳብደኛለህ
There is much work yet to be done. ገና ፡ ብዙ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ አለ
Did you see the new play yet? አዲሱን ፡ ቲያትር ፡ ገና ፡ አላየኸውም ?
Haven't you read the book yet? መጽሐፉን ፡ ገና ፡ አላነበብከውም ?
It was not yet dark. ገና ፡ አልጨለመም ፡ ነበር
2. አሁን. Don't go yet! አሁን ፡ አትሂድ
We can't leave just yet. አሁን ፡ ልንሄድ ፡ አንችልም
3. አሁንም. Be thankful you are yet alive. አሁንም ፡ በሕይወት ፡ በመገኘትህ ፡ እግዜርን ፡ አመስግን
4. ወደፊት. I may yet get rich. ወደፊት ፡ እበለጽግ ፡ ይሆናል
5. ሆኖም. The story was strange, yet true. ወሬው ፡ እንግዳ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ እውነተኛ ፡ ነው
6. እንዲያውም. The king spoke yet more harshly. ንጉሡ ፡ እንዲያውም ፡ በቁጣ ፡ ተናገሩ

**yet** (conj.) ነገር ፡ ግን
He didn't want to go, yet he had to. ለመሄድ ፡ አልፈለገም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**and yet** ሆኖም
And yet you can't help liking him. ሆኖም ፡ እሱን ፡ መውደድህ ፡ አይቀርም

**as yet** እስካሁን ፤ እስካሁን ፡ ድረስ
As yet, we have made no plans. እስካሁን ፡ (እስካሁን ፡ ድረስ) ፡ ምንም ፡ አላቀድንም

**not yet**
1. ገና + (affirmative verb). It's not yet time to go. የመሄጃው ፡ ሰዓት ፡ ገና ፡ ነው
Are you finished? Not yet. ጨርሰሃል ? ገና ፡ ነው
2. ገና + (negative verb). Haven't you seen him yet? ገና ፡ አላገኘኸውም ?
I'm not yet done. ገና ፡ አልጨረስኩም

**yield** (vt.)
1. አስገኘ. His business doesn't yield much profit. ሥራው ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ አያስገኝም
The money yields interest. ገንዘቡ ፡ ወለድ ፡ ያስገኛል
2. አፈራ. These trees yield fruit. እነዚህ ፡ ዛፎች ፡ ፍሬ ፡ ያፈራሉ
3. ለቀቀ. The enemy yielded the city. ጠላት ፡ ከተማዋን ፡ ለቀቀ

**yield** (vi.)
1. ተረታ. I'll yield on this point. እዚህ ፡ ላይ ፡ እረታለሁ
2. እጅ ፡ ሰጠ. The enemy yielded to our soldiers. ጠላት ፡ ለወታደሮቻችን ፡ እጁን ፡ ሰጠ

**yield (one's) consent** ተስማማ
Her father yielded his consent to the plan. አባቷ ፡ በእቅዱ ፡ ተስማማ

**yield ground** አፈገፈገ
The troops had to yield ground to the enemy. ወታደሮቹ ፡ ለጠላት ፡ ማፈግፈግ ፡ ነበረባቸው

**yield to** ተቀበለ
The father yielded to his request. አባትዬው ፡ ልመናውን ፡ ተቀበለው
*He yielded to curiosity and opened the letter addressed to his father. ጉጉት ፡ ገፋፍቶት ፡ ላባቱ ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከፈተው
*They will yield only to force. የሚያሸንፉቸው ፡ በኀይል ፡ ብቻ ፡ ነው
*The door yielded to his touch. በሩን ፡ ገና ፡ ሲነካው ፡ ተከፈተ
[See also 'temptation']

**yield** (n.) ምርት
The yield this year is much greater than it was last year. የዘንድሮው ፡ ምርት ፡ ከዓምናው ፡ በጣም ፡ ይበልጣል

**(be) yielding** ትሙክ ፡ ትሙክ ፡ አለ
It was soft and yielding to the touch. ሲዳሰስ ፡ ለስላሳና ፡ ትሙክ ፡ ትሙክ ፡ የሚል ፡ ነበር

**have a yielding nature** እሺ ፡ ባይ ፡ ነው
She has a yielding nature with her children. ለልጆቿ ፡ እሺ ፡ ባይ ፡ ናት

**yogurt** እርጎ
Some people like to eat yogurt. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እርጎ ፡ መጠጣት ፡ ይወዳሉ

**yoke** (v.) ጠመደ
The farmer yoked his oxen. ገበሬው ፡ በሬዎቹን ፡ ጠመደ

**be yoked** ተሳሰረ
They are yoked in marriage. በጋብቻ ፡ ተሳስረዋል

**yoke** (n.) ቀንበር
The oxen were strong and broke the yoke. በሬዎቹ ፡ ኀይለኞች ፡ ስለሆኑ ፡ ቀንበሩን ፡ ሰበሩት
The enemy's yoke was broken by our patriots. የጠላት ፡ ቀንበር ፡ ባርበኞቻችን ፡ ነኰተ

The people were under the yoke of a dictator. ሕዝቡ ፡ በአምባገነን ፡ ቀንበር ፡ ሥር ፡ ነበር

**yoke of oxen** የተጠመዱ ፡ ጥንድ ፡ በሬዎች
The plow was drawn by the yoke of oxen. ሞፈሩ ፡ የሚጐተተው ፡ በተጠመዱ ፡ በጥንድ ፡ በሬዎች ፡ ነበር

**have a yoke on the neck** ተጠመደ
The oxen do not like to have a yoke on their necks. በሬዎቹ ፡ መጠመድ ፡ አይወዱም

**yolk** የእንቁላል ፡ አስኳል
The yolk of the egg is yellow. የእንቁላል ፡ አስኳል ፡ ብጫ ፡ ነው

**yonder** adj. (= adv.) እዚያ ፡ ማዶ
There is still snow on yonder mountain. እዚያ ፡ ማዶ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ አሁንም ፡ በረዶ ፡ አለ

**yonder** (adv.) እዚያ
Look yonder! እዚያ ፡ ተመልከት

**over yonder** እዚያ ፡ ማዶ
The house is over yonder. ቤቱ ፡ እዚያ ፡ ማዶ ፡ ነው

**you** (subject)
1. አንተ (masc. sg.), አንቺ (fem. sg.), እናንተ (pl. com.), እርስዎ (resp.)
You (masc. sg.) are a good student. አንተ ፡ ጐበዝ ፡ ተማሪ ፡ ነህ
You (fem. sg.) are a good student. አንቺ ፡ ጐበዝ ፡ ተማሪ ፡ ነሽ ፡
You are good students. እናንተ ፡ ጐበዝ ፡ ተማሪዎች ፡ ናችሁ
You (resp.) are a good teacher. እርስዎ ፡ ጐበዝ ፡ አስተማሪ ፡ ነዎት
2. ሰው. When you have been ill, your face is sometimes pale. ሰው ፡ ሲታመም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ ይገረጣል
3. (plural). The days pass quickly when you are busy. ሥራ ፡ ሲይዙ ፡ ቀኑ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል

**you** (direct object) -ህ (masc. sg.), -ሽ (fem. sg.), -ዐችሁ (pl. com.), -ዎ, -ዎት (resp.)
Yesterday I saw you (sg. masc.). ትናንት ፡ አየሁህ
Yesterday I saw you (sg. fem.). ትናንት ፡ አየሁሽ
Yesterday I saw you (pl.). ትናንት ፡ አየኋችሁ
Yesterday I saw you (resp.). ትናንት ፡ አየሁዎ ፡ (አየሁዎት)

**young** (n.)
1. ልጅ. The cat fought to defend its young. ድመቲቱ ፡ ልጇቿን ፡ ተከላከለች
2. ግልገል. Some animals will fight to protect their young. ብዙ ፡ እንስሳት ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ ከፉ ፡ እንዳያገኛቸው ፡ ይከላከላሉ
3. ወጣት ፣ ወጣቶች. This is a game for young and old. ይህ ፡ ለወጣትም ፡ ለሽማግሌም ፡ የሚሆን ፡ ጨዋታ ፡ ነው
The educated young of today have different ideas. የዛሬ ፡ ጊዜ ፡ የተማሩ ፡ ወጣቶች ፡ የተለየ ፡ አስተሳሰብ ፡ አላቸው

**young** (adj.)
1. ልጅ. She looks very young for her age. ለዕድሜዋ ፡ በጣም ፡ ልጅ ፡ ትመስላለች
2. ወጣት. She is very young for her age. ለዕድሜዋ ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ ናት
The young lawyer lacked assurance. ወጣቱ ፡ ጠበቃ ፡ በራሱ ፡ የመተማመን ፡ ጠባይ ፡ ይጐድለዋል
3. (= adv.) እንደ ፡ ሕፃን. John is young for his years. ጆን ፡ በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ነው
4. ታዳጊ. Kenya is a young nation. ኬንያ ፡ ታዳጊ ፡ አገር ፡ ነች
There are many young trees in this park. እዚህ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ታዳጊ ፡ ዛፎች ፡ አሉ

**young** (adv.) እንደ ፡ ወጣት
She acts young for her years. ከዕድሜዋ ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ የምትሠራው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ወጣት ፡ ነው

**young child** ሕፃን ፡ ልጅ
A young child needs motherly love. ሕፃን ፡ ልጅ ፡ የእናት ፡ ፍቅር ፡ ይፈልጋል

**young couple** ወጣት ፡ የሆኑ ፡ ባልና ፡ ሚስት
Triplets were born to a young couple recently. በቅርቡ ፡ ወጣት ፡ የሆኑ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሦስት ፡ መንታ ፡ ወለዱ

**young man** ወጣት
Who is that young man? ያ ፡ ወጣት ፡ ማን ፡ ነው ?

**young man!** ወንድም
Listen to me, young man! ወንድም ፤ አዳምጠኝ!

**young people**
1. ወጣቶች. The young people had a lot of fun. ወጣቶቹ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ነበር
2. ልጅ ፡ እግሮች. There was a sprinkling of young people in the congregation. በምእመናኑ ፡ መካከል ፡ ልጅ ፡ እግሮች ፡ እልፎ ፡ እልፎ ፡ ይታዩ ፡ ነበር

**young woman** ልጅ ፡ እግር ፡ ሴት
A young woman came to see me. ልጅ ፡ እግር ፡ ሴት ፡ ልትጠይቀኝ ፡ መጣች

**(the) night is yet young** ገና ፡ አልመሸም
Please stay! The night is yet young. ቆይ ፡ እባክህ ፤ ገና ፡ አልመሸም

**with young** ግልገል ፡ ያላት

A wild animal with young is dangerous. ግልገል ፡ ያላት ፡ አውሬ ፡ አደገኛ ፡ ናት

**younger**

1. ታናሽ. My younger brother was killed in the war. ታናሽ ፡ ወንድሜ ፡ ጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተ
2. ትንሽ. Pliny the Younger wrote a series of biographies. ትንሹ ፡ ፕሊኒ ፡ ተከታታይ ፡ የሕይወት ፡ ታሪኮች ፡ ጽፏል
3. የመጨረሻ. The younger son has pretentions to the estate. የመጨረሻው ፡ ልጅ ፡ መሬቱ ፡ ይገባኛል ፡ ባይ ፡ ነው

**youngish** ልጅ

He looks youngish for his age. ለዚህ ፡ ዕድሜው ፡ ልጅ ፡ ይመስላል

**youngster** ወጣት

The youngsters stood around in the school-yard. ወጣቶቹ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ዙሪያውን ፡ ቆሙ

**your**

1. -ህ ፣ ያንተ (masc. sg.). Your clothes are dirty, my boy. ልብስህ ፡ (ያንተ ፡ ልብስ) ፡ ቆሽሿል ፡ ልጄ
2. -ሽ ፣ ያንቺ (fem. sg.). Your dress is torn, my girl. ልብስሽ ፡ (ያንቺ ፡ ልብስ) ፡ ተቀዷል ፡ ልጄ
3. -aችሁ ፣ የናንተ (pl. com.). Put your books away, children! ልጆች ፣ መጽሐፎቻችሁን ፡ (የናንተን ፡ መጽሐፎች) ፡ አስቀምጡ
4. -ዎ ፣ የርስዎ (resp.). Is this your book, sir? ይህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ (የርስዎ ፡ መጽሐፍ) ፡ ነው ፡ ጌታዬ?

**yours**

1. ያንተ (masc. sg.). The book is yours, my boy. መጽሐፉ ፡ ያንተ ፡ ነው ፣ ልጄ
2. ያንቺ (fem. sg.). The chair is yours, my girl. ወንበሩ ፡ ያንቺ ፡ ነው ፣ ልጄ
3. የናንተ (pl. com.). These books are yours, boys. ልጆች ፣ እነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ የናንተ ፡ ናቸው
4. የርስዎ (resp.). The book is yours, sir. መጽሐፉ ፡ የርስዎ ፡ ነው ፣ ጌታዬ

**yourself**

1. (subject) አንተ ፡ ራስህ (sg. masc.), አንቺ ፡ ራስሽ (sg. fem.), እናንተ ፡ ራሳችሁ (pl. com.), እርስዎ ፡ ራስዎ (resp.).
You yourself said so. አንተ ፡ ራስህ ፡ ነህ ፡ እንደዚያ ፡ ያልከው
2. አንተው (sg. masc.), አንቺው (sg. fem.), እናንተው (pl. com.), እርስዎው (resp.).
Did you knit these gloves yourself? ይህንን ፡ የእጅ ፡ ሹራብ ፡ የጠለፍሽው ፡ አንቺው ፡ ነሽ?
3. (object) ራስህን (sg. masc.), ራስሽን (sg. fem.), ራሳችሁን (pl. com.), ራስዎን (resp.).
Ask yourself what you really want. በእርግጥ ፡ ምን ፡ እንደምትፈልግ ፡ ራስህን ፡ ጠይቅ
*Can you identify yourself? ማን ፡ እንደሆንክ ፡ ልትነግረን ፡ ትችላለህ ?

**feel like yourself** (masc. sg.) እንደወትሮህ ፡ ትሆናለህ

Now that your cold is better, you'll feel like yourself again. አሁን ፡ ጉንፋንህ ፡ የተሻለህ ፡ ስለሆነ ፡ እንደገና ፡ እንደወትሮህ ፡ ትሆናለህ

**youth** (n.)

1. ወጣት. As a youth, he showed no promise. ወጣት ፡ ሳለ ፡ ምንም ፡ ተስፋ ፡ የሚጣልበት ፡ መልክ ፡ አላሳየም ፡ ነበር
He has the vigor of youth. የወጣት ፡ ወኔ ፡ አለው
2. ወጣቶች. There is a club for the youth in our town. በከተማችን ፡ ውስጥ ፡ የወጣቶች ፡ ክበብ ፡ አለ
3. ልጅነት ፣ የወጣትነት ፡ ዘመን. He had to work hard in his youth. በልጅነቱ ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ ነበረበት
He mourned his misspent youth. በባከነው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ ተጸጸተ
4. ልጅ ፡ መሆን. His youth was an obstacle to his success. ልጅ ፡ መሆኑ ፡ ለዕድሉ ፡ መቃናት ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆነበት

**youth** (adj.) የወጣቶች

The youth movement in Europe was started in the beginning of the 20th century. በአውሮፓ ፡ የወጣቶች ፡ ንቅናቄ ፡ የተጀመረው ፡ በሃያኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ነው
[See also 'bloom']

**youthful**

1. የወጣትነት. She still has a youthful appearance. አሁንም ፡ የወጣትነት ፡ መልክ ፡ ይታይባታል
2. ወጣት. He still looks youthful. አሁንም ፡ ወጣት ፡ ይመስላል

## Z

**zeal** ቅንአት
His zeal for the faith brough him the martyr's crown. በእምነቱ ፡ የነበረው ፡ ቅንአት ፡ የሰማዕትነትን ፡ ዘውድ ፡ አቀዳጀው

**zealot** ቀናኢ
He is a zealot who can tolerate no religion but his own. የራሱን ፡ እንጂ ፡ የሌላን ፡ ሃይማኖት ፡ መኖር ፡ የማይፈልግ ፡ ቀናኢ ፡ ነው

**zealous** ቀናኢ
Abuna Petros was a zealous patriot. አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቀናኢ ፡ አርበኛ ፡ ነበሩ

**zebra** የሜዳ ፡ አህያ
Hunting zebras is not permitted. የሜዳ ፡ አህያ ፡ ማደን ፡ አይፈቀድም

**zebu** በሬ
The Ethiopian zebu has a hump. የኢትዮጵያ ፡ በሬ ፡ ሻኛ ፡ አለው

**zenith**
1. የሰማይ ፡ እምብርት. The stars that are near the zenith sparkle. ከሰማዩ ፡ እምብርት ፡ አጠገብ ፡ ያሉት ፡ ከዋክብት ፡ ብልጭ ፡ ድርግም ፡ ይላሉ
2. ከፍተኛ ፡ ደረጃ. Rome reached the zenith of its power in 225 A.D. በ፪፻፳፭ ዓ. ም. ሮም ፡ የኀይሏን ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ደረሰች

**zephyr** በጣም ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ ነፋስ
A zephyr ruffled her hair. በጣም ፡ ለዘብ ፡ ያለ ፡ ነፋስ ፡ ጸጉሯን ፡ አመሳቀለው

**zero** (v.), ~ **in** አነጣጠረ
They zeroed in their cannons on the church. መድፋቸውን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ላይ ፡ አነጣጠሩ

**zero** (zeros, or zeroes), n. ዜሮ
Two minus two is zero. ከሁለት ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ሲነሣ ፡ ዜሮ ፡ ይቀራል
There are three zeros in 1,000. በ 1,000 ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ዜሮ ፡ አለ

**zero** (adj.) የዜሮ
At zero hour the attack will begin. በዜሮ ፡ ሰዓት ፡ ጥቃቱ ፡ ይጀምራል

**sink to zero** ከንቱ ፡ ሆነ
My hopes of getting a new car sank to zero. አዲስ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ የነበረኝ ፡ ተስፋ ፡ ከንቱ ፡ ሆነ

**zest**
1. ድምቀት. Your presence will add zest to the party. ያንተ ፡ መኖር ፡ ለግብዣው ፡ ድምቀት ፡ ይጨምርለታል
2. ወዝ. He added zest to the discussion by making good suggestions. ጥሩ ፡ ሐሳቦችን ፡ በማቅረብ ፡ ለውይይቱ ፡ ወዝ ፡ ሰጠው
3. የደስታ ፡ መንፈስ. He works with zest. በደስታ ፡ መንፈስ ፡ ይሠራል
*He ate with zest. ጥርቅም ፡ አድርጎ ፡ በላ

**have zest** ተደሰተ
He has zest for life. በኑሮ ፡ ይደሰታል

**zigzag** (zigzagged), v. የተጠማዘዘ ፡ መሥመር ፡ ሠራ
Lightning zigzagged across the sky. ብልጭልጭታው ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የተጠማዘዘ ፡ መሥመር ፡ ሠራ

**zigzag down** እየተጠማዘዘ ፡ ወረደ
The road zigzagged down the side of the mountain. መንገዱ ፡ በተራራው ፡ ሥር ፡ እየተጠማዘዘ ፡ ወረደ

**zigzag** (n.) የተጠማዘዘ ፡ ቅርጽ
The border of the picture is formed by a zigzag. የሥዕሉ ፡ ጠርዝ ፡ የተጠማዘዘ ፡ ቅርጽ ፡ አለው

**in zigzag** እየተጠማዘዘ
He ran in a zigzag to avoid being shot. ተኩስ ፡ እንዳይመታው ፡ እየተጠማዘዘ ፡ ሮጠ

**zinc** ዚንክ
Roofing tin is plated with zinc. የቤት ፡ ክዳን ፡ ቆርቆሮ ፡ ዚንክ ፡ ይቀባል

**zip** (zipped) ተፈተለከ
He zipped through the town. በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ተፈተለከ

**zip past one** ባጠገቡ ፡ እያፏጨ ፡ አለፈ
Bullets zipped past me. ጥይት ፡ ባጠገቤ ፡ እያፏጨ ፡ አለፈ

**zip through** በቶሎ ፡ ጨረሰ
He zipped through the lesson. ጥናቱን ፡ በቶሎ ፡ ጨረሰ

**zip up** ዚፑን ፡ ሳበ(ለት) ፤ ዚፕር ፡ ዘጋ
Please zip me up! እስቲ ፡ ዚፑን ፡ ሳብልኝ
He zipped up his coat before going out. ከቤት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የኮቱን ፡ ዚፕር ፡ ዘጋው

**zipper** ዚፐር
The zipper on my jacket is broken. የጃኬቴ ፡ ዚፐር ፡ ተበላሽቷል

**zither** [ከሠላሳ ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ክሮች ፡ ያሉት ፡ በጣት ፡ የሚመታ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**zodiac** [በሐሳብ ፡ እኩል ፡ በሆኑ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ የተከፈለ ፡ የሰማይ ፡ መቀነት]

**zone** (v.)
1. **ከፈለ.** They zoned the city into five voting districts. ከተማውን ፡ ባምስት ፡ የምርጫ ፡ ወረዳ ፡ ከፈሉት
2. **ከለለ.** They zoned the east of the city as a residential area. የከተማውን ፡ የምሥራቅ ፡ ክፍል ፡ የመኖሪያ ፡ ሰፈር ፡ አድርገው ፡ ከልለዋል

**zone** (n.)
1. **ክልል.** This is a 25 mph. traffic zone. ይህ ፡ ከሃያ ፡ አምስት ፡ ማይል ፡ በላይ ፡ የማይነዳበት ፡ ክልል ፡ ነው
2. **የግዛት ፡ ክልል.** The Russians would not let anyone in their zone. ሩሲያውያን ፡ በግዛት ፡ ክልላቸው ፡ ውስጥ ፡ ማንንም ፡ አያስገቡም
3. **ክበብ.** In the frigid zone, plants cannot grow. በዓለም ፡ የበረዶ ፡ ክበብ ፡ ዕፀዋት ፡ አይበቅሉም

**border zone** የድንበር ፡ ክልል
No one is allowed in the border zone without a pass. በድንበሩ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ያለፈቃድ ፡ መግባት ፡ ለማንም ፡ አይፈቀድም

**zoo** የእንስሳት ፡ ማኖሪያ ፤ የአራዊት ፡ መጠበቂያ
The lions in the zoo are roaring. በእንስሳት ፡ ማኖሪያ ፡ (በአራዊት ፡ መጠበቂያ) ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ አንበሶች ፡ ያገሣሉ

**zoology** ዙኦሎጂ
Zoology teaches us about animal life. ዙኦሎጂ ፡ ስለ ፡ እንስሳት ፡ ሕይወት ፡ ያስተምራል

**zoom** እያጕረመረመ ፡ በረረ
The airplane zoomed through the air. አውሮፕላኑ ፡ እያጕረመረመ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ በረረ

**zoom past one** ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ
The cars zoomed past me. መኪናዎቹ ፡ ሽው ፡ ብለው ፡ አለፉኝ

**zoom up** በድንገት ፡ መጠቀ
The airplane zoomed up. አውሮፕላኑ ፡ በድንገት ፡ መጠቀ